"የካልቪኒዝም ጽንሰትና ውልደት፤ ክርስቶሳዊነት ወይንስ እልህና ፖለቲካ?"

"ቫለንቴን ግኖስቲካውያን"

1 .ታሪካዊ መንደርደሪያ

ታሪክ ወደ 20 አመተ ኩነኔ ይወሰደናል እስራኤላዊ ገዳማውያንን ወይም ኢሴኔሳውያንን ለማገናኘት:: እነዚህ የእስራኤል ገዳማውያን:: ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን የእስራኤልን የሃይማኖት ሃይልና ቤተ መቅደሱን በተቆጣጠሩ ጊዜ ወደ ቁምራን ዋሻ በማምራት በዛ ቅዱሳት መጻህፍትን በማጥናት: በማባዛትና በማስቀመጥ የተቀመጡ ማህበረሰቦች ነበሩ:: የቁምራንን አካባቢም የመረጡበት ምክኒያት በደረቅ አየር ጸባዩ የተነሳ ቅዱሳን መጻህፍትን ሳይበሰብስ ያተርፍልናል በሚል ሃሳብ እንደሆነም ይነግረናል:: ከነዚህም በተጨማሪ ደግሞ በግብጽ ተመሳሳይ ኢሴኔሳውያን ተነሱ: ምንም እንኳ ራሳቸውን ኢሴኔሳውያን ብለው ቢጠሩም ካእስራኤል ኢሴኔሳውያን የተለዩ እንደሆኑ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳናል:: የግብጾቹ ኢሴኔሳውያን በአይሁድ የአምልኮ ስርአት ላይ የአስማትና የጥንቆላ ልምምዶችን ጨምረው ይተገብሩ ነበር:: ከሌሎቹ በተቃራኒው እነዚህኞቹ ኢሴኔሳውያን ገዳማውያን እምነታቸውን በማሻሻል በኡደተ ሰጋዌ(REINCARNATION) በዝገመተ ለውጥ (የቅድስና ደረጃ በጨመረ ቁጥር ወደ እሳተ መለኮትነት ወደማደግ) እንዲሁም አስቀድሞ ውሳኔ(PREDESTINATION) እምነትን አዳበሩ:: ይህንን እምነታቸውን ከሂንዱ እመነት እንደተዋሱት የታሪክ ምሁራን ይናገራሉ::

ስለነዚህ ሰወች ታሪክ ጸሃፊው ጆሲፈስ የሚከተለውን አስፍሯል::
"ራሳቸውን ከወይን የከለክላሉ: የአትክልት ተመጋቢወች ናቸው: ቁጥቦች ናቸው: አካላዊ ትንሳኤን ይክዳሉ: መላእክትን በጸሎቶቻቸው ይማጸናሉ: የድንጋዮችንና የሰራሰሮችን አይነቶች ይማራሉ: ርኩሳን መናፍስትን የማስወጣት ልምምድ አላቸው: በአስማትና: ድንቆች ልምምዶች ላይ መጻህፍት ነበራቸው: ህልሞችን ይተረጉማሉ: የማለዳ የዘወትር ጸሎት አላቸው:"
(ጆሲፈስ አንቲቆስ 15:10:5)

2 .ስመኦን ማጉስ(10-65 AD)
ከቀደሙ የቤተ ክርስቲያን አባቶች አንዱ ቅዱስ ቀለሜንጦስ: በጥበበ ቀለሜንጦስ 2:5-16 ላይ "ጊታ ከምትባል ሰፈር በሰማርያ አውራጃ የሆነ የመጥሙቁ ዮሐንስ ደቀ መዝሙር የነበረ ሰው ነበረ:: ዮሐንስም በአደባባይ አገልግሎቱን በመጀመር ሰወችን ወደንሰሃ እየጠራ ለመሲሁ ህዝቡን ያዘጋጅ ነበር:: ስምኦንም በቅዱሳት መጻህፍት ትንቢቶችና ህጎች ተማረረ: በዚህ ጊዜም በግብጽ ስላሉት ኢሴኔሳውያን ዜና ይሰማ ነበር:: እነርሱ ዝም ብሎ መሲሁንና የመጠባበቅ አስልቺ ሁኔታ ውስጥ ሳየሆን በድንቆቸና በታምራቶች የታጀበ ኑሮ የኖሩ ነበር:: ወዲያውንም ዮሐንሰን ጥሎ ወደ ግብጽ አመራ ሰምኦን ከሄደ በሁኋላ መሲሁ መጥቶ በህግና በነብያት ስለእርሱ የተነገሩትን ፈጸመ:: ዮሐንሰም አንገቱ ተቀላ:: አንዳንዶቹ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትም የኢየሱስ ደቀ መዛሙርቶች ሆኑ:: መሲሁ ተሰቀለ: ተነሳ: አረገ፤ ቤተክርስቲያንም ተወለደች:: ይህ በሆነ ወደ ሶስት አመት ገደማ ሰመኦን ወደ እስራኤል ተመለሰ: በመጀመሪያም ወደ ሰማሪአ አመራ:: ሙሉ ለሙሉ በግብጻውያን ኢሴኔሳውያን አስተሳሰብ ተበክሎ ነበር የመጣው:: ታላቁ የማይገፋው እያለም ራሱን ይጠራ ነበር: ይህ አገላለጽ በግብጻውያን ኢሴኔሳውያን ዘንድ በትልቅ ደረጃ ከውሽት አካል ሰወችን ወደ እውነተኛ መንገድ ና አምላክነት የሚመራ ማለት ነበር:: በእርሱ እምነት በዳንኤል 9 የተጠቀሰው መሲህና የብሌይ ኪዳኑ እግዚአብሔር ከ 30ውቹ እውነተኛና ዘላለማዊ አማልክቶች መካከል ናቸው ብለ ያምን ነበር:: ይህ ሰው ወደ መንደሩ በምሞለስ ብዘወችን በድንቆችና በተአምራቶች እያታለለ እንዲያመለኩት ያደርግ ነበር:: እንደውም ሐውልት ሰርተው ታላቁ ሰው ብለው በመጻፍ እስከማምለክም ደርሰው ነበር:: ሰወቹን በደንብ እያጭበረበረ ከበዘበዛቸው በኋላ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ስለመሲሁ ኢየሱስ እርግጠኛ ባለመሆናቸው ዶሲጢረስ በተባለ ሰው መሪነት ቅዱሳት መጻህፍትን እየመረመሩ መሆናቸውን ሰማ እርሱም ወደነርሱ ወጥቶ ተገናኛቸው: ነገር ግን ሰምኦን የሚያደርገውን ነገር ለመቀበል አልፈለጉም: አንዳንዶቹም ኋላ ላይ ኢየሱስ በ ዳንኤል 9 የተጠቀሰው መሲህ መሆኑን በማመን የኢየሱስ ተከታዮች ሆኑ: እነሱንም በሐዋ 19:1-7 ላይ ኢየሱስን ሲሰብኩ እናገኛቸዋለን:: ነገር ግን ስለ መንፈስ

ቅዱስ ስጦታ አልሰሙም ነበር: እነርሱም በመጠመቅ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ተቀብለው አገልግሎታቸውን ቀጠሉ:: ስምኦንም ሐዋርያትን ለመፈለግ ወሰነ::(ሐዋ 8:9-11) ስምኦን ግን ልቦናው ሁሉ በግብጽ አሴኔሳውያን ስለታወረ አሁንም ልክ እንደ አስማቱ የመንፈስ ቀዱስን ስጦታ ለመግዛት አዝማሜአ ሰላሳየ ተወገዘ:(ሐዋ 8:18-23)" ከዛን ጊዜ ጀምሮ ማጉስ የተባለው ስምኦን እስከ እለተ ሞቱ ድረስ ክርስትናን ሲቃወም ኖረ:: በሞቱ እንኳ ይህ ሰው ቤተ ክርስቲያንን እረፍት አልሰጣትም፤ ከሞተም በኋላ እስከዛሬ ከእሱ ፍልስፍና የወጡ የፍልስፍና ትምህርቶች መለካቸውን ኤቄኤሩ የሱ ጦስ የቤተ ክርስቲያን የጎን ውጋት ሁኖ በበቀለችበት እየበቀለ በገባችበት እየገባ ግሪሳ ሁኖ ቤተ ክርስቲያንን ሲፈታተናት አለ: በዚህ አካሄድ የቲኦሎጅ ትምህርት ቤቶቿን ሳይቀር ተቆጣጥሮ የሄው ዛሬ ድረስ ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያን ለመግባት የሰመኦን ብቃዮች ፍቃድ ጠያቂ ለመሆን ተገደናል:: እነሱ ዛሬ እነማን ናቸው? እንዴትስ ይመሳሰላሉ መልካቸውን እንዴት ቀያየሩ? እየገባን እንየው::

3. የግኖስቲካውያን እምነት

የግኖስቲካውያን እምነት ማጉስ ከተባለው ስምኦን እምነት እንደመጣ ይነገራል: ልክ እንደ ስምኦን ሁሉ ሰላሳ ዘላለማዊ አማልክት እንዳሉ ያምናል:: እነዚህ አማለክትም በብሔረ አማልክት(PLEROMA) ከ ጊዜና ስማይ በላይ እንዳሉ ያስተምራሉ:: አምላኪት ሶፊያ የብሉይ ኪዳኑን እጅግ ሃያሉን እግዚአብሔርን ፈጠረችው: እርሱም ስለ ሌሎች ዘላለማዊ አማልክት ብዙም እውቀት የለውም:: ስለዚህም እሱ አንድ ብቸኛ አምላክ እንደሆነ አሰበ:: ሰውንም ፈጠረ:: ነገር ግን ሶፊያ ለሰው መንፈስን ሰጠችው:: አንዳንዶች መልካም ስራ በመሰራት ሲድኑ አንዳንዶች ግን ለገሃነም ተወሰነዋል:: ግኖስቲካውያን ሰው ከሶፊያ የወጣ መንፈስ ነው ብለው ያምናሉ:: ይህም የሚድኑት አሰቀድመው ተወሰነዋል ሚለውን እምነት እንዲመሰርቱ አደረጋቸው:: ስለዚህም የሚድኑት ደህንነታቸውን በምንም ሁኔታ መጥፎ እንኳ ቢሰሩ አያጡም የሚለውን እምነታቸውን እንዲፈለስፉ አደረጋቸው:: ይህም ወደ እንርሱ ሚለወጡትን ሴቶች ለማረከስ አበረታቷቸዋል:: ግዙፉ ሰማይና ምደርም ሃጢያት ስለሆነ ይጠፋል ይድን ዘንድም ኤeቻለውም ብለውም ያምናሉ:: እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ባሪያው አድርጎ በገነት ሰላሰቀመጣቸው በእውቀት ይድኑ ዘንድ ከአምላኮች አንዱ የሆነውን ሰይጣንን ባእባብ መልክ ላከችላቸው::

4. ቫለንቲናውያን ግኖስቲኮች::

ክግኖስቲክ ክፍሎች አንዱ የሆነው ቫለንቲናዊ ገኖስቲክ እምነት ከመንፈሳችን ይወጣል ብለው ያምናሉ:: ከተመረጡት ውስጥ ከሆንክ ደግሞ የምትወለድ ለመዳን ነው ይላሉ:: አንዳንዶች ደግሞ ለገሃነም ተፈጥረዋል ብለው ያስተምራሉ:: የተወሰኑት ደግሞ በስራቸው እንዲድኑ ዌeም እንዲጠፉ የተተው አሉ ብለው ያምናሉ:: መንፈሳቸውን ከሶፊያ ያገኙት በቻ ለመዳን ተመርጠዋልም ይላሉ:: ሌሎች ሁሉ ለገሃነም ተወሰነዋል በማለት እምነታቸውን ይገልጻሉ:: እነዚህ ለመዳን የተመረጡትም ምንም አይነት መልካም ስራ ከነሱ አይጠበቅም ይላሉ::

ከዚህ እንደምንረዳው እንግዲ በቤተክርስቲያን ታሪክ ወስጥ ቀድሞ ስለ ቅድመ ውሳኔ የስህተት ትምህርትን ያሰገባው ጠንቋዩ ሲሞን ሲሆን እሱን ተከትለው ግኖስቲከኮች ከዛም ሲከፋፈሉ ቫለነቲናውያን ይህን ሃሳብ አሰፍተው ዋና የትምህርታቸው መገለጫ አድርገውታል::

5. የሜኔቃያውን ትምህርት በአውግስጢንና በጵላጊየስ ውዝግብ የተነሳ በቤተ ክርስቲያን ዘልቆ መግባት::

አብዛኞቹ ግኖስቲካውያን በቤተክርስቲያን አባቶች ከፍተኛ የ እቅበተ እምነት ትግል: ድምጥማጣቸው እየጠፉ ቢመጣም በሁለተኛው ክፍለ ዘመን መካከል ላይ የቫለነቲያን እና የባስሊዳውያን የግኖስቲክ ክፍሎች ቀሩ:: በነዚህ በሁለቱ ክፍል ላይ ፍጹም የሆነ ተቃርኖ ስለነበር እርስ በእርሳቸው ተበላልተው እንደሚጠፉ ግልጽ እየሆነ ስለመጣ ለቤተ ክርስቲያን ትንሽ እርፈት ሰጥቷል:: የሁለቱ አመለካከት የቤተ ክርስቲያንን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ቆንጽሎ በመውሰድ ጽንፍ ረገጥ ነበር:: ቫለንቲያውያን ሰው ከሶፊያ መንፈስ በመወለድ አሰቀድሞ ለዘላለም ሂወት እና ወደገሃነም ለመጣል ተወሰኗል ሲሉ ባስሊዳውያን ደግሞ ሰው በራሱ ጽድቅ ሰርቶ ይድናል ብለው ያምኑ ነበር:: ቤተ ክርስቲያን ምንም እነኳ የቷስነ መዘናጋትን ብታሳይም ፈጽሞ ግን አላረፈችም: ነበር:: ቀስ በቀስም የባስሊዳዊአን እምነት እየሞተ መጣ:: በተቃራኒው ደግሞ ቫለነያናውያን እየጠነከሩና እየበረቱ ሌላ የቤተ ክርስቲያን ፈተና ወደመሆን መጡ

በተለይም በግብጽ ተራራማ ሰፍራወች ላይ ጥንካሬያቸው ጎልቶ ነበር:: ነገር ግን የህኛው የግኖስቲክ ክፍል ሲበረታ ቤተክርስቲያንም እቅበተ እምነቷን በማጠንከር መልሳ ቀበረችው:: በ 216 ኢ.ም ሜኔ የተባለ ሰው ተወለደ እርሱም ወደ አድገት ደረጃ ሲያድግ ታላላቅ ፍልሰፍናወችን አጠና:: እራሱንም የእግዚአብሔር ነብይ ነኝ ብሎ አወጀ:: ሌላ የግኖስቲካውያን የቤተ ክርስቲያን ፈተናም ከዚህ ይጀምራል::

6. ሜኔቃውያን

በ256 አካባቢ የሜኔ ተከታዮች ሜኔቃውያን በመባል የጠሩ ጀመር:: እነሱም ክርሰትናን ከቫለነቲያን እና የ ፐርሺያ እምነቶችጋ በመቀየጥ ማስተማር ጀመሩ:: ሜኒ እምነቱን ከክርሰቶሰና ከፐርሺያው ማጊ እንደተማረው ይናገር ነበር:: ሜኔ ሁለት አምለኮች አሉ አንደኛው ክፉው እና ሁለተኛው መጥፎው አምላክ በማለት ያሰተምር ነበር:: ኢየሱሰም የመጣው ሰውን ከሰይጣን ጋር ለማሰታረቅ ነው የመጣ ይል ነበር:: ኢየሱስም አልሞተም አልተሰቀለም ብሎም እንደዛሬ ሙሰሊሞች ያሰተምር ነበር:: ሰይጣን የሙሴና የነብያት አምላክ የሆነው እግዚአብሔር ነው በማለትም ያሰተምር ነበር:: ሰውም ነጻ ፍቃድ የሌለው ፍጡር ነው ሚለው ትምህርቱም አንዱ የትምህረቱ ማእክል ነው:: ከአንዳንዶች ለፍጽምና ትንሽ ሲቀራቸው ከተወለዱት በቀር ሰው ፍጹም ተበክሏል ሚለው ካልቪናዊ ትምህረቱም የሜኔቅ መሰረታዊ ትምህርት ነው:: ራሱንም አጽናኙ እኔ ነኝ ይል ነበር:: ከማኒ ትምህርቶች eሰጥ አትክልት ተመጋቢነት: ትዳር: ልጆችን መውለድ ሃጢያት ነው ይላል:: ቤተ ክርስቲያን የሜኔን ትምህርት ከሰማች በኋላ መናፍቅ መሆኑን በግልጽ አወገዘች:: የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የሆነውን የሰውን ነጻ ፍቃድ መካዱ ከዋና ዋና ሜኔን ካሰወገዙ ክህደቶች ውሰጥ ነበሩ:: የቤተክርሰቲያን አባት የሆነው ቅዱሰ አርቄሎሰ

“የቤ ክርሰቲያን ፈራጆች ክሜኔኔሰ በተቃራኒ በመቆም ሰው ነጻ ፍቃድ ያለው መሆኑን: ማኒ ሃጢያት የሚሰራ ሰለሆነ ከእግዚአብሔር የወጣ አለመሆኑን መንፈሱም ከእግዚአብሔር የወጣ አለመሆኑን: ሰይጣንም ሆነ መላዕክት የእግዚአብሔር ክፍሎች አለመሆናቸውን ወሰነዋል” (ARCHELAUS 33) በማለት የቤተ ክርሰቲያንን ውሳኔ ዘግቧል:: ዞሮሰቶሪያኖች እሰከሚያሳድዱት ድረሰ ሜኔ መልእክቱን በ ፐርሺያ በሙሉ ያሰተላልፍ ነበር:: ሜኔ በመጨረሻም ቴeዞ በእሰር ቤት በ 277 ሞቷል:: ሜኔ ከሞተም በኋላ መልእክቱ እሰከሮም ድረሰ ተሰፋፋ::

7. የሂጶው አውግጢን

አውግሰጢን እጅግ የምወደውና የማከብረው አባት ነው: ለተመሰጦ የሱን “ኑዛዜ” የተሰኘ መጽሐፍ ዋነኛ ተጠቃሚ ነኝ:: ሰማየ ሰማያትን ያዘልቀኛል: የኔን ባዶነት የልኡል አምላክነት ታላቅነት ያሰታውሰኛል: ትእቢቴን ያሰተነፍሰዋል:ተራነቴን ያሳየኛል:: እንዴት እኔን ትንሹን ወደደኝ በየ እሰክጤeቅ ድረሰ የልኡልን ታላቅነት የኔን ባዶነት ነገር ግን ሌኔ ያለውን ፍቅር ፍንትው ያደርግልኛል:: ሂወቴን በሙሉ የዳሰሰ እሰኪመሰለኝ ድረሰ ማንነቴን ያሰጎበኘኛል:: ድንቅ ነው:: ግን ከልኡል በቀር ፍጹም ማን አለና? ከሴት የተወለደ የማይበድል የለም::

በህዳር 20 347 ኢ.ም አንድ ህጻን ተወለደ: አውግሰጢን የተባለ:: በእድገቱ ሁሉ እግዚአብሔርን የማይወድና ዱርየ የነበረ ሰው ነበር:: ነገር ግን ሃጢያት ሰለሰለቸው ወደ መንፈሳዊ አለም በመግባት ነፍሱን ያሳርፍ ዘንድ ወደደ:: ብዙ መጻህፍትንም ካጠና በሁዋላ ሜኔቃውያንን ተቀላቀለ:: በሜኔቃውያን እምነት ለ9 አመታት በታማኝነት እያገለገለ ዘለቀ:: ነገር ግን የግኖሰቲክ ሜኔቃውያን እምነት ሊያረካው ሰላልቻለ አውግሰጢን ወደትክክለኛው ክርሰትና ተመለሰ:: በኋላም “የእግዚአብሔር ከተማ” እና እጅግ ምወድለትንና ሰማያትን ሚያሰነካኝን “ኑዛዜ” የተባለውን መጽሐፍ ጻፈ:: እነዚህ መጻህፍት ወደ ክርሰቶሰ ያደረገውን አሰቸጋሪ ጉዞ የመሰከረባቸው መጻህፍቶቹ ናቸው:: በነዚህ መጻህፍቱም ሰለሰው ነጻ ፍቃደና ሰለ ቅዱሳት መጻህፍት ያለውን ጽኑ እምነት ተናግሯል:: ሁሉንም የቫለንቲናውያንና የሜኔቃውያንን እምነት እንደማይቀበልም አሰፍሯል:: ብክርሰትና ቆይታው እጅግ ተወዳጅ ይቤተ ክርሰቲያን ፈላሰፋና አቃቤ እምነት በመሆን ለመናፍቃን የራሰ ምታት እየሆነ መጣ::

8. ፔላጊየሰ

 ልክ በአውግስቲን ዘመንም አንድ ጴላጊየስየተባለ ታላቅ መምህር በእንግሊዝ አገር የክርስትና አስተማሪ ሁኖ ያስተምር ነበር:: ጴላጊየስ በብሪቴን ሁሉ እየዞረ ቅዱሳት መጻህፈትን ያስተምር ነበር:: ከዛም ወደ ሮም በማቅናት ትምህርቶቹን ማሰራጨት ጀመረ:: ጴላጊየስ የአዳም ሃጢያት ለልጆቹ መጥፎ ምሳሌ ከመሆኑና የኢየሱስመ ሞትና ትምህርተ ሃጢያትን ለመጥላት ምሳሌ ከመሆን ያለፈ ተግባር የለውም ሰው ፍጹም ሁኖ መኖር ይችላል በማለት ያስተምር ነበር:: ይህ ትምህርትም ከባሲሊዳውያን ግኖስቲኮች የተለ አልነበረም::

 አውግስጢን የፕላጊየስን ትምህረት ሲሰማና እጅግ እየተሰፋፋ መሆኑን ሲመለከት: ትምህርቶቹን መቃወም ጀመረ:: አውግስጢን በጵላጊየስ ላይ ያተረፈው ትንሽ ድል ብቻ መሆኑን ሲመለከት ቫሊቲያውያን ግኖስቲኮች በባሲሊዳውያን ግኖስቲኮች ዘንድ እንዴት ድልን እንደተጎናጸፋ ለመመልከት ታሪክን ወደኋላ በማጠንጠን ማጥናት ጀመረ:: በዚህም ቫለነቲያውያን በ ቅድመ ውሳኔ ትምህርት ላይ በማተኮር እንዳሸነፏቸው ተረዳ:: የቫለነቲያውያን ትምህርት ከመንፈስ ከአምላክ(ሶፊያ)  የተወለዱ ሊጠፉ አይችሉም በሚለው ትምህረት ላይ ተመሰርተው እንዳሸነፏቸው ተረዳ፤ ነገር ግን ይህ ከክርስትና ትምህርት ጋ የማይጣጣም ትምህርት መሆኑን ሲረዳ: የተወሰነ ማሻሻያ በማድረግ: ለመዳን የእግዚአብሔር ቅድመ ውሳኔ ብቻ ነው ሚያስፈልገው ሰውለመዳን ምንም ሚጠበቅበት ነገር የለም በእግዚአብሔር ምክንያተ ቢሰ ምርጫ ብቻ ነው፤ በሚለው እሱ ራሱ ቀድሞ ሜኔቃውያንን ሲቃወም ያወገዘውን የሰውን ነጻ ፍቃድና የቤተ ክርስቲያንን ትምህረት አፍርሶ ተነሳ:: ለዚህም ምክንያቱ ሰው ሙሉ ለሙሉ ሰለተበከለ ነው በሚል ለፔላጊየስ መልስ ለመስጠት ሲል ብቻ ስህተት ውስጠ ገባ::

9 የቤተ ክርስቲያን ውሳኔ:

ቤተ ክርስቲያን በጴላጊየስና በአውግስጢን መካከል ያለውን እሰጣ ገባ ከተመለከተች በኋላ: በኤፌሶን ጉባኤ አዝጋጅታ ሁለቱም እንዲሟገቱ መድረክ አመቻቸችላቸው:: ቤተ ክርስቲያን የሁለቱን የሙግት ነጥብ ካየች በኋላ ሁለቱም ስህተት መሆናቸውን አወጀች::

 በውሳኔዋም “ፔላጊየስ ስህተቱ ሰው በራሱ ጥረት መዳን ይችላል አዳኝ አያስፈልገውም ማለቱ ሲሆን: አውግስጢን ደግሞ ስህተቱ ቅዱሳት መጻህፍት ያስተማሩትን እና አባቶች የተሟገቱለትን እግዚአብሔር የማዳን ጸጋውን ለሰ ሲሰጥ የመቀበልም ሆነ ያለመቀበል ነጻ ፍቃድ አለው ሚለውን ታሪካዊና ቅዱሳት መጻህፍታዊ ትምህርት በመካዱ: እንዲሁም ደህንነት ከሟለዳችን በፊት የተሰጠን ነው በማንኛውም ሃጢያት ውሰጥ ብናልፍ አናጣውም በማለቱ” መሆኑን አወጀች::

 ከኤፌሶን ጉባ እስራ ምእት አመታት በኋላ የሮማ ካቶሊክ በአውሮጳና በ ኤዢያ ሃይሏ የፈረጠመበት ና አዛዥ ናዛዥ የሆነችበት ጊዜ ነበር:: እሰቀድሞ ግን የምስራቅ አብያተ ክርስቲያናት በዚህ የሮማ ቤተ ክርስቲያን ሁሉን አውቃለሁ እልስትም ባይነቷ ምክንያት ተለይታታለች:: የሮማ ካቶሊክ ሃይሏን ለማጽናት ስተል የማእቀብ ስርአት ነደፋ ነበር:: ቤተ ክርስቲያኒቱ አንድን ነገር ካልወደደች በፍጥነት ንጉስ ነገስቱ የማሰቆም ሃላፊነት ጭናበትም ነበር:: ንጉሱ ይህን ካላደረገ ጳጳሱ ህዝቡን ለንጉሱ እንዳይታዘዙ ያወግዛል:: በፍጥነትም ህዝቡ ንጉሱን ያገለዋል:: ህዝቡ በጳጳሳቱ ውግዘት ውስጥ የሞተ ሰው ወደ ሲኦል እንደሚገባም ያምን ስለነበር ጳጳሱን ከንጉስ በላይ ይታዘዛል:: ስለዚህም ህዝቡ ንጉሱን ገድለው ሌላ በጳጳሱ ፍቃድ የተቀባ ንጉስ ይሾማሉ:: በተመሳሳይም ህዝቡ ለጳጳሱን ለንጉስ በሚከፍሉት የተጋነነ እስራት በኩራት እና ግብር እጅግ ተማረው ነበር::ነገር ግን ከዛ በላይ ጳጳሱ ወደ ገሃነም እንዳይልካቸው በመፍራት ዝምታን መረጡ::

10, ጆን ካልቪን

ካልቪኒዝም ምንድን ነው ሚለውን ከማየታችን በፊት የካልቪቨዝም መሰራቹን የጆን ካልቪንን ታሪክ በምጠኑ እንይና ወድ ትመህርታቸው ከዛም ወደ ግምገማው ከዛም ከመጸሕፍ ቅዱስ በሚያነሷቸው ጥቅሶች ላይ መልስና አጸፋው እናልፋለን::

 ጆን ካልቪን በ ሐመሌ 10 1509(ምጠቀምባቸው ካሌንደሮች የአውሮጳውያን ናቸው) በፈርንሳይ ኖዮን በተባለች ሰፍራ ተወለደ:: እደሜው 14 ሲሆን ወደ ፈርንሳይ በመጓዝ የጥንታዊ ፍልሰፍናዊ መዛብብትን

አጠና፤ ካልቪን በሙግት ቸሎታው እጅግ የተካነ ነበር በዚህ የተነሳም አባቱ በ19 አመቱ ጥብቅና እንዲያጠና አባቱ ወደ ኦርሊያነስ ዩንቨርስቲ ላከው:: በ 1531 አባቱ ሲሞት ካልቪን ወድ ፍርንሳይ በመመለስ እብራይሰጥና የጥንት ምዛግብት ጥናት ጀመረ:: በዚህ ጊዜ ነበር ካልቪን ወድ ተሐድሶ ልቡ እንደሸፈተ ሚነገርለት:: እሱ "ድንገኛ ለውጥ" በሎ ከገለጸው ጊዜ በኋላ ካልቪን ተሐድሶን በሙሉ ሃይሉ ማራመድ ጀመረ:: ከ1529-1534 ድረስ ካልቪን በፓሪስ ቀንደኛ የተሐድሶ ሰባኪ ሆነ:: ነገር ግን የፈረንሳዩ መንግስት ይህን የሚታገስ ሁኖ አላገኘውምና ጆን ከገዥወቹ በትር ለማምለጥ ከሃገር ሃግር ለመሰደድ ግድ ሆነበት:: ከብዙ መንከራተት በኋላም ወጣቱ ጆን በሰዊዘርላንድ መንግስት ቦታ ተሰጦት እፎይታን አገኘ:: በዚህም ሰፍራ በመሆን በካለቪናውያን ዘንድ ትልቅ ክብር ያለውንና እንዳንዴም እንደምጸሐፍ ቅዱስ ሚጠቅሱትን "Institutes of the Christian Religion." የተባለውን የመጀምሪያውን ቅጅ የጨረሰው:: ካልቪን የመጀመሪያውን ቅጀ ሲጽፍ የተበራራ የተሐድሶ እምንት አቋምን በቻ ያሰበ ቢሆንም በኋላ ላይ እጅግ አሰፍቶታል::

ካልቪን በተሐድሷዊው መምህር ጌይለም ፋሬል(1489-1565) ጋባዥነት ወደ ወቧ ከተማ ጄኔቫ አቀና: በዛም ትምህርቱ ተቀባይነት አገኘ ካልቪንም ቷዳጅነትን በማገኘቱ የቤተክርስቲያን መሪ እንዲሆን ተመረጠ:: በጄኔቫም ሳለ ባለ 21 አንቀጽ የተሐደሶ የእምነት አቁዋም ኑዛዜ አዘጋጅ ይህንንም እያንዳንዱ ዜጋ ቃል በመግባት እንዲቀበለው ግዴታ አሰደረገ:: በ 1542 የመጅመሪያውን መሰረተ እምነት ጻፈ፤ እሱም ለበዙ ተሐድሷዊ አቢያተ ክርሰትያናት የእምነት መገምገሚያ ሁኖ ያገለግላል::

የጆን ጠንካራ የእምነት አቋምና መርሆ ሰነ ምግባር በወንደሞች መካከል እጀግ የሰፋ መከፋፈልን ማምጣቱ አልቀረም:: ይህ መከፋፈል ከካቶሊክ ወንድሞች ጋር በቻ ሳይሆን ከተለያዩ የተሐድሶ መምህራንን የሰነ መለኮት ምሁራንም ጨምር ነበር:: ለምሳሌ በጌታ ራት ዙሪያ ከማርቲን ሉተር ጋር የነበረው ልዩነት ወንደሞችን ሉተራን እና ተሐድሱአውያን በሚል ከፈለ: ሌላው በካልቪን ታሪክ ላይ ጠባሳ አሻራ ጥሎ ያለፈው የታሪክ ገጠመኝ ደግሞ በግጻዌ መለኮት ላይ ከካልቪን ጋር በመለያየቱ በቻ ሰፔናዊወን ሰነ መለኮታዊ በ 1553 ሚካኤል ሰርቬቱሰ ተቃጥሎ እንዲገደል ማድረጉ ነው:: የካልቪን አቋማዊነት በራሱ ተከታዮች ዘንድ እንኩዋ መከፋፈል አምጠቱዋል::

በአጭሩ

ካልቪን የሮም ቤተ ክርቲያንን ሚያዳክምበትን መንገድ የጥብቅና እውቀቱን በመጠቀም ማንሰላሰል ጀመረ:: የአውግሰጢንን መጻህፍት እሰኪያጠና ድረሰ ግን ምንም አይነት ሃሳብ ሊመጣለት አልቻለም:: የአውግሰጢንን ትምህርት ካጠና በኋላ: ለመቀበል አዳጋች የሆኑትን የግኖሰቲክ አመለካከት ያላቸውን የሜኔቃውያንና የቫለነቲናውያንን አመለካከት ከአውግሰጢን አሻሽሎ የቅድመ ውሳኔን ትምህርት ለህዝቡ ቢያሰተምር የሮምን ቤተ ክርሰቲያን እጅጉን ሊያዳክማት እንደሚችል ተረዳ:: ምክንያቱም እግዚአብሔር አሰቀድሞ የሚጸድቁትነና ወደ ገሃነም ሚጣሉትን ከወሰነ ጳጳሱ ወደገሃነም ሊጥል እንደማይችል ህዝቡ ይገነዘባልና:: መክንያቱም አሰቀድሞ የተወሰነ ከሆነ ጳጳሱ ሊለውጠው የሚችለው ነገር ሊኖር እንደማይችለ ይረዳሉና:: ከዛም ካልቪን የመጀመሪያወ መጽሀፉ የሆነውን "የክርሰትና ሃይማኖት ተቁአም"( INSTITUTION OF CHRISTIAN RELIGION) ሚለውን መጽሐፉን አሳተመ:: በዚህም የፕሮቴሰታንታዊ ተሐድሶን ሃይማኖት እጅጉ ሰፋ:: ብዙ ህዝብም የሮምን ቤተ ክርሰቲያን እየተወ ወጣ::

የግኖሰቲካውያንን ትምህርት ቅድመ ውሳኔን በቤተ ክርሰቲያን ዘውግ በማቅረብ ና የቤተ ክርሰቲያንን ታሪካዊና ቅዱሳት መጻህፍታዊ መልእክትም በመካድ ካልቪን የተሳካለት ሰው ነበር:: እነዚህን ትምህረቶችም ከቅዱሳት መጻህፍት ሚመሰሉለትን በመፈለግ እና ቆራርጦ በማቅረብ ካልቪን የፈለገውን ጶለቲካዊ ገብ ለማሳካት ቻለ::

11. ጥንታውያን አበው ለዚህ አመለካከት ምን አይነት ምላሽ ሰጥተው ነበር?

ከካልቪንና ከአውግሰጢን በፊት የቅደመ ውሳኔንና: የምክንያተ ቢሰ ምርጫን አመለካከት: በቤተ ክርሰቲያን ውሰጥ አሰረገው ሊያሰገቡ በብዙ የሞከሩ የቤተ ክርሰቲያን ግሪሳወች ግኖሰቲካውያን መሆናቸውን የቤተ ክርሰቲያን ታሪክ ያሳየናል:: አባቶች እንዲ ያለ ትምህርት ሲገባ ግን ቤት ለእግዜር በለው አኀንበሰው ሳይሆን

የተቀበሉት ለቤተ ክርስቲያን በመቆርቆር አስቀድሞ ውሳኔ ሚባልን አስተምህሮ ደም እስከማፍሰስ ተዋግተውት በኤፌሶን ጉባኤም አውግዘውት አለፈዋል::

ግኖስቲኮች አስቀድሞ ለገሃነም የተወሰኑትን ሰዎች ልብ እግዚአብሔር ደፍኗል በማለት 2ኛ ቆሮ 4:3 ላይ “ወንጌላችን የተከደ ቢሆን እንኳ ለሚጠፉት ነው” ሚለውን ይጠቅሱ ነበር ለዚህም ቅዱስ ኢራኒየስ “እግዚአብሔር ሃሳባቸውን ያሳወረው ላለማመን የመረጡትን ብቻ ነው: ላለማመን ራሳቸው መርጠዋልና: በሮሜ ላይ እግዚአብሔርን ለማወቅ ያልወደዱትን እነርሱን ለማይገባ አምሮ ሰጣቸው ይላልና: በሁለተኛም ተሰሎንቄ 2:9-10 “ይድኑ ዘንድ ያeውነትን ፍቅር ሰላልተቀበሉ ለሚጠፉት: ያeርሱ መምጣት በተአምራትና በድንቆች በአመጸም መታለል ሁሉ እንድሴeጣን አሰራር ነው” እንደሚል ለማመን ያለፈለጉ ሰህተትን እንዲያምኑ የሰህትት አሰራር የላክባቸዋል:: እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ በመሆኑ አስቀድሞ የማያምኑትን ቁጠራችውን እንኳ ያወቃል:: ሰለዚህም ላለማመን አሳልፎ ሰጣቸው::”
(መናፍቃን 4:29)

“ሰው መለካምነና ከፋን ለመለየት አቅሙ አለው:: አቅሙም በነጻ ፍቀዱ የተነሳ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ያሰችለዋል:: ይህም በ ሮሜ 2 የተብራራ ነው እግዚአብሔር ማንንም እንዲድን አያሰገድድም: ሰለዚህም የተታለሉም በራሳቸው ነው: እግዚአብሔር ራሳቸውን እንዲያሳውሩ ፈቅዶላቸዋልና::
(መናፍቃን 4:39)

“ጽድቅን በነጻነት ለመምረጥ ለሰው የተሰጠ ችሎታ ነው:: እውነተኛ እምነትም ንሰሃን ይወልዳል” (ቅዱስ ቀለሜንጦስ ዘ አሌክሳንደሪያ: ሰቶርማታ 2:4)

“ጳውሎስ በሮሜ 3:10-18 ሚጠቅሳቸው ራሳቸውን ያሳወሩትን አይሁድና አህዛባ ነው እንጅ ማንም በዚህ ሁኔታ ኤይወለድም” (መናፍቃን 1:19)

“እግዚአብሔር ሰውን ከመጀመሪያው ነጻ ልኡክ አድርጎ ነው የፈጠረው: ይህ ከጥንት የነበረት የሰው ነጻነት ነው: በእግዚአብሔር ዘንድ ማሰገደድ የለምና:: በሰውና በመላእክት ዘንድ የመምረጥን ሃይል አነሯል:: የግኖሰቲካውያን እንዳንዱ ለመጥፎው እንዳንዱ ለመልካም ተፈጥረዋል ሚለው ሰህተት ነው:: ማንም ወንጌልን ለመቃወን ነጻነት አለው: ልክ እግዚአብሔር ነጻ ፍቃድ እንዳለው ሁሉ እኛም አለን:: በእርሱ አምሳል ተፈጥረናልና:: እግዚአብሔርን የሰውን ምርጫ ነጻ አድርጎታል: በእርሱ ቁጥጥር የምንህንውና ወደ ፍጽምና ምንመጣው በትንሳኤ ነው::” (መናፍቃን 4:37)

ከቤተ ክርሰቲያን ታሪክ እንደምንረዳው: የአሰቀደሞ ውሳኔ ጀማሪወች ግኖሰቲካውያን ሲሆኑ: የቤተ ክርሰቲያን አባቶችም በጥብቅ ተቃውመውታል:: በጉባኤም አውግዘውታል:: ነገር ግን ይህ ግሪሳ አሰተምህሮ ከቤተ ክርቲያን ውልደት ጀምሮ በበቀለችበት እየበቀለ: በሄደችበት እየሄደ: በአውግሰጢን እልህ ወደ ቤተ ክርሰቲያን ተመልሶ ዘፋን ሲይዝ ቤተ ክርሰቲያን ብታሰወጣውም በ ካልቪን ፖለቲካዊ አላማ ተመልሶ በቤተ ክርሰቲያን ዘፋኑን በመቆጣጠር ዛሬ ድረሰ በኢትዮጴአ ቤተ ክርሰቲያን ቲኦሎጆወች ሳይቀር በመግባት ቤተ ክርሰቲያንን ረፈት ነሰቷታል:: ዛሬም ድረሰ ቤተ ክርሰቲያንን እንዳታድግ ማነቆ ሁኖ አሰሮ አላሰተነፍስ ብሎ የአይን ሞራ: የጉሮሮረ ሳንካ: የሳንባ ኮሮና: የእግር እንቅፋት ሁኖ ተለጥፎ እንደ መዥገር ደሟን እየመጠመጠ አለ:: ይህንን ለመታገል ደግሞ የቤተ ክርሰቲያን ለጆች እጅ ለእጅ መያያዝ የአባቶቻችን ለጆች መሆን ይጠበቅብናል::

የእምነት አቋማቱ::

ካልቪናውያን አምሰት TULIP(አበባ) ብለው ሚጠሩዋቸው የእምነት አቁዋማት አሏቸው:: እያንዳንዱ ፊደል የሚቆሙላቸው ቃላት አሏቸው: T=Total hereditary depravity.(ጠቅላላ የዘር ብክለት) U=unconditional election.(ሁኔታ ቢሰ ምርጫ) L=limited atonement.(ውሰን ቤዘወት) I= Irresistible grace(የማይገረሰሰ ጸጋ) P=perseverance of saints.(የቀዱሳን ዘላለማዊ ጸደቅ)።

እነዚህን አቋዋማት አንድ በአንደe ለማየት እንሞክራለን::

1. Total Hereditary Depravity. (ጠቅላላ የዘር ብክለት)

ይህኛውን አስተምህሮ አበዛኛወቹ ቤተ እምነቶች የኔዋን ሙሉወንጌለና ኦርቶዶክስን ጨምሮ ሚያስተምሩት ካልቪናዊ ትምህርት ነው:: በሃገራችን የዚህ ትምህርት ሚታወቅበት ዋና የዳቦ ስሙ "የውርስ ሃጢያት" የባላል:: ኦርቶዶክስ እንዳውም ይህን ትምህርት የክርስቶስን ቢeዛት ዋጋቢስ ለማድረግ ትጠቀምበታለች::(ኢየሱስ የሞተው ለውርስ ሃጢያት በቻ ነው እንዲሉ)::

ካልቪን ይህን ትምህርት ሲያስተምር ሶስት ነገሮች ላይ አስምሯል:

1. "ግለሰቦች ተበክለዋል፤ ተጠመደዋል፤ የሃጢያት ተጤአቂ ናቸው::
2. "አጠቃላይ በጠቅላላ ተበክለዋል፤ ከውስጣቸው ምንም በጎ የለም"
3. "የሃጢያት ሁኔታቸው ብክለታቸው በውስጣቸው ያለው ሁሉ በዘር የተላለፈ ነው:: ከወላጆቻቸው ወደ እነሱ መጥቷል::"

የዌስት ሚኒስተር ኑዛዜ:-

"አዳም እና ሔዋን የሰው ዘር ስር ስለሆኑ ሃጢያተኝነት ገባ ሞትና የተፈጥሮ ብክለትም ከዘር ዝር በትውልድ ሁሉ ወደዘሮቻቸው ሁሉ ተላለፈ:: በዚህ የቀደም በክለት የተነሳ ታመምን፤ ተጎዳን፤ የበጎ ሁሉ ተቃራኒ ተደረግን ለክፋት ሁሉ ተሳብን፤ ከህጉ ውጭየሆነውን ሁሉ አደረግን"

የፊሎፊዲያ የእምነት አቋዋም:-

"የመጀምሪያወቹ አባቶቻችን በሃጢያት ከመጀምሪያው ጸድቅና ከእግዚአብሔር ሕብረት ወደቁ: እኛም በነሱ ወስጥ ነበርን በዚህም ሞት ወደ ሁሉም መጣ፤ በሃጢያት ሁሉም ሙት ሆነ:: በጥቅላላ ማንነታችን ረከሰ የነፍስና የስጋችን ሁሉ" (ገጸ 24)

የአውግስበርግ የእምነት አቋዋም::

"ከአዳም ወድቀት ጀምሮ ሰው ሁሉ በሓጢያት ይወለዳል ያም ፈሪሐ እግዚአበሒየር አለመኖር ነው: እናም ይህ በሽታ ወይም ወንጀል መሰረት በእውነቱ ሃጢያት ነው አሁን እንኩዋ ዳግም ባልተወለዱት ላይ የዘላለምን ፍዳ እና ሞት እያመጣባቸው ነው::"

ጆን ዊስሊ:

"ገና መለካምና ክፉን ሳንለይ ተፈርዶበናል:: ምን እንደሆነ ሳናወቅ ጀምረን በእርግማን ስር ነበርን"

" (ትምህርተ የውርስ ሃጢያት ገጽ 340)

መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

መጸሐፍ ቅዱስ ሰው ያለሃጢያት እንደሚወለድና በተለያዩ የሂውት ልምምዶች ከቤተሰቡ ከማህበረሰቡ ነገሮችን እንደሚማርና በለቡ እንደሚቀመጡ የናገራል: በዚህም በተደጋጋሚ ከሌላው መንማርባቸውን የሰውነት ከፍሎቻችንን እንድንጠብቅ ያሳስበናል::

በዘጸ 32:31-33

"ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ፦ ወዮ! እኒህ ሕዝብ ታላቅ ኃጢአት ሠርተዋል፥ ለራሳቸውም

የወርቅ አማልክት አድርገዋል፤ አሁን ይህን ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው፤ ያለዚያ ግን ከጻፍኸው መጽሐፍህ እባክህ ደምስሰኝ አለ። እግዚአብሔርም ሙሴን፦ የበደለኝን እርሱን ከመጽሐፌ እደመስሰዋለሁ።”

በዚህ ክፍል ላይ ሙሴ በህዝቡ ሃጢያት እሱን እንዲገድለው እና ህዝቡ እንዲደኑ ይለምነዋል፤ እግዚአብሄር ግን ሃጢያትን የሰራውን ራሱን እንደሚያጠፋ ይነግረዋል::

ዘዳግም 1:34-39

“እግዚአብሔርም የቃላችሁን ድምፅ ሰምቶ ተቆጣ። ለአባቶቻችሁ እሰጣት ዘንድ የማልሁላቸውን መልካሚቱን ምድር ከእነዚህ ሰዎች ከዚህ ክፉ ትውልድ ማንም አያይም፥ ከዮፎኒ ልጅ ከካሌብ በቀር እርሱ ግን ያያታል እግዚአብሔርን ፈጽሞ ተከትሎአልና የረገጣትን ምድር ለእርሱ ለልጆቹም እሰጣለሁ ብሎ ማለ። እግዚአብሔርም ደግሞ በእናንተ ምክንያት በእኔ ተቆጣእንዲህም አለ፦ አንተ ደግሞ ወደዚያ አትገባም በፊትህ የሚቆም የነዌ ልጅ ኢያሱ እርሱ ወደዚያ ይገባል እርሱ ለእስራኤል ምድሪቱን ያወርሳልና አደፋፍረው። ደግሞ። ለምርኮ ይሆናሉ ያላችኋቸው ሕፃናቶቻችሁ፥ ዛሬም መልካሙን ከክፉ መለየት የማይችሉ ልጆቻችሁ፥ እነርሱ ወደዚያ ይገባሉ፥ ምድሪቱንም ለእነርሱ እሰጣለሁ ይወርሱአታልም።”

እግዚአበሔር እስራኤላውያን በሃጢያታቸው ወደ ተሰፋይቱ ምድር እንደማይገቡ ነገር ግን ለጆቻቸው እንደሚገቡ ይናገራል፤ ይህ ሚያሳየን ሃጢያት በራስ እንጅ በዘሩ ላይ እንደማይቆጠር አመላካች ነው:: ሃጢያታቸው በልጆቻቸው የሚቆጠር ቢሆን እውነትም እነዚህ “መልካምና ክፉን የማያውቁ” ብሎ እግዚአበሔር ባልጠራቸው ነበር በአባቶቻቸው. በመጣው ሃጢያት ከፋን አውቀዋልና ክፍጥረታቸውም የቁጣ ለጆች ነበሩና ሂወትንም ባላዩ ነበር::

መክብብ 7:29

“እግዚአብሔር ሰዎችን ቅኖች አድርጎ እንደ ሠራቸው፥ እነሆ፥ ይህን ብቻ አገኘሁ፤ እነርሱ ግን ብዙ ብልሃትን ፈለጉ።”

እግዚአበሔር ሰውን ቅን አድርጎ እንደፈጠረው ሰው ግን ክጥረቱም ቅንነት ያለበት እንዳደረገው ነገር ግን ወደሃጢያት ያዘነበሉት በገዛ ፈቃዳቸው ብልሃትን በመፈለግ የተነሳ ቅዱስ ቃሉ እየተናገረ፤ የቃሉን ባለቤት መናቅ ብሎም ከእርሱ ማመጽ ካለሆን “እግዚአብሔር ሰወችን ሃጢያተኛ አድርጎ ሰራቸው ማለት” ፈጽሞ ትእቢት ነው ወይ ደግሞ ያህዌ አምላክ ሰወችን አለፈጠረም ብሎ ፈጣሪነቱነ መካድ ነው::

ማቴወስ 18:1-5

“በዚያች ሰዓት ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ ቀርበው፦ በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ የሚበልጥ ማን ይሆን? አሉ ሕፃንም ጠርቶ በመካከላቸው አቆመ እንዲህም አለ፦ እውነት እላችኋለሁ፥ ካልተመለሳችሁ እንደ ሕፃናትም ካልሆናችሁ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም። እንግዲህ እንደዚህ ሕፃን ራሱን የሚያዋርድ ሁሉ፥ በመንግሥተ ሰማያት የሚበልጥ እርሱ ነው። እንደዚህም ያለውን አንድ ሕፃን በስሜ የሚቀበል ሁሉ እኔን ይቀበላል፤ “

ጌታችን ኢየሱስ በግልጽ ቃል እንደዚህ ህጻን ያለ ነው መንግስተ ሰማይ ሚገባ ካለ ያ ህጻን ንጹህ ነው ማለት ነው ለመንግስቱም በቂ ነው: ለዚህ ያደረሰው ምን ነው ብለን ብንጠይቅ የነፍሱ ንጽህና ነው: ይህ ሀጻን ትዕቢት አያውቅም የትእቢትን ሃጢያት አልተማረምና::

ሮሜ 7:9-11

“እኔም ዱሮ ያለ ሕግ ሕያው ነበርሁ፤ ትእዛዝ በመጣች ጊዜ ግን ኃጢአት ሕያው ሆነ እኔም ሞትሁ”

ሐዋርያው ጳውሎስ ሃጢያት የሚመጣው በህግ የተነሳ መሆኑን በሮሜ 5 በደንብ ያብራራል:: እንግዲህ መጠየቅ ያለብን የአዳም ልጆች ወይንም እኛ ህጉ ተሰጦናል ወይ ህጻናትንስ ህግ ይገዛቸዋል ወይ ብለን ብንጠይቅ ማንም አመክኔዐታዊ ሰው መልሱ ሊሆን የሚችለው "አረ በጭራሽ ነው:: ታዲያ ያለ ህግ ሃጢያት የለም ያለንን አምላካችንን እግዚአበሔርን፤ የለም በልጅነታችንም ሃጢያት ሳንሰራ ህግም ሳይሰጠን ሃጢያተኞች ነበርን፤ ሐዋርያወም ተሳስቶ እንጅ መልካምና ከፉን አውቆ ህግን ከመቀበሉ በፊት ሃጢያተኛ ነበረ ከማለት በላይ ምን ኢክርስቲያናዊነት ይኖር ይሆን?

1 ቆሮ 14:20

"ወንድሞች ሆይ፥ በአእምሮ ሕፃናት አትሁኑ፤ ለክፋት ነገር ሕፃናት ሁኑ እንጂ በአእምሮ የበሰሉ ሁኑ።" ሐዋርያው በዚህ ከፍሉ ላይ በአእምሮ እንድህጻናት ሁኑ ያለው ለክፋት ነገር ነው ይህ ሚያሳየን ሐዋርያው ፈጸሞ የውርሰ ሐጢያት አመለካከት እንደሌለው ነው ይህ ጸሁፍ ትኩረቱ ለማንኛውም አንባቢ በመሆኑ እንጅ የውርሰ ሃጢያት አማነኞችን ጠለቅ በለን ሰናያቸው "ሰው ፈጽሞ ጥሩ መሆን አይችልም ምክንያቱም ሰው መልካም ለመሆን ሃጢያቱ ይገድበዋል" ብለው ያምናሉ ይህ ደግሞ ከሐዋርያው አመለካከት ፈጽሞ የተቃረነ ሁኖ እናገኘዋለን::

1 ዮሐ 3:4

"ሃጢያትን የሚያደርግ ሁሉ ዐመጽን ያደርጋ ል: ሃጢያትም ዐመፀ ነው"

ሐዋርያው ሃጢያትን ሲያሰረዳ ድርጊትና አመጽ መሆኑን በማያሻማ መንገድ ይገልጿአል የህም ድርጊት ነው በማለት ነው:: እንግዲህ ሀጻናት በዚህ ድርጊትና አመጽ የሌሉ መሆኑን አመክንዮታዊ አምሮ ሁሉ ይረዳዋል:: ድርጊቱ ውሰጥ የሌል በሃጢያት የለበትም ማለት ነው:: የአምላክ ቃል ይህን በግልጽ እያሰረዳን የለም ሃጢያት የሚወረሰ ነው ብሎ መሟገት አመጽ ነው አመጸም ሃጢያት ነው ሰለዚህ የውርሰ ሃጢያትን ማመን በራሱ ሃጢያተ ነው::

"የቀደሙ የቤተ ክርሰቲያን አባቶች በሰው ሃጢያትና ተፈጥሮ ላይ ምን ተናገሩ?"

በሰው የሃጢያት ተፈጥሮ ላይ እጅግ የምወደው የቤተ ክርሰቲያን እና የአውሮጳ ተሒድሶ አባት ቅዱሰ አውግሰጢን(የካልቪን አብዛኛው ትምህርቶች አመንጪ) ቢናገርም አልተሳሳተም ወደሚል ግን አልደርሰም: እርሱ ክ ፒላጊየሰ በተቃራኒ የግሪክ እውቀት ሰለሌለው እና ከሂወቱ ልምምዶች(ከወጣትነት የሴሰኝነት ሰሜት ክርሰቶሰን በማመኑ ነጻ መውጣት) ለዚህ ድምዳሜ መድረሱ ይነገርለታል: አብዛኛው ምሰራቃውያን የቤተ ክርሰቲያን አበውም በግሪከኛ ሰለ ጳፋ ፕላጊየሰ የነሱን በመውሰድ በጣም ለጥጦ እንዳሰተማረና በራሰ ሰራ መዳን እንደሚቻል ለማሰተማር እንደበቃና የእግዚአበሔርን ጸጋ እንዳላሰፈላጊ እንደተረዳ ይነገርለታል:: ይህ ማለት ግን ጥንታውያን አበው ሰለ ውርሰ ሃጢያት አሰተምረዋል ወደ ሚል ድምዳሜ እንድንደርሰ አያበረታታም:: የተወሰኑትን ለማቅረብ ልሞክር::

የሐዋርያው ዮሐንሰ ደቀ መዝሙር የአንጾቂያው ኤጲሰ ቆጶሰ ኢግናጢዮሰ(35-107)

"ሁለት አየነት ሰወ አለ ማለቴ አደለም ይልቁንም #ሁሉም ሰው አንድ ነው እንጅ፤ እንዳነዴ ለእግዚአበሔር እንዳንዴም ለሴeጣን ይሆናል፤ ሰውየው መንፈሳዊ ከሆነ ለእግዚአበሔር የተገባ፤ ኢ-ሃይማኖት ከሆነና ምንፈሳዊም ካልሆን ለሰይጣን ይሆናል ይህ ደግሞ #በተፈጥሮ_ሳይሆን በምራጫው ነው"(ወደ መግኒሳውያን የ ኢግናጢዮሰ መልእክት ም 5)

"በፊታችን ሂወት ለእግዚአበሔር በመታዘዝ እና ሞት ባለመታዘዝ ተቀምጦልናል እናም ሁሉም

#ወደመረጠው ወደዛ ይሄዳል ከሞት አምልጣችሁ ሂወትን ምረጡ" (ዝኒ ከማሁ)

ኢራኒየስ(120-202)

"ሰው ነጻ ፍቃድ ከመምረጥ ችሎታ ጋር ተችሮታል፤ ሰው በተፈጥሮው አንዱ ጥሩ ሌላው መጥፎ ነው ሚባለው ስህተት ነው።" (ተቃውሞ መናፍቃን መጸሐፍ 4)

"ሰው መልካምና መጥፎን ለመለየት ችሎታ የተሰጠው ነው፤ ስለዚህም ያለ ተጽእኖ እግዚአብሔርን መታዘዝ ይችላል" (ዝኒ ከማሁ XXXIX)

'እነዚህ በጎ ያላደረጉት ከእግዚአብሔር ፍርዳቸውን ያገኛሉ ምክንያቱም የማድረግ ችሎታው እያላቸው በጎውን አላደረጉምና።"(ዝኒ ከማሁ 37 የሰው ታሪክ)

ሰማእቱ ጀስቲን(110-165)

"ሰው ሃጢያትን እመቢ ማለት ባይችል ኑሮና ጸድቅን መምረጥ ባይችል ኑሮ ለስራቸው ተጠያቂ ባይሆኑም ነበር>>> መጥፎም ሀነ በጎ ለመሆን ቀደሞ ተወሰኖ ለትስ ቢሆን ኑሮ ሁለቱም ተቃራኒውን ለማድረግ ባልቻሉም ነበር።"(እቅበተ እምነት 1 ም 43)

"ሁሉም ሰው ሃጢያትም ሆነ በጎን ሚያደርገው በፍቃዱ ነው""(እቅበተ እምነት 2 ም 72

"ማንም ቢሆን የሚቀጣው በራሱ ሃጢያት ነው ጽድቁም ለራሱ ነው"(ዝኒ ከማሁ ም 160)

ቀለሜንጦስ ካልአይ(80-140)

"ሰንወለድ መጥፎም ጥሩም ሳንሆን ነው" (ቅጽ 8 ANTE NICEAN FATHERS P 273)

የአሌክሳንድርያው ቀለሜንጦሰ(150-225)

"ነፍሰ ሳትመርጥ ብትቀጣ ፍርዱ ልክ አደለም"

ጢጢያን ዘአሲሪያ(120-180)

"መጥፎ የሆነ ሁሉ(በተፈጥሮው) በእግዚአበሔር የተፈጠረ አደለም"

ቅዱሰ ላክታንቲየሰ(240-320)

"ማንም ሃጢያተኛ ሁኖ አልተወለደም"

ከቀድሞ አባቶች ሰው በተፈጥሮወ ከምንም ነጻ ሁኖ እንደተፈጠረ የተናገሩ ቢሆንም ብንዘረዝረው ቦታ አይበቃም ለፊሰቡክ ፕላትፎርምም ኤeሆንም።

"ካልቪናውያን ለጠቅላላ የዝር ብክለት ሚያቀርቧቸው ጥቅሶችና መልሶቻቸው።"

እንደማነኛውም የሰህተት አሰተማሪወች ሁሉ ካልቪናውያን ለሰህተት ትምህርታቸው እንዲያመቻቸው የሚጠቅሱዋቸው ጥቀሶች አሉዋቸው። ለነሱም በተቻለ መጠን መልሰ ለመሰጠት እንሞክራለን።

ዘፍ 6:5

“እግዚአብሔር አምላክ የሰው አመጽ በምድር ላይ የበዛና የልቡም አሳብ ዘወትር ወደክፋት ብቻ ያዘነበለ እንደሆነ ተመለከተ::”

ይህን ጥቅስ ከአወዱና ከክፍሉ ሃሳብ ነጥለን ያየነው እንደሆነ፤ የካልቪናውያንን ሃሳብ የሚደግፍ ሊመስለን ይችላል:: ነገር ግን አውዱን ስናየው ፈጽሞ ከካልቪናውያን ሃሳብ በበዙ ማይልስ የራቀና ሆድና ጀርባ መሆኑን ይልቁንም ሰው በፍቃዱ በሚሰራው ሃጢያት እንጂ የወረሰው ሃጢያት የሚቀጣ እንዳልሆነ እንረዳለን::

1.ኛ ካልቪናውያን የክፍሉን ጉልህ ገጸ ባህርይ ኖህን ይረሱታል፤ ኖህ ሰው አደለም ለማለት ተፈልጎ ካልሆነ በቀር በውርስ ሃጢያት ቢሆን ኑሮ የሰው ዝንባሌ ክፉ የሆነው ኖህ ራሱ ሰው ነውና ዝንባሌው እርሱም ፈጽሞ ክፉ ሊሆንና ሊጠፋ የገባው ነበር:: ነገር ግን የሰው ዝንባሌው ክፉ የሆነው ከራሱ ፈቃድ ነበርና ኖህ እግዚአብሔርን በምመረጥ አካሄዱንም ከእርሱጋ በማድረግ ደኗል::

2ኛ. ቀ 12 ላይ ስናይ “ሰው ሁሉ አካሄዱን አበላሽቶ ነበር” እንጅ የተባለው በወረሰው ሃጢያተ የተነሳ ነው ሚጠፋው ወይንም ሃጢያተ ሚሰራው አልተባለም:: ስለዚህ እያንዳንዳችን ምንጠየቀው በራሳችን አካሄድ እንጅ በአዳም አደለም:: በክፍሉም አዳም አልተወቀሰበትምና እኛ አምላክን እናወቅለሃለን ብለን ባንወቅሰው ባንወቅሰለትም የሻላል::

መዝ 51:1-5

“እነሆ በአመጻ ተጸነሰሁ እናቴም በሃጢያት ወለደችኝ”

በዚህም ምንም አይነት የውርሰ ሃጢያት አናገኝም፤ የዳዊት እናት ዳዊት ሲወለድ ወይም በምን እንደወለደቸው አናወቅም፤ እሱዋ በሃጢያት ወለደችው ማለት ዳዊት ሃጢያተኛ ነው ሚል ምንም አየነት አመክንዮታዊ መንገድ አይኖርም::

መዝ 53:1-3

“ሰነፍ በልቡ አምላክ የለም ይላል:: ረከሱ በበደላቸውም ጎሰቆሉ፤ በጎ ነገርን የሚያደርጋት የለም:: የሚያስተውል እግዚአብሔርንም የሚፈልግ ያይ ዘንድ እግዚአብሔር ከሰማይ የሰው ልጆችን ተመለከተ: ሁሉ በደሉ አብረውም ረከሱ አንድስ እንኳ በጎን የሚያደርጋት የለም”

በዚህ ክፍል የውርሰ ሃጢያትን ከሚያሳይ ይልቅ ነጻ ፍቃድን ሚያሳይ ክፍል ተብሎ ሊጠቀሰ የገባው ነበርኮ፤ እንዳንዴ ስንጠቅስ አይን ጥርስ አንልም ማለት ነው:: በዚህ ከፍል ሰወች ሰወች ስናያቸው የጎሰቆሉት በገዛ በደላቸው መሆኑን ነው ሚናገው፤ እግዚአብሔር ለዚህ ነው ተሰፋ በማድረግ ወደ ሰወች ያየው ፍቃድ ሰጧቸዋልና ይህን ፈቃዳቸውን ወደርሱ ያደርጉ እንደሆን::

መዝ 58:3

“ሓጥአን ከማህጸን ጀምረው ተለዩ: ከሆድም ጀምረው ሳቱ: ሐሰትንም ተናገሩ”

በመጀምሪያ ደረጃ ይህን ጥቅስ ለመረዳት መዝሙረ ዳዊት መን አይነት መጸሐፍ ነው ሚለውን መረዳት ያሰፈልጋል፤ ይሀ መጸሐፍ የጥባብና የቅኔ መጸሐፍ ነው፤ የጥበብና የቅኔ መጸሀፍት ደግሞ “ግነት” የተባለውን የቋንቋ ህግ ይጠቀማሉ(ቅኔን ቅኔ ከሚያሰኘው አንዱ):: ለምሳሌ “ሐሰትን ተናገሩ” ሲል ከማህጸን ውሰጥ ሁነው ሲያወሩና ሲዋሹ ፊቱ ላይ ድቅን ሚልበት ሰው አለ ይሆን? ስለዚህ የህ እንደግን ሚወሰድ አንቀጸ ሁኖ በዛላይ “ሳቱ” በማለት በራሳቸው ሰህተትን እንደፈጸሙት እንጅ እንዳልወረሱት ያሰረዳል::

ሮሜ 3:19

“እፍም ሁሉ ይዘጋ ዘንድ አለምም ሁሉ ከእግዚአበሔር ፍርድ በታች ይሆን ዘንድ ህግ የሚናገረው ሁሉ ከህግ በታች ላሉት እንዲናግር እናወቃለን”

ታዲያ ይህ ክፍል የቱጋ የሆነ ስለ ውርስ ሃጢያት ሚያወራው? የህ ክፍል ባጠቃላይ ሚያወራው እህዛብም ሆኑ አይሁድ ሃጢያት #እንደሰሩ እንጅ እንደወረሱ አደለም:: መሰራት ደግሞ የምርጫ ጉዳይ ዕንጅ የመውረስና ያለመውረስ ጉዳይ አደለም::

ሮሜ 5:12-21

በዚህም ክፍል አንድም ቦታ ላይ ሃጢያት ከአዳመ ይወረሳል ወይም የወረሰ አለ አይልም:: “ሞት በአንድ ሰው ወደ አለም ገባ” ሚለውም ከሆነ አዳም የሞት መግቢያ በር እንደሆነ እንጅ ለሌሎች ሞት ምክንያት እንደሆነ አይገልጽም የሌሎች ሞት ምክንያት ሲገልጽ “ሁሉ ሃጢያት #ሰላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ” ይላል፤ ሰለዚህም ሁሉ የሞቱት ራሳቸው ሃጢያት ሰላደረጉ እንጅ አዳም በውክልና የሰራላችው ሃጢያት ሰላለ አደለም::

ማንም ክርስቲያን ያልሆነ ሰው በጎ አደለም::

ካልቪናውያን ዳግመኛ ያልተወለደ ሰው በጭራሽ በጎ አይሰራም ብለው በመደምደም ክርስቲያን ከሌላው ማህበረሰብጋ ጤነኛ ያለሆነ ገንኙነት እንዲኖረው እንዲሁም፤ እንዳይቀበለው ሲያደርጉ ይስተዋላል:: እኔ እንደውም ክርስቲያን ያልሆኑትን እንድንጠላ፤ የጨለማውም ሰለሆኑ ፈጽሞ እንዳንቀበላቸው ያበረታታኝ ካልቪናዊ አጋጥሞኛል::

ይህ ትምህርት ስለ እግዚአብሔር የተዛባ አመለካከት እንዲኖረን ያደርጋል:

እግዚአበሔርን ሃጢያት ያልሰሩትን ሃጢያት እንደሰሩ እንደሚቆጥርና ያላዩትን ያልሰሙትን ያላደረጉትን ነገር እንዳደረጉ ሚያሰብ አምላክ እንደሆን እንድናሰብ ሚያደርግ የተሳሳተ አመለካከት ነው:: ይህ ትምህርት እኛ ሃጢያተኞች ነንና እራሱ ይሞጣ ብለን እግዚአበሔርን እንደ ቆርነሌወሰ፤ እንደ ነቢየቱ ሐና፤ አረጋዊው ሰምኦን መዳንን እንዳንጠባበቅ ያደርጋል: ይህ ትምህርት የወረሰኩት ነው እያልን ሃጢያትን እንድንለማመድ ያደርጋል:: ባጠቃላይ ክርሰቶሳዊ ያልሆነ ትምህርት ነው ይህ ትምህርት::

Uunconditional Election(ምክንያተ ቢሰ ምርጫ)

መግቢያ

ይህኛው ሁለተኛው የካልቪናዊአን የእምነት አቋም ሲሆን ከጠቅላላ ብክለት ተከታይ የሆነ የእምነት አቋማቸው ነው:: የጠቅላላ ብክለትን አምኖ ይህን አለማመን የሚቻል አይመሰለኝም:: የኦርቶዶክሰን የካቶሊክ አማኞች የጠቅላላ ብክለትን ባያምኑም በብክለት ግን ያምናሉ:: የካልቪኒዘሙ በክለት ጠቅላላ ብክለት በመሆኑ ሰው ፈጽሞ መልካም ማድረግ አይችልም ብለው ያምናሉ የኦርቶዶክሰና ካቶሊክ ብክለት ደግሞ ሰው ሃጢያትን ወርሷል ነው መጽሐፍ ቅዱሰ ግን ሁለቱንም በአንድም ክፍል እያሰተምርም ይህን በመጀመሪያው ክፍላችን አይተነዋል:: በዚህ ዙሪያ ሰናጠና ደግሞ ካቶሊክም ሆኑ ኦርቶዶክሰ የሚቀበሉት ሁኖ እናገኛቸውም::
የካቶሊክ ቤተ ክርሰቲያን በትሬንት ጉባኤ ይህን ትምህርት በሰሙ ጠርታ:-
“ማንም የጽድቅ ጸጋ የሚገኘው ቅድሚያ ለህይወት በመወሰን ነው ነገር ግን ሌሎች የተጠሩት ሁሉ በርግጥ ተጠርተዋል ነገር ግን በመለኮታዊ ወሳኔ አሰቀድመው ለክፋው ተወስነዋል ብሎ ሚያምን ቢኖር የተወገዘ ይሁን” (CANON XVII)
በማለት አውግዛለች:: የኦርቶዶክሰ ቤተ ክርሰቲያንም ይህን በጉባኤ ባትገለጽም አቡነ ሸኖዳ “MANY YEARS WITH PEOPLE’S QUESTIONS II” (ገጸ 10-15) በተባለው መጽሐፋቸው ላይ ሰለ ሰው ነጻ

ፍቃድ ሰፋ አድርገው አቅርበዋል ካነሱት ነጥበ ውስጥም
1ኛ.The existence of God's commandment is a proof that man has a free will. (የእግዚአብሔር ፍርድ መኖር የሰው ነጻ ፍቃድን ያረጋግጣል)
2ኛ. The existence of sin is a proof that man has a free will. (የሃጢያት መኖር የሰው ነጻ ፍቃድን ያረጋግጣል)
3ኛ. The existence of a condemnation is a proof that man has free will. (የፍርድ መኖር የሰው ነጻ ፍቃድን ያረጋግጣል) ብለው አብራርተዋል::
በኮፕት ኦርቶዶክስ የመዳን ትምህርት ገጽ 71 እና 72 ደግሞ ስለ ቅድመ ውሳኔ ሲያብራሩ "የአውግስጢን ቅድመ-ውሳኔ(እንደኔ ቅድመ-ድምዳሜ) ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የጸጋ ትምህርት ጋር የተቃርን ነው ብለው ያወግዛሉ::
ስለዚህ በቤተ ክርስቲያኒቱ ኦፊሴላዊ መግለጫ እስካልተሰጠ ድረስ በኦርቶዶክስ ና በፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ አንድ ሰው የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት መወሰን ስለማይችል ትምህርቷ ምን እንደሆነ ምናውቀው ነገር የለም ማለት ነው:: ነገር ግን ለጊዜው የአቡነ ሽኖዳን ትምህርት እና የመዳን ትምህርት ቅጻቸውን እንደ ቤተ- ክርስቲያኒቱ አቋም ከወሰድነው ቤተ ክርስቲያኒቱ በዚህ ትምህርት አታምንም ብሎ መደምደም ይቻላል ማለት ነው::

በመሰረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ቅድመውሳኔን በትክክል ያስተምራል፤ ነገር ግን የካልቪናውያን ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊው ቅድመ ውሳኔ ሳይሆን፡ የመናፍቃን "ቅድመ ድምዳሜ" ነው::

## 2.1 የካልቪናውያን ምክንያተ ቢስ ምርጫ አስተመህሮ

ከላይ እንደገለጽኩት የካልቪናውያን ቅድመ ድምዳሜ አስተምህሮ ከመጸሐፍ ቅዱሱ ቅደመ-ውሳኔ ጋር ሳይሆን ከእስልምናውና ከሜኔቃውያን ቅድመ ድምዳሜ ጋ ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ ለዚህ ምክንያተ ቢስ ምርጫ ለተባለው የስህተት አስተምህሮ አጋልጧቸዋል::

ምክንያተ ቢስ ምርጫ እግዚአበሔር የሰውን ነጻ ፍቃድ በመሻር በሉአላዊ ምርጫው አንዳንደ ሰወችን ለዘላለም ህይወት አንዳንድ ሰወችንም ለገሃነም ወሰኗል ብለው የሚያስተምር ትምህርት ነው:: ይህ ውሳኔ ደግሞ ግለሰቦችን በመልክ በቁመት በቆዳ ቀለም በቁጥር ውስን ያደረገ ምርጫ ነው ብለው ያምናሉ:: ስለዚህም ይህ ቅድመ ምርጫ በምንም ተአምር እንደማይቀየር ያምናሉ:: ይህንም እነሱ የእግዚአብሔር ሉአላዊ ቅድመ ውሳኔ ነው በማለት ይጠሩታል::

የዌስት ሚኒስተር የእምነት መግለጫ

"እግዚአብሔር በቅድመ ውሳኔወ አንዳንድ ሰወችን እና መላእክትን እንዲሁ በጸጋው እና ፍቅሩ እምነታቸውን ስራቸውን እንዲሁም በነሱ ያለውን ጽናት ሳያይ ለዘላለም ሂወት ወሰኗቸዋል:: ሌሎችንም ለዘላለም ሞት ወሰኗቸዋል የሁለቱም(ለዘላለም ሂወትም ለሞትም የተወሰኑት) በቁጥር የተወሰነ ስለሆነ በቁጥር አይጨምርም አይቀንስምም" (Chap. III, art. 3,4 &5; Chap. X, art. 2)

የ ፕሪስባይቴሪያን ቤተ ክርስቲያን የዕምነት መግለጫ USA

"እግዚአበሔር ከዘላለማ በቅዱስ ምክረ ፍቃዱ የሚሆነውን ሁሉ ያለተጸእኖ በማይቂር ሁኔታ ወሰኖታል:: ክብሩ እንዲገለጥ በእግዚአብሔር ውሳኔ የተወሰኑ ሰወችንና መላእክትን ለሂወት፡ ሌሎችንም ለዘላለም ሞት ወሰኗቸዋል:: ዕነዚህ መላእክትና ሰወች በማንነት በማይቁር ሁኔታ ተወስነዋል፤ ቁጣራቸውም ውሰን ስለሆነ አይጨምርም አይቀንሰም::" (ም 3)

INSITUTION(ካልቪን)

"ሁሉም በዕኩል ሁኔታ የተፈጠሩ አደሉም አንዳንዱ ለዘላለም ሂወት የተፈጠሩ ናቸው ሌሎችም ለዘላለም ጉስቁልና፤ እያንዳንዱመ ለአንዱ ወይም ለሌላው እንዲሁ መጨረሻው ይሆናል:: ዕኛ ዕርሱ ለሂወትና ለሞት ወሰኗል እንላለን::"

2.2 ምክንያተ ቢስ ምርጫ እውነት ቢሆን ኑሮ

1ኛ ጽድቅ የቶምቦላ ሎተሪ ይሆን ነበር

እግዚአብሔር አስቀድሞ ውሳኔው በቅድመ እውቀቱ(ማን እንደሚያምን እና እንደሚጸና ቀድሞ በማወቁ) ላይ ቢሆን ምንም ችግር ባልነበረው ነበር ነገር ግን ከላይ ካልቪናውያን አማኞች እንደሚሉን ከሆነ ግን ገና እምነቱንም ሆነ ስራውን ጽናቱንም ሳያይ ይመርጠዋል ነው ይህ ደግሞ ልክ እንደ ብሔራዊ ሎተሪ በዘፈቀድ ነው ማለት ነው:: እንዲህ ያለ አመለካከት ፈጽሞ በመጸሐድ ቅዱስ የሌለና ጽድቅ በዕምነት ነው:: እርሱን አምኖ በመምጣት ነው የሚለው የወንጌልን ጠቅላላ መልእክት ገደል ሚከት ነው::

2.ኛ ወንጌል መሰበክ አያሰፈልግም::

ሜንቶሬ እና ፓስተሬ ልጁ ለምን እግዚአበሔርን እንደካደ ጠየኩት፤ የመለሰልኝ መልስ አስደነገጠኝ

"የኔ ካልቪኒሰትነት ነበር ለጅን ከሃዲ ያደረገው"

አለኝ በሰአቱ ግራ በመጋባት ድጋሚ ጠየኩት "እንዴት?"፤ በትካዜ ትንሽ ወደኋላ ጋለበ፤ እኔም የሃሳቡን ፈረስ ለጓሙን እሰኪይዝ ጠበኩት፤ ከትንሽ ሰከንዶች በኋላ ትእግስቴ ሳያልቅ ራሱ እየባነነ::

"ልጅን ካልቪኒስታዊ አመለካከት እጭንበታለሁ ብየ ከሃዲነትን ጫንኩበት: እየህ ካልቪኒዝማዊ አመለካከቶችን ሰናወራ ምን ሰንል ነበር ድንገት ግን የሆነ ቀን 'እግዚአብሔር ሁሉን አስቀድሞ ወሰኖ ከሆነ የኔ ማመንም አለማመንም ጥቅማ አልባ ነው' አለኝ ያልጠበኩት ሰለሆነ ደነገጥኩ ይሄወ በዚህ የተነሳ ልጀ 'እግዚአብሔር ከመረጠኝ ማመኔ አይቀርም ካልመረጠኝም ማመኔ ጥቅም የለውም" ብሎኝ የአለም ለጅ ሁኗል" አለኝ

እኔም "ካልቪኒዞም እውነት ቢሆን የልጀህን ወሳኔ እኔም እወሰን ነበር" ሰለው ደነገጠ:: (በነገራችን ላይ ካደረገኳቸው ትልልቅ ነገሮች አንዱ ፓስተሬን ከካልቪኒዝም አመለካከት ማውጣቴ ነው::)

እውነት ነው እግዚአብሔር አስቀድሞ ሰለወሰነው ነገር ብዞወች ሂወታቸውን ገብረው ሰለምን ወንጌልን ይሰብካሉ? ኢየሱስ ወደ አለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልን ለፍጥረት ሰበኩ ብሎ ማዘዝ ለምን አሰፈለገው? እረ ከአለም አስቀድሞ ለጽድቅ ለተወሰኑ ሰወችስ መሞት ለምን አሰፈለገው? እንዴ በመልክ በቁመት በቁጥር ሳይቀር ተወሰነው ሳለ የሚቄር ነገር እንደማይኖር እያወቅ እግዚአበሔር ለምን አንድያ ለጁን እንዲሞት አደረገ?

3ኛ  ከእግዚአብሔር ጨካኝ አምላክ እንጅ ፍቅር አይሆንም ነበር

በምክንያተ ቢስ ምርጫ መሰረት እግዚአብሔር አንዳንዶቹን ያለጥፋታቸው ለገሃነም አለም ሳይፈጠር ወሰኗል: በዚህ መሰረት ደግሞ እግዚአበሔር ሰወችንና መላእክትን ለራሱ ክብር ሲል ያነዳቸዋል እንዲህ አይነት አምላክ በቁራን እንጀ በመጸሐፍ ቅዱስ በአንደም ሰፍራ አናገኝም:: ደግሞስ ፍቅር የተባለው አምላክ እንዴት እንዲህ ኤeነት የጭካኔ ባህርይ ሊገኝበት ይችላል? IMPOSSIBLE. ወንጌል ደግሞ እግዚአብሔር ፍቅር መሆኑን ከማሰተማሩጋ ፈጽሞ የተቃረነ ነው::

4.ኛ ባልንጀራህን ውደድ ሚለው ወርቃማው የወንጌል መልእክት ልክ ኤeሆንም ነበር::

ወንጌል መልእክቱ ሁሉ ሰለ ፍቅር ነው: እንዳውም የወንጌል መልእክትኮ ሚለው "ፍቅር ከእምነት ይበልጣል" ነው:: 1 ቆሮ 13:13 በዚህ የወንጌል ቃል መሰረት ደግሞ እኛ ባልንጀሮቻችንን እንዳወም ጠላቶቻችንን እንኳ እንድንወድ ታዞናል::  መጽሐፍ ቅዱሳችን ደግሞ እግዚአብሔርን እንድንመሰል ያሰተምረናል (ዘሌ 11:45፤19:2 20:7: 1ጴጥ 1:15-16)

ታዲያ በዚህ መሰረት እግዚአበሔር ጠልቷቸ ወደ ገሃነም የጣላቸውን እኛ እንወድ ዘንድ በውኑ እኛ ከእግዚአብሔር ይበልጥ ጻድቅ ልንሆን ነውን?

5ኛ ከክርስቲያኖች በላይ ራስ ወዳድ አይኖርም ነበር

ራስን መውደድ ና ስለ ራስን ብቻ መውደድ ይለያያሉ(እዚጋ ራስን መውደድ ስል ምጠቀመው ራስን ብቻ መውደድን ነው)፤ ብዙ ጊዜ ካልቪኒስቶችን ሳስብ ምን ያህል ራስ ወዳድ መሆናቸው ነው ድቅን ሚልብኝ:: እስቡት እስኪ ዕኔ እድናለሁ በሎ ሌላወ ግን ለገሃነም ይገባል ብሎ ሌላውን ከመኮነን እና ከማግለል በላይ ምን ራስ ወዳድነት አለ? "ሰዎች እንዲያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው"(ማቴ 7:12፤ ሉቃ 6:31) የሚለውን ቅዱስ ቃል የሻረ እምነት ከካልቪኒዝም በላይ ከወዴት ይገኛል? እኔ ገሃነም መግባት ሳልፈለግ እንዴት ሌሎች ለገሃነም ተወስነዋል ሚል እምነት ይኖረኛል? እይ እኔ አልመኛላቸውም ካሉ ታዲያ እነሱ መልካም ከሆኑላቸው እግዚአብሔርማ እንዴት አብዝቶ ቅዱስ መንፈሱን አይመኛላቸውም?

6ኛ እግዚአብሔር ታማኝ አምላክ አይሆንም ነበር

እግዚአብሔር የሚደኑትን በመልክ በቁመት በቁጥር ከወሰነና ማይቀየር ከሆነ እኔ ከነዚህ ውስጥ መሆኔን እንዴት ላውቅ እችላለሁ?

በማመንህ ወይንም በፍሬ የሚል መልሰ ብዙ ጊዜ እሰማለሁ በዚህ አይነት ደግሞ ጆን ካለቪን ራሱ የዳነ አደለም ማለት ነው ምክንያቱም ጆን ካልቪን ምናልባት ወደፊት ምናየው ወይንም በ ላምፒስ ህብረት ፔጀ እንደምናካፍለው ካልቪን ብዙ ወንጀል ያለበት ሰው ነው:: እሱም አልዳነም ማለት ነው በካልቪኒዝም እምነት መሰረት ደግሞ ካልዳነ ሰው ፈጽሞ ምንም በጎ የለምም አይወጣምም ስለዚህ ካልቪኒዝም በጎ ያልሆን አስተምህሮ ነው ማልት ነው(COMMON SENES)

በተጨማሪም መጸሐፍ ቅዱስ በ ዕብ 6: ዕብራውያን 6:4-6 "አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን ሰማያዊውንም ስጦታ የቀመሱትን ከመንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን መልካሙንም የእግዚአብሔርን ቃልና ሊመጣ ያለውን የዓለም ኃይል የቀመሱትን በኋላም የካዱትን እንደገና ለንስሐ እነርሱን ማደስ የማይቻል ነው፤ ለራሳቸው የእግዚአብሔርን ልጅ ይሰቅሉታልና ያዋርዱትማልና።" እንዲሁም 2ኛ ጴጥሮስ 20-21 "በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ከዓለም ርኵሰት ካመለጡ በኋላ ዳግመኛ በእርሰዋ ተጠላልፈው የተሸነፉ ቢሆኑ፥ ከፊተኛው ኑሮአቸው ይልቅ የኋለኛው የባሰ ሆኖባቸዋል። አውቀዋት ከተሰጣቸው ከቅድስት ትእዛዝ ከሚመለሱ የጽድቅን መንገድ ባላወቋት በተሻላቸው ነበርና።" ስለሚል የዳኑት የተባሉት ራሱ የመዳን ተሰፋ የላቸውም ማለት ነው፤ ስለዚህ ወይ እግዚአብሔር ታማኝ አምላክ አይሆንም ወይ ደግሞ የዳኑት ከቁጥር ይጎድላሉ ማለት ነው፤ ይህ ደግሞ የካልቪኒዝምን "በቁጥር የተወሰኑ ስለሆኑ ኤeጨምሩም ኤeጎድሉም ሚለው ልክ አደለም ማለት ነው"

2.3 መጽሐፍ ቅዱስ ስለተመረጡት ይናገራልን?

በማይታበል ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ የተመረጡ እንዳሉ ይናገራል:: ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ምርጫ ሲያወራ በአዲስ ኪዳን ከሆነ ስለቤተ ክርስቲያን ወይ ደግሞ በብሉይ ኪዳን ከሆነ ስለ እስራኤል ነው:: እያንዳንዱን የሚያነሷቸውን ጥቅሶች የምናይ ቢሆንም ለጥናታችን ሲባል ግን የ ኤፌሶንን መልእክት 1:4 እዚህ እምጥተን እንየው፤ ቃሉ እንዲህ ይላል
"ዓለም ሳይፈጠር፥ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን።"
በመሰረቱ የኤፌሶንን ሰዎች ላጠና ሰው ከሁለት አካል(ከአህዛብና ከአይሁድ) አንድ አካልን(ቤተ ክርስቲያንን) እንደመሰረተ(ኤፌ 2:16፤ ኤፌ 2፤14-15 ኤፌ 3:5-6) ስለመሰራቱ ሚናገር ክፍል ነው:: ስለዚህም ከአህዛብ ወደ ክርስቲያን የተቀየሩ ምእመናን ክርስቶስ በመስቀሉ የጥልን ግድግዳ በመስበሩ የተመረጠው ህዝብ አካል መሆን እንደሚችሉና ይህ የአህዛብና የአይሁድ ጥምረት የሆነቸው ቤተ ክርስቲያንም ነውር የሌላት እንድትሆን በክርስቶስ የተመረጠች እንደሆነች እየተናገረ እንጅ እግዚአብሔር በቁመትና በቆዳ ቀለም በድምጸና በግዝፈት ለይቶ የመረጣቸው ሰዎች እንዳሉ እየተናገረ አደለም:: ይህን ያለው ስለ ቤተ ክርስቲያን

ስለ ህብረቷ እየተናገረ መሆኑን ደግሞ
"እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ።" ኤፌሶን 5፥27 በማለት በጅማሬው ላይ ስለማን እየተናገረ መሆኑን በግልጽ ያሳያል::
በመሰረቱ ክፍሉን ራሱ ካየነው ተመረጥን ሚለው ላይ "ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ" እና "በክርስቶስ"
የሚሉ ወሳኝ ነጥቦች እናገኛለን፤ ከዚህ ምንረዳው የተመረጡት ቅዱሳንና ነውር የሌላቸው ይሆኑ ዘንድ ነው:: ይህ ምን ሏeጥ ያመጣል ተብሎ ቢጠየቅ:: 1ኛ ማንንማ በክርስቶስ መረጠው እንጅ በክርስቶስ እንዲያምን እንደመረጠው አይናገርም:: ይህም ማለት ለውጤቱ እንጂ ለመንስኤው የተመረጠ እንደሌለ መረዳት እንችላለን:: ስለዚህ መንኤው ለኛው የተተወ ነው ማለት ነው፤ ያም እምነት ነው፤ ስለዚህ ስናምን በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌላት ትሆን ዘንድ የተመረጠችው አለማቀፋዊት ቤተ ክርስቲያነ አካል እንሆናለን ማለት ነው:: ይህም እኛን የዚህ ወጤት ተሳታፊ ያደርገናል::

"በክርስቶስ" ሚለውን ያየን እንደሆን ደግሞ የዚህች ቤተ ክርስቲያን የቅድስናዋ ያለነውር የመሆኗ እና የመመረጧ ምንጭ የሆነው አካል ይገለጥልናል:: ክርስቶስ በእግዚአብሔር የተመረጠ ነው:
"እነሆ ደግፌ የያዝሁት ባሪያዬ፤ ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት ምርጤ፤ በእርሱ ላይ መንፈሴን አድርጌአለሁ፥ እርሱም ለአሕዛብ ፍርድን ያወጣል።"
 — ኢሳይያስ 42፥1
"ከደመናውም፦ የመረጥሁት ልጄ ይህ ነው፥ እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ።"
 — ሉቃስ 9፥35
የቤተ ክርስቲያንም የመመረጧ የቅድስናዋ ያለነውር የመሆኗ ምንጭ ይሄው ከክርስቶስ ጋር በመንፈሳዊ ጋበቻ ተጣምራ አንድ አካል መሆኗ ነው:: ኤፌሶን 5:31-32 "ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው፥ እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን እላለሁ።" ከዚህ ክፍል ምንረዳው:: የተመረጠው ክርስቶስ መሆኑን: ቤተ ክርስቲያንም የርሱ አካል በመሆን ያለነውር እንድትሆን እንተመረጠች እና ማንም በነጻ ፍቃዱ በክርስቶስ በማመን የተመረጠችው ቤተ ክርስቲያን ብልት መሆን እንሚችል ነው:: ስለዚህ ስለምርጫ በ መጽሐፍ ቅዱስ ስናገኝ የቤተ ክርስቲያን እንጅ ሰለሆኑ ግለሰቦች አለመሆኑን እኛ በእግዚአብሔር ጸጋ ምርጡን በመላክ የዚህ አካል በመሆን በክርስቶስ የእግዚአብሄር ምርጥ ለመሆን እድሉ የተሰጠን ደካም ሃጢያተኞች የሆንን የምርጡ የክርስቶስ ጽድቅ ቅድስና ያለነውር መሆን እንዲሁ በጸጋው የተቆጠረልን መሆናችንን መገንዘብ ያሰፈልጋ ል እንጅ እኛ ሰላደረግነው ሰለመልካም ሰራችን አደለም::

## 2.4 መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?
1ኛ እግዚአብሔር ለሰው የመምረጥ ነጻነትን ሰጥቷል::
ሀ. እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን የመምረጥ ነጻነትን ሰጥቷል::

እግዚአበሔር ሰውን ሲፈጥውና ሂወትን ሲሰጠው አስፈቅዶ አደለም ስለዚህም ደግሞ፤ ሂወቱን የመንሳትና ወዳለመኖር(ሞት) የመሄድ ነጻ ፍቃድን ሰጥቶታል፤ ሰለዚህም እግዚአብሔር ለአዳም የዚህን ምርጫ እጸ በለሰን በገነት ዛፎች መካከል በማሰቀመጥ ሰጥቶታል:: ዘፍ 2:16-17 የአዳም እና የሔዋን የራሳቸው ምርጫ ካሉበት ሁኔታ ይልቅ አምላክነትን በመመኘት ወደ አለመኖር ምትወሰዳቸውን እጽ በሰይጣን አታላይነት ቀጥፈው በሉ:: ነገር ግን የነሱ አላማ አምላክነት እንጅ ሞት ባለመሆኑና ተታለው ሰለበሉ እግዚአብሄር ሌላ እድል ሰጥዋቸዋል:: አሁን በዚህ የእግዚአብሄር ቃል መሰረት እግዚአብሄር አስቀደሞ ወሰኖት ከሆነ ተጠያቂው እግዚአብሔር እንጅ እነሱ ወይም ሰይጣን ኤeሆንም ነበር:: ነገር ግን ቅዱሱ መጽሐፍ "ማንም ሲፈተን በእግዚአብሔር እፈተናለሁ አይበል እግዚአብሔር በክፉ አይፈትንምና" ያዕ 1:13 ሰለሚል እግዚአብሔር በቅድመ ውሳኔም ሆነ በምንም መንገድ እጁ የለበትም::

ለ. ከውድቀትም በኋላ ሰው የዘላለም ሂወትና ሞት ምርጫ አለው

ዘዳግም 30:15-20 "ተመልከት፤ ዛሬ በፊትህ ሕይወትንና መልካምነትን፥ ሞትንና ክፋትን አኑሬአለሁ። በሕይወትም እንድትኖር እንድትባዛም፥ አምላክህም እግዚአብሔር ልትወርሳት በምትገባባት ምድር

እንዲባርክህ፥ አምላክህን እግዚአብሔርን ትወድድ ዘንድ፥ በመንገዱም ትሄድ ዘንድ ትእዛዙንና ሥርዓቱን ፍርዱንም ትጠብቅ ዘንድ ዛሬ እኔ አዝዝሃለሁ። ልብህ ግን ቢስት አንተም ባትሰማ፥ ብትታለልም፥ ለሌሎችም አማልክት ብትሰግድ ብታመልካቸውም፥ ፈጽማችሁ እንድትጠፉ እኔ ዛሬ እነግራችኋለሁ፤ ዮርዳኖስን ተሻግረህ ትወርሳት ዘንድ በምትገባባት ምድር ዘመናችሁን አታስረዝሙም በፊታችሁ ሕይወትንና ሞትን በረከትንና መርገምን እንዳስቀመጥሁ እኔ ዛሬ ሰማይንና ምድርን በአንተ ላይ አስመሰክራለሁ፤ እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን #ምረጥ፤ እግዚአብሔርም ለአባቶችህ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም እንዲሰጣቸው በማለላቸው በምድሪቱ ትቀመጥ ዘንድ፥ እርሱ ሕይወትህ የዘመንህም ርዝመት ነውና አምላክህን እግዚአብሔርን ትወድደው ትጠባበቀውም ቃሉንም ትሰማ ዘንድ #ምረጥ_ ።"
በማለት እግዚአብሔር ሂወትን እንዲመርጡ እግዚአብሄር አመላክ ለእስራኤላውያን የሞት ናየሂወት የመኖርና ያለመኖር ምርጫ ይሰጣቸዋል:: ይህ ህዝብ የተመረጠ ህዝበ መሆኑን እግዚአብሔር አምላክ ደጋግሞ ቢናገርም መመረጡ በህዝብ ደረጃ እንጅ በግለሰብ ደረጃ ባለመሆኑ በግለሰብ ደረጃ ሂወትን እንዲመርጡ ደጋግሞ ያሳሰባቸዋል::
ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ይህ ክፍል ለአዲስ ኪዳን እንደሚያገለግል
ሮሜ 10:5-14 "ሙሴ ከሕግ የሆነውን ጽድቅ የሚያደርገው ሰው በእርሱ በሕይወት እንዲኖር ጽፎአልና። ከእምነት የሆነ ጽድቅ ግን እንዲህ ይላል፦ በልብህ፦ ማን ወደ ሰማይ ይወጣል? አትበል፤ ይህ ክርስቶስን ለማውረድ ነው፤ ወይም፦ በልብህ፦ ወደ ጥልቁ ማን ይወርዳል? አትበል፤ ይህ ክርስቶስን ከሙታን ለማውጣት ነው። ነገር ግን ምን ይላል? በአፍህ በልብህም ሆኖ ቃሉ ቀርቦልሃል፤ ይህም የምንሰብከው የእምነት ቃል ነው። ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና። መጽሐፍ፦ በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም ይላልና። በአይሁዳዊና በግሪክ ሰው መካከል ልዩነት የለምና፤ አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና፥ ለሚጠሩትም ሁሉ ባለ ጠጋ ነው፤ የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ?"
በማለት ይጠቅሰዋል:: በዚሁም ክፍል ሐዋርያው ሳይሰሙ እንዴት ያምናሉ? በማለት የሚያምኑት በእግዚአብሔeረ ቅደመ ወሳኔ ሳይሆን ቃሉን ሰምተው በፍቃዳቸው በመወሰን መሆኑን ያብራራል:: በመጽሐፈ ኢያሱ ደግሞ መስፍኑ ኢያሱ:-
"እግዚአብሔርንም ማምለክ ክፉ መስሎ ቢታያችሁ፥ አባቶቻችሁ በወንዝ ማዶ ሳሉ ያመለኩአቸውን አማልክት ወይም በምድራቸው ያላችሁባቸውን የአሞራውያንን አማልክት ታመልኩ እንደ ሆነ፥ የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን።" በማለት የሚያመልኩትን እንዲመርጡ ያሳሰባቸዋል በቅድመ ውሳኔ ቢሆን እግዚአብሔር ለምን ይህን ሁሉ ድራማ መስራት አስፈለገው?
በራእይ 3 ጌታችን ሰባቱን አብያተ ክርስቲያናት ለንስሃ ጥሪ ከተጣራ በኋላ ራእይ 3፥20 ""እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።" ይላል እንጅ በአባቴ ቅድመ ወሳኔ በመሆኑ አታስቡ ባትፈልጉም ንስሃ መግባታችሁ አይቀርም አላላቸውም::
በራእይ 22፥17 "መንፈሱና ሙሽራይቱም፦ ና ይላሉ። የሚሰማም፦ ና ይበል። የተጠማም ይምጣ፥ የወደደም የሕይወትን ውኃ እንዲያው ይውሰድ።" በማለት "የወደደ" ለዘላለም ለመኖር የህይወት ውሃ ክርስቶስን በማመን እንዲሁም በመናፈቅ ወደና ፈቅዶ መኖር እንደሚችል እንጅ በተደመደመበት ላይ እንደማይሆን በግልጽ አስቀምጦልናል::

ሐ. እግዚአብሔር ፍትሐዊ አምላክ ነው

እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያደላም 2 ዜና 19፥7 "አሁንም እግዚአብሔርን መፍራት በእናንተ ላይ ይሁን፤ በአምላካችንም በእግዚአብሔር ዘንድ በደልና ለሰው ፊት ማድላት መማለጃም መውሰድ የለምና ሁሉን ተጠንቅቃችሁ አድርጉ አላቸው።" እግዚአበሔር ለሰው ፊት በማድላት ገና ቀደሞ አይወስንባቸውም:: መጸሐፍ እንደሚል ወጫዊ ገጽታን ወይንም ሌላን ወይንም ሌላን አይቶ ሚወሰን ባለመሆኑ በፊቱ መጠንቀቅ ያሰፈለጋል የኛ አጸፋ ነውና ይእግዚአበሔርን ውሳኔ በኛ ላይ ሚያስከትለው:: ካልቪኒዘም እውነት ቢሆን እግዚአብሔር ገና ምንም ሳይሰሩ የተወሰኑትን ለሂወት የተወሰኑትን ለሞት በመወሰኑ ለሰው ፊት የሚያደላ አምላክ ነው ባልነው ነበር::
"ጴጥሮስም አፉን ከፍቶ እንዲህ አለ፦ እግዚአብሔር ለሰው ፊት እንዳያደላ ነገር ግን በአሕዛብ ሁሉ እርሱን

የሚፈራና ጽድቅን የሚያደርግ በእርሱ የተወደደ እንደ ሆነ በእውነት አስተዋልሁ።”
— ሐዋርያት 10፥34-35
“እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያዳላምና።”
— ሮሜ 2፥11
“ለሰው ፊትም ሳያደላ በእያንዳንዱ ላይ እንደ ሥራው የሚፈርደውን አባት ብላችሁ ብትጠሩ በእንግድነታችሁ ዘመን በፍርሃት ኑሩ።”
— 1ኛ ጴጥሮስ 1፥17

መ. መታዘዝ የሰው ሃላፊነት እንጅ የእግዚአብሔር አደለም::

“ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤት ተነሥቶ የሚጀመርበት ጊዜ ደርሶአልና፤ አስቀድሞም በእኛ የሚጀመር ከሆነ ለእግዚአብሔር ወንጌል የማይታዘዙ መጨረሻቸው ምን ይሆን?”
— 1ኛ ጴጥሮስ 4፥17

ተብሎ ተገልጿል እግዚአብሔር መቸም በራሱ ላይ እንዲያድሙ አያደርግም ይህን ካደረገ በኋላ ደግሞ ለፍርድ ካመጣችው፤ ከላይ እንደገለጽነው እግዚአብሄር ራሱ እንጀ ሰወቹ አደሉም ማለት ነው የተሳሳቱት:: “ለምክንያተ ቢስ ምርጫ ሚያቀርቧቸው ጥቅሶችና መልሶቻቸው::”

1ኛ. ዮሐ 10:26 “እናንተ ግን እንደነገርኳችሁ ከበጎቸ ስላልሆናችሁ አታምኑም(አላመናችሁም) በጎቸ ድምጼን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ”(እንግሊዘኛው YE BELIEVE NOT ስለሚል በቅንፍ አላመናችሁም በሚለው አስፍሪያለሁ::)

ካልቪናውያን ይህን ቃል ይዘው ኢየሱስ አስቀድመው የተወሰኑ በጎች አሉት ማመን “ሚችሉ” እነሱ “ብቻ” ናቸው ብለው ያሰባሉ በትምህረተ ጥቅስ ያሰቀመጥኳቸው ቃላት ካለቪናውያን ለማሳሳቻነት ሚጨምሯቸው ቃላት ስለሆኑ ነው:: የካልቪናውያንን ጸሁፍ ስታነቡም ሆነ ቪዲዮ ስታዩ በጣም እንድትጠነቀቁ ምመክራችሁ እንዲህ አይነት እርሾ በመጨመር በጣም የተካኑበት ስለሆነ ነው:: ካልቪናውያን መጽሐፍ ቅዱስን ሲያነቡላችሁም ሆነ ሲጸፉላችሁ መጽሐፍ ቅዱሳችሁን ከፍታችሁ አንብቡ ይህንና ወደ ፊት በምመጣባቸው ጊዚያት ሁሉ እንዲህ ያለ ጥቃቅንየ ልናስተውላቸው ና ልናሰባቸው ማንችላቸው የቃላት ጭማሪወችን ያደርጋሉ:: ቃሉን በቃላችሁ ብታስታውሱት እንኳ ቃሉን ከፍታችሁ አንብቡ:: ወደ ቀደመ ነገራችን ስነመለስ፤ ይህ ንግግር ሚጀምረው ከ ም 9 መጨረሻ ላይ ሲሆን ንግግሩንም ሚያደርገው ከፈሪሳውያን ጋር ነው:: ይህም “ የማያዩም እንዲያዩ የሚያዩም እንዲታወሩ መጣሁ” ብሎ ለተፈሰው አይነ ሰውር ሲነግረው “እኛ እውሮች ነንን?” ብለው ከሚጠይቁበት ክፍል ጀምሮ ነው:: እዚጋ ልናስምርበት ሚገባን ነጥብ ኢየሱስ “ዕውሮችስ ብትሆኑ ሃጢያት ባልሆነባችሁ ነበር አሁን ግን እናያለን ትላላችሁ ሃጢያታችሁ ይኖራል” በማለት የፈሪሳውያንን ግብዝነት ይናገራል እንግዲህ ጌታችን ኢየሱስ የፈሪሳውያን ያለ ማመን ምክንያት ግብዝነታቸው ለጽድቅ እንደከለከላቸው ያሰምራል::(ይህን ክፍል ይበልጥ ለማጥናት ሰለ ፈሪሳውያን እንደታጠኑ አበረታታለሁ::) ም 10 ቁ 1 ላይ “ወደ በጎች በረት በበሩ የማይገባ በሌላ መንገድ ግን የሚጣ እርሱ ሌባ ወንበዴም ነው” ይላቸዋል በሩም ራሱ ጌታችን መሆኑን “በሩ እኔ ነኝ” በማለት በእርሱ በኩል ካልሆነ በቀር በሌላ መንገድ(በህጉ፤ በሰራቸው፤ መጻህፍትን በመመራመር) ወደ በረቱ(መንግስቱ) ለመግባት ሚሞክር ሁሉ ወንበዴ መሆኑን ይነግራቸዋል:: እንግዲህ በጎች ክርሰቶስ ከመምጣቱም በፊት እንደነበሩ በቁ 8 ላይ ይናገራል በጎቹ የማን ሁነው ነው የኖሩ? ብለን ብንጠይቅ “በጎቹ” በማለት የአብ በግ እንደሆኑ ይናገራል:: እንግዲህ በጎች ክርሰቶስ ከመምጣቱ በፊት የአብን ቃል በትክክል እያመኑ የኖሩ ከእርሱ የተማሩ እንደሆኑ ይገልጻል:: ፈሪሳውያን ታዲያ አብን አያውቁምን? ብለን ብንጠይቅ እነርሱ መሲሁን ለመዳን ተሰፋ ከማድረግ ይልቅ በራሳቸው ጽድቅ የሚመኩ ነበሩና መጻህፍትን ቢያነቡም ቢመረምሩም ስለክርሰቶስ እንደሚናገሩ ባለማወቃቸው በጎች መሆን አልቻሉም ስለዚህ ኢየሱስን አላመኑም “ሙሴንስ ብታምኑ እኔን ባመናችሁ ነበር፤ እርሱ ስለኔ ጸፏልና:: መጻህፍትንስ ካላመናችሁ ቃሌን እንዴት ታምናላችሁ?’ ስለዚህ:: እንግዲህ በጎች ያለመሆናቸው ሚስጥር ግልጽ ነው::
LOGICAL CONCLUSION 1
1.ኛ የአብ በጎች ስላልሆኑ ነው
2.ኛ የአብ በጎች ያልሆኑት ከአብ ስላልተማሩ(መጻህፍትን ስለማያውቁ) ነው::

3.ኛ አብ የራሱን በጎች(የአብን ፈቃድ የሚያደርጉትን) ለወልድ ሰጥቶታል:: ዮሐ 10:29

ድምዳሜ: የኢየሱስ በግ ለመሆን ከአብ መማር(በቅዱሳት መጸህፍት የተነገሩትን መቀበል) ከዛም በጉ መሆን ያስፈልጋል፤ አብም ለክርስቶስ ይሰጠናል:: ስለዚህም የክርስቶስ በጎች እንሆናለን::

አመክንዮው ይህ ነው እንጅ በዚህ ቦታ አንድም ቦታ አስቀድሞ ስለወሰናቸው ወይንም ራሱ በምክንያተ ቢስነት የመረጣቸው በጎች እንዳሉ አይናገርም::

እስኪ ካልቪናውያን ይህን ይመልሱልን? አማኞች ሁሉ የኢየሱስ በጎች ለመሆን ቀድመው ከተመረጡና ድምጹንም ቀድሞውኑ ሚያውቁት ከሆነ ለምን ወንጌል ሲሰበክላቸው በአንዴ አሜን ብለው አይመጡም? ድምጹን የሚያውቁት አደሉምን?

2.ኛ “በቀባኸው በቅዱሱ ብላቴናህ በኢየሱስ ላይ ሄሮድስና ጴንጤናዊው ጲላጦስ ከአሕዛብና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር፥ እጅህና አሳብህ እንዲሆን አስቀድመው የወሰኑትን ሁሉ ሊፈጽሙ፥ በዚች ከተማ በእውነት ተሰበሰቡ።”
 — ሐዋርያት 4፥27-28
REALY? አስቀደሞ መወሰን ሚባል ሲያዩ በቃ ምንም አይቀራቸውም ጠቅለልል አድርገው ይጠቅሳሉ:: እውነት ይህ ክፍል እግዚአብሔር ነው ወይንስ ሰወቹ ናቸው የወሰኑት? ሰወቹ ታዲያ እዚህጋ ምን ቅድመ ውሳኔ ይታያል? ምናልባት “እጅህና አሳብህ እንዲሆን” ከሆነ ታዲያ ይህ ምን ነው ችግሩ? እግዚአብሔር ለጁ በሃጢያተኞች ሰፍራ እንዲሞት አሳቡ አደለምን?

3ኛ. ሐዋ “አሕዛብም ሰምተው ደስ አላቸው የእግዚአብሔርንም ቃል አከበሩ፥ ለዘላለም ሕይወትም የተዘጋጁ ሁሉ አመኑ፤” ሐዋርያት 13፥48
ካልቪናውያን እዚጋ “ለዘላለም ሕወት የተዘጋጁ” ሚለውን ይይዙና እንደተለመደው አንዲት አሳሳች ቃል ይጨምሩባታል እስኪ እነሱ ሲያነቡ ሚሉትን እና ቃሉ ሚለውን እንብቡ: እንዲህ ነው ሚያነቡት እነሱ “አሕዛብም ሰምተው ደስ አላቸው የእግዚአብሔርንም ቃል አከበሩ፥ ለዘላለም ሕይወትም በእግዚአብሔር የተዘጋጁ ሁሉ አመኑ፤” እንግዲህ የሚጨምሯት ቃል አንድ ስለሆነች ቃሉ ግን ተመሳሳይ ስለሆነ በቃላችን ብናውቀው እንኳ የሚጨምሯትን ቃል ለማስተዋል ጊዜ አይኖረንም:: ከላይ ያለው ኦሪጅናሉ ቃል “በእግዚአብሔር” ሚል የለውም:: ታዲያ ሰው ራሱን ለዘላለም ሂወት ሊያዘጋጅና ላያዘጋጅ ይችላል ወይ? ብለን ብንጠይቅ መልሱን እዛወ ላይ ከፍ ብሎ ቁጥር 46 ላይ “ጳውሎስና በርናባስም ገልጠው፡- የእግዚአብሔር ቃል አስቀድሞ ለእናንተ ይነገር ዘንድ ያስፈልጋል፤ ከገፋችሁትና የዘላለም ሕይወት እንዳይገባችሁ በራሳችሁ ከፈረዳችሁ ግን፥ እነሆ፥ ወደ አሕዛብ ዞር እንላለን።”
 ሐዋርያት 13፥46
 በማለት የዘላለም ሒወት እንዳይገባቸው አይሁድ #በራሳቸው ራሳቸው ላይ ፈርደዋል እንጅ እግዚአብሔር አስቀድሞ አልወሰነላቸውም:: ስለዚህ ቁጥር 48 ም በተመሳሳይ አውድ CONTRARY ሁኖ ሰለምናገኘው ራሳቸውን ያዘጋጁት ራሳቸው እንጅ እግዚአብሔር ነው የሚል ምንም አይነት መሰረትም ሆነ ሐሳብ የለውም:: ቃሉም የለም አውዱም የለም:: ተዘጋጁ መባሉም ቀድመው ወንጌልን ተሰብከው ነበርና ይህ ያመኑበት እለት በሁለተኛው ሰንበት ሰለሆነ ሳምንቱን የሰሙትን ቃል እንስላሰለውበት የመጡት መሆኑን ለማመልከት ነው::
 ከአውዳዊ ጥናት በተጨማሪ “የተዘጋጁ” ሚለውን ግሪከኛውን ሰናየው τάσσω “ታሶ” የሚል ሁኖ እናገኘዋለን፤ ይህም ቃል በአዲስ ኪዳና ውስጥ 8 ጊዜ ብናገኘውም አንድም ቦታ ቅድመ ውሳኔን እያሳይም ሁሉም መታዘዝን: መቁረጥን ወይንም መገዛትን እንጅ ማቴ 28:16 ኢየሱስ እንዳዘዛቸው ሉቃ 7:8 የመቶ አለቃው የሚገዛው ሰው እንዳለው ሐዋ 15:2 ሐዋ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመጡ መቆረጡን ሐዋ 22:10 እና የመሳሰሉት እንጅ ቅድመ ውሳኔን ሚያመለክተው προορίζω “ፕሮሪድዞ” ሚለው ቃል አልዋለም:: ስለዚህ እነዚህ ሰወች በእግዚአብሔር በቅድመ ውሳኔ ያመኑ ናቸው ለማለት ሚያስችል ምንም አይነት ነጥብ አናገኝም::

 4ኛ ሮሜ 8:28-30
“አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው፤ የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው።”

እግዚአብሔር የመረጠው ማንን ነው በማለት ያነኑ ክፍል ብንጠይቅ "አስቀድሞ ያወቃቸውን መምረጡን" ክፍሉ ያስረዳል፤ ስለዚህ እዚህጋ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸው የተባሉት እነማን ናቸው? ይህን ለመመለስ ሁለት አማራጮች አሉን አንደኛው *ጥቃሌ* ሲሆን *በክርስቶስ ማወቅ* ደግሞ ሁለተኛ ሁኖ ይከተላል የመጀመሪያውንና ጥቃሌውን ስናው እግዚአብሔር ሚያውቃቸው የፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ ወይንስ ያጸድቃቸውን ብቻ? ብሎ መጠየቁ ራሱ ወደመልሱ ያደርሰናል አምላክ በመሆኑ ራሱ እግዚአብሔር ሁሉን ያውቃልና ሁሉም ይጸድቃሉ ወደሚል ድምዳሜ ያስገባናል ምናልባት አይ እግዚአብሔር ሓጥያተኞችን አስቀድሞ አያውቅም እንዳትልመጽሐፈ ኢዮብ 11፡11 "ምናምንቴዎችን ሰዎች ያውቃልና፥ በደልንም ሲያይ ዝም ብሎ አይመለከትም።" በማለት እግዚአብሔር እውቀቱ በሃጢያተኞች ላይ ውስንነት ያለበት እንዳልሆነ ይመሰክራል"፡፤ ሌላው እና ተከታዩ ደግሞ በክርስቶስ የሚያውቃቸውን ከሆነ ደግሞ ሚያውቃቸው ፈቃዳቸውን ተጠቅመው እርሱን በመቀበል ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ቅዱሳን መጻህፍት ደጋግመው ያስረዳሉ የዮሐንስ ወንጌል 1፡11 ይህን ሲያስረዳም "የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤" በማለት ፍቃዳቸውን ተጠቅመው በመቀበልና ባለመቀበል ላይ የተመሰረቱ እንደሆኑ ይናገራል።

5ኛ ሮሜ 9:11-16
“ልጆቹ ገና ሳይወለዱ፥ በጎ ወይም ክፉ ምንም ሳያደርጉ፥ ከጠሪው እንጂ ከሥራ ሳይሆን በምርጫ የሚሆን የእግዚአብሔር አሳብ ይጸና ዘንድ፥ ለእርሰዋ፦ ታላቁ ለታናሹ ይገዛል ተባለላት። ያዕቆብን ወደድሁ ኤሳውን ግን ጠላሁ ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው። እንግዲህ ምን እንላለን? በእግዚአብሔር ዘንድ ዓመፃ አለ ወይ? አይደለም። ለሙሴ፦ የምምረውን ሁሉ እምረዋለሁ ለምራራለትም ሁሉ እራራለታለሁ ይላልና። እንግዲህ ምሕረት ለወደደ ወይም ለሮጠ አይደለም፥ ከሚምር ከእግዚአብሔር ነው እንጅ”

ካልቪናውያን ለዚህ ክፍል አውዱን ያልተከተለ ፍች አላቸው:: ይህም ቃሉ ስለግለሰቦች ምርጫ እንደሆነ አድርገው ነው:: በመሰረቱ ይህ ክፍል ሚያወራው ስለ አሕዛብና አይሁድ ምርጫ እንጅ ስለ ግለሰቦች ምርጫ አደለም እንዲህ ያለ ነገርም አያነሳም። ይህን “የምህረት እቃወች አይሁድ ብቻ አይደሉም ከአይሁድ ደግሞ የጠራን እኛ ነን” ቁ 24 “እንግዲህ ጽድቅን ያልተከተሉ አህዛብ ጽድቅን አገኙ እርሱ ግን ከእምነት የሆነ ጽድቅ ነው” ቁ 30 በማለት ያሳያል ይህን ክፍል በሰፋት ሰናጠናው የተመረጡ ህዝቦች አይሁድ ሆነው ሳለ እንዴት አህዛብ ይጸድቃሉ ለሚለው OBJECTION መልስ እየሰጠ ነው:: ጳውሎስ ሲመልስ “እግዚአብሔር የምምረውን እምረዋለሁ የምራራለትን እራራለታለሁ ይላል” ስለዚህም ለአህዛብ ለመራራትና ምህረት ለማድረግ የእግዚአብሔር ሉአላዊ ፍቃድ ነው አንተ ምን አገባህ? ነው ቁሞ ነገሩ:: “ሕዝቤ ያልሆነውን ሕዝቤ ብየ ያልተወደደችውንም የተወደደች ብየ እጠራለሁ” ቁ 25 በማለት ይህ ክፍል ስለ NATION እንጅ ስለግለሰብ እንደማያወራ ይናገራል እንዲያውም እግዚአብሄር ዘር ባያስቀር ኑሮ እስራኤል ይጠፋ ነበር የለናል በ ቁ 29 ለምን? ብለን ሚለውን ሲመልስ በስራ እንጅ በእምነት ጽድቅን ስላልተከተሉ ነው ይለናል:: አህዛብስ ለምን ተመረጡ? ሚለውን ደግሞ በ ቁ 30 ሲመል “ከእምነት የሆነ ጸደቅን” ስለተከተሉ መሆኑን ያስረዳናል:: ስለዚህ እግዚአብሔር በህዝብ ደረጃ አህዛብ የተመረጡ አልነበሩም አሁን ግን ተመርጠዋል:: ማንም ሰው ለምን ብሎ አህዛብ በእምነት በኩል ይመረጣሉ ብሎ መጠየቅ አይችልም ምክንያቱም ይህ የእግዚአብሔር መብት ነውና:: ነገር ግን ተመርጫለሁ ብሎ ብለው አህዛብ ደግሞ በትእቢት አይሁድን እንዳይንቁ መቸም አልወድቅም  እንዳይሉ
ሮሜ 11:19-22 "እንግዲህ፦ እኔ እንድገባ ቅርንጫፎች ተሰበሩ ትል ይሆናል።  መልካም፤ እነርሱ ከአለማመን የተነሣ ተሰበሩ አንተም ከእምነት የተነሣ ቆመሃል። ፍራ እንጂ የትዕቢትን ነገር አታስብ። እግዚአብሔር እንደ ተፈጠሩት ለነበሩት ቅርንጫፎች የራራላቸው ካልሆነ ለአንተ ደግሞ አይራራልህምና።“እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጭከና ተመልከት፤ ጭከናው በወደቁት ላይ ነው፥ በቸርነቱ ግን ጸንተህ ብትኖር የእግዚአብሔር ቸርነት በአንተ ላይ ነው፤ ያለዚያ አንተ ደግሞ ትቆረጣለህ።” በማለት በግለሰብ ደረጃ ግን ከተመረጠው ህዝብ መካከል ተቆርጠህ እንደምትጣል(እንደምትጠፋ) ይገልጻል:: ስለዚህ ይህ አውድ የሚያስተምረው በህዝብ ደረጃ እንጅ በግለሰብ ደረጃ መመረጥ እንደሌለ ነው:: ስለዚህ ማንኛውም ሰው ከተመረጠው ህዝብ መካከል ማንም በእምነት መጣበቅ ይችላል ማንም ደግሞ ተቆርጦ ሊጣል ይችላል:: ለምሳሌ ሊቨርፑል ሚባል ክለብ አለ አንድ የሊቨርፑል ተጫዋች ከሊቨርፑል ሊገባም ሊወጣም ይችላል፤ ዘንድሮ ሊቨርፑል ዋንጫ ቢበላ ተጫዋቾች ኖሩም ለቀቁም የ 20202 ሻመፒየን ሊቨርፑልነቱ አያቆምም: የዛሬ 10 አመት አንድ አዲስ ተጫዋች ለሊቨርጱል ቢፈርም በ

2020 ዋንጫ በልተናል ብሎ መናገር ይችላል ምክንያቱም ነገሩ የግሩፕ እንጀ የግለሰብ አደለምና::

በነገራችን ላይ በ ምክንያተ ቢሰ ምርጫ መሰረት እግዚአብሔር ሉአላዊ አምላክ አደለም

ጌታችን ኢየሱሰ በማቴ 5:48 "እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ ይላቸዋል" "እንግዲህ" ምትለው ቃል ከላይ የቀጠለ መሆኑን ያሳያል:: ከላይ ምን ይላል ብንል ቁጥር 44 ላይ "በሰማይ ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ወደዱ" ይላል:: እንግዲህ የእግዚአብሔር ፍጽምና ጠላቶቹን መውደዱ ላይ ነው:: "የመረጣችሁትን ጠላቶቻችሁ ውደዱ" ይላልን? አደለም:: "ጠላቶቻችሁን" በማለት እንጅ እንግዲያሰ እግዚአብሔር ጠላቶቹን እንዴት እንደሚወድ አሳየ? ያለልዩነት "በክፉወችና በበጎወች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፤ በጻድቃንና በሃጢያተኞች ላይ ዝናቡን ያዘንባልና" በማለት ይገልጻል:: ክፉም ሆነ በጎ ጻድቅም ሆነ ሃጢያተኛ እርሱ ያለ ልዩነት ይወዳልና ይህ የእግዚአብሔር ፍጽምና ነው:: እንግዲህ ሁሉን ከወደደ እግዚአብሔር ለጽድቅ ጊዜ1ኛ  የሚወደውን ሁሉ ለማጽደቅ ነጻ አደለም ግማሹን ለማጽደቅ ግማሹን ግን ለፍርድ ለመመደብ ግዴታ ተጥሎበታል ማለት ነው:: ማን? ይህ የካልቪኒሰቶች ችግር ነው:: የኛ አይሆንም:: እንኪያሰ እግዚአብሔር ሃጢያተኛው ይጠፋ ዘንድ ፍቃዱ ሰለሆነ ነውን? ይህም ፈቃዱ አደለም "ሕዝ 18:23 "በውኑ ሃጢያተኛው ይሞት ዘንድ እፈቅዳለሁን? ይላል ጌታ እግዚአብሔር ከሃጢያቱ ይመለሰና በሒወት ይኖር ዘንድ አይደለምን?" በማለት ፈቃዱን ይነግረናል:: እንግዲህ በካልቪናውያን መሰረት ሰው ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርም ነጻ ፈቃድ የለውም:: ምክንያቱም እንዲሞት የማይፈቅደውን ሃጢያተኛ ባለመምረጥ አንድ ካልቪናውያን ብቻ ሚያውቁት የበላይ አካል እንዳይመርጠው አግዶታል:: የታል የአምላክ የፈቃዱ ፍጻሜ? በውኑ ያታለ? 1ኛ ጢሞ 2:3-4 "ሰወች ሁሉ ሊድኑ እና እውነቱን ወደማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር" ይላል ሐዋርያው:: እንግዲህ እግዚአብሔር ሐጢያተኞችን "ይወዳል፤ ፈቃዱ ሕይወትን እንዲወርሱ ነው፤ እንዲድኑም ይወዳል":: በምክንያተ ቢሰ ምርጫ ግን ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር ምርጫ ተሸሮ፤ እግዚአብሔር ሃጢያተኞችን አይወድም ምክንያቱም እግዚአብሔር የወደደውን ያደርጋልና መዝ 135:6::

6ኛ የኤፌሶን መልእክት ነበር ሃሳባችንን ለማስረዳት ሰንል በ አንቀጽ 2.3 "መጽሐፍ ቅዱስ ሰለተመረጡት ይናገራልን በሚለው ርእሰ ሰር መልሰናል::

"LIMITED ATONMENT"(ውሱን ቤዘወት)

መግቢያ

እውነት ለመናገር እንደዚህኛው ክፍል ካልቪኒዝምን ለመገምገም ያሰቸገረኝ ክፍል የለም ይህን ጽሁፍ ለማዘጋጀት በጣም ብዙ የካልቪናውያንን ጽሁፎች ለማየት ሞክሪያለሁ:: ነገር ግን ይህንን በጣም ፈታኝ ሚያደርገው በዚህ ጉዳይ ላይ ቋሚ የሆነ የካልቪናውያን አመለካከት የለም:: አንዳንዶቹ በዚ አያምኑም እንደውም ካልቪን ራሱ በውሱን. ቤዘወት(ኢየሱሰ ለተመረጡት ብቻ መሞቱን) አለማመኑ በራሱ ገርሞኛል:: ገላ 5:12 ን ሲተረጉም "...እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ ያለምንም ልዩነት መዳን  ክርሰቶሰ ለአለም ሁሉ እንደሞተ አዞናልና" ቆላሰያሰ 1:14ን ሲተረጉም "በመሰዋእታዊ ሞቱ የአለም ሃጢያት ተወገደ" ሮሜ 5:18ን ሲተረጉም "ክርሰቶሰ ለአለም ሁሉ ተሰቃየ  በዕግዚአብሔር በጎነት ለአለም ሁሉ ተቸረ ነገር ግን ሁሉ አልተቀበሉትም" ብሏል ይህ ለኔ እንግዳ ሰለሆነ በዚህ ጉዳይ ላይ ጊዜ ሰጥቼ ማሰብን አበረታቶኛል፤ እንዳውም አንዳንዶች እንደ  LEWIS SPERRY CHAFER የዳላሰሰ ቲኦሎጂካል ሴሚናሪ መሰራች ያሉት ራሳቸውን "ባለ አራት ነጥብ ካልቪኒሰቶች" (lewis sperry chefer, systematic theology ,dallas Texas seminary press 1948, 3:184) ብለው ጠርተዋል:: ለአንዳንዶች ይህን መቀበል ያቃታቸው በጣም ደካማው የካልቪኒዘም ነጥብ በማለት ነው:: በዚህ የተነሳ "ይህን ነጥብ እንርሳው በመዳን ላይ የእግዚአብሔር ሉአላዊነት ጦርነት ላይ ተሸናፊወች ሆንን::"(ካልቪኒሰቶች በመዳን ላይ የእግዚአብሔርን ሉአላዊነት እንደሚያጎሉ ሰልሚያምኑ መሰለኝ ይህ ያለው) በማለት እነ ጆሴፍ ተነዘዋል(Joseph .M willson "How is the atonment Limited?" the baptist examiner, December 9, 1989) ጆን ማካርተር በበኩሉ "እግዚአብሔር ሁሉ እንዲድን ፈቃዱ ነው ነገር ግን እንዲድኑ የወደደውን ሁሉ

አልመረጣቸውም አስቀድሞም አልወሰናቸውም"( John MacArthur study bible , Nashvill: word publishing, 1997) 1862:: በማለት ገልጿል ነገሩ በካልቪናውያን ዘንድ ግራ አጋቢ ሚያደርገው ደግሞ በአምላክ ሉአላዊነት እናምናለን በሚለው የካልቪኒዝም ክፍል ዘንድ ይህ መባሉ እንግዳ ነው:: እግዜር ያሳያችሁ እንግዲ በካልቪኒዝም መሰረት ይህ እግዚአብሔር ፈቃዱንና የሚወደውን እንኳ ማደረግ የማይችል አምላክ ነው ታዲያ ሉአላዊነቱ ምን ላይ ነው? ብለን በክፍል 2 "ለ" መጠየቃችን ይታወሳል አሁን ደግመን እንጠይቃለን:: ሉአላዊነቱ ምን ላይ ነው? ካልቪናውያን እንዲህ አንዱ ከአንዱ የተለየ አቋም ስላላቸው አንዱ አንዱን HYPER CALVINIST እያለ ይከሰዋል:: ሁሉም ስለሚባባሉ እኔ ሁሉንም በሚጠራሩበት ሰም HYPER CALVINIST እላቸዋለሁ::

በቤተ ክርስቲያን ትውፊት ላይ ደግሞ ካልቪናውያን ይህንን ትምህርት እንደሌላው(በተለይ አጠቃላይ ብክለት) አለማግኘታቸው ለካልቪናውያን ሌላወ ትልቁ ፈተና ነው:: የፕሪስ ባይቴሪያን ጸሐፊ walter Elwell "የጠቅላላ ቤዘወት ተሟጋቾች ከታሪካዊው የቤተክርሰቲያን ነው ነጥባቸውን ሚጀምሩት ከብዙ ቲኦሎጅያን: ተሐድሷውያን: ወንጌላውያን እና በዕርግጥ አውግስጢን ባይኖርበትም ከአባቶች በመነሳት በደምዳሜው ከተሐድሶ በፊት ያሉትን ጸሐፊወች እስከዛሬይቱ ቤተ ክርቲያን ደረሰ ይይዛል:: ከተሐድሶ ሰወች መካከል(ትምህርታቸው) ከሉተር: ሜላንችቶር ቡሊንገር: ላትመር: ኮቬርዳል: ካልቪንም ጨምር በአንዳንድ ማብራሪያወቹ ይገኛል::" (walter Elwell, Evangelical dictionary of theology: Atonment, Grand Rapids MI: Eardman, 1994. ገጽ 97) በማለት አረጋግጧል:: ጀምስ ዋይት ደግሞ ዴቭ ሀንት ጋር በነበረው ሙግት "በቤተ ክርስቲያን ትውፊት የተጨኮነ ትምህርት" ብሎታል(አሰቂኝ)

በአለም አቀፍ ቤዘወት የማያምኑትን(የሚያምኑ ሰላሉ) ካልቪናውያን ለምን ነው ክርስቶስ ለአለም አልሞተም ብላችሁ አታምኑም ብላችሁ ብታቀርቡላቸው 1ኛ አለም ሚለው ቃል ብዙ ትርጉም አለው ይላሉ(STARANGE) 2ኛ. ለአለም ከሞተማ አለም በሙሉ ይድናል ይላሉ(የሰውን አጸፋዊ ምላሽ የዘነጋ አስተሳሰብ: ወይም በካልቪናዊ ትምህርት ጥልቅ ሰትልና እግዚአብሔር በሉአላዊ ፍቃዱ ለሰው ነጻ ፍቃድን እንደሰጠ ሰትዘነጋ ሚገጥመህ):: በነገራችን ላይ ውሱን ቤዘወት "ጠቅላላ ብክለት" ጋ ሚጋጭና ሚደመሰስ ትምህርት ነው ምክንያቱም ክርሰቶስ የሞተላቸው ሁሉ ድነዋል ከተባለ ተበክለዋል ወይም በእግዚአብሔር አምጸዋል ማለት አንችልም ምክንያቱም ክርሰቶሰ ሞቶላቸዋልና ንጹሃን ናቸው:: ሌላውን ነጥባቸውን በመልስ ክፍላችን አብረን ምናየው ይሆናል::

1. ካልቪናውያን ምን ብለው ያምናሉ?

Curtis C. Thomas.

"የክርስቶስ የቤዛነት ስራ ለተመረጡት ብቻና ለነርሱ ጥቡቅ ደህንነት የታለመ ነው:: ሞቱ ለተወሰኑ ሃጢያተኞች የሃጢያት ቅጣት ምትካዊ መሰዋእት ነበር:: የክርስቶስ ቤዛነት የህዝቡን ሃጢያት ከማሰወገድም በተጨማሪ ደህንነታቸውንና ከእርሱ ጋር ያጣበቃቸውን እምነት ያረጋገጠ ነው:: የእምነት ስጦታ በትክክል በመንፈስ ቅዱስ ክርስቶስ ለሞተላቸው ተከናውኗል በእርሱም መዳናቸው ተረጋግጧል:: (The Five Points of Calvinism, Defined, Defended, Documented, p. 17)

"ሰናየው ክርሰቶሰ ለሁሉ አልማለደም ለሁሉም አልሞተም::" (John Owen, the deth of Christ,, works of John Owen Volume 10)

ከዚህ እንደምንረዳው ካልቪናውያን "እግዚአብሔር የሞተው በእግዚአብሔር ዘንድ በምክንያት ቢሰነት ለተመረጡት ብቻ እንደሆነ:: እግዚአብሔር የመረጣቸው ጥቂቶች እንደመሆናቸው መጠን ልጁን ለአለም መላክ አስፈላጊ አስፈላጊ እንዳልሆነ ወይንም ሞኝነት እንደሆነ:: ስለዚህም ክርሰቶስ የሚሞተው ለምርጦቹ ብቻ መሆኑ ትክክለኛ እና መጸሐፍ ቅዱሳዊው የወንጌል መልእክት እንደሆነ ነው::

2. ውሱን ቤዘወት እውነት ቢሆን ኑሮ

2.1 ኢየሱስ አማላጅ አይሆንም ነበር::

ብዙ ካልቪናውያንን ሳናግር ባኢየሱስ አማላጅነት ያምናሉ:: የተለያየ አመለካከት ያላቸው እንደመሆናቸው መጠና ደግሞ አንዳንዶቹ "የኢየሱስ ሞት ብቻ ለመዳን በቂ ነው ብለው የሚያምኑ ናቸው" ይህ ደግሞ ሊቀ ካህንነቱን መካድ ነው ምክንያቱም ሊቀ ካህናቱ ከመሰዋእት ማቅረብ በተጨማሪ ማማለድ አንዱ አገልግሎቱ ስለሆነ:: ሁለትም ኢየሱስ አሁን በሰማይ ባለችው መቅደስ አገልጋይነቱን መካድ ነው:: አንዳንዶቹ ደግሞ ኢየሱስ ሚያማልደው ለተመረጡት ብቻ ነው ብለው ያምናሉ የተመረጡት ደግሞ እንዴ በሰም በአካል በቁመትና በቆዳ ቀለም የተወሰኑ በመሆናቸው ኢየሱስ ለዘላለም ለማማለድ በሂወት መኖር ባላስፈለገው ነበር:: መጽሐፍ ደግሞ ለማማለድ ለዘላለም ሕያው ሁኖ እንደሚኖር ይነግረናል::

2.2 ኢየሱስ ሕግን መፈጸም አያስፈልገውም ነበር::

ኢየሱስ ሕጉን የፈጸመው ሕጉን መፈጸም ላልቻሉ ሃጢያተኞች ነው ኢየሱስ ደግሞ የሞተው ለተመረጡት ከሆነ የተመረጡት ደግሞ በማንነታ የሚታወቁ ስለሆኑ ከልጅነታቸው ጻድቃን ናቸው አለዚያ ግን የኢየሱስ ሞት ከንቱ ነበር ማለት ነው::

2.3 የተመረጡት ሞትን ሊቀምሱ አይገባም ነበር::

የሞት አስፈላጊነት ሃጢያት ሚሰራ ሰውነትና አጥፍቶ ሃጢያትን የማይሰራ ሰውነትን መተካት ነው:: ምክንያቱም ሃጢያት የሰራ ሰውነት(ምድራዊው) ፍርጃው ሞት ስለሆነና ስለሚበሰብስ ሃጢያትን ማይሰራ ሰውነት(መንፈሳዊ) ይሰጠናል:: 1 ቆሮ 15 ሙሉውን ማንበብ በቂ ነው ይህነ ለመረዳት:: ነገር ግን ክርስቶስ የሞተው ለተመረጡት ብቻ ስለሆነ:: እነዚህ የተመረጡት ደግሞ ክርስቶስ ሃጢያታቸውን በቅድመ ውሳኔ ስለደመሰሰ ሃጢያት ቢሰሩም ሃጢያት ስለማይሆንባቸው ፍጹማን ስለሆኑ ሞትን መቅመሳቸው ምክንያታዊ አደለም::

2.4 ክርስቶስ ከሞት መነሳት አልነበረበትም::

ምክንያቱም የክርስቶስ ትንሳኤ አላማ::(KEEP IN MIND UNCONDITIONAL ELECTION WITH THE FOLLOWING REASONS MEANS FAITH IS OUT OF COMPOSIT)

1. እኛን ስለማጽደቅ(ሮሜ 4:24-25) (ከአለም አስቀድሞ ለጽድቅ ስለተመረጡ ትንሳኤው አያስፈልግም::)
2. ለእኛ የሙታን በኩር ለመሆን ወይንም የእርሱ ሞትን ድል ማድረግ ለእኛ ለማካፈል::(ቆላ 1:18)(ለተመረጡት ክርስቶስ ስለሞተ እነርሱ ሃጢያታቸው በመስቀል ስለተደመሰሰ ሞት. ሊነካቸው ስለማይገባ
3. ሊያማልድልን(የሰማይቱ መቅደስ አገልጋይ ለመሆን)(ዕብ ም7 እስከ9) ስለሃጢያታቸው ክርስቶስ እንዴ ስለሞተላቸው ሃጢያታቸው ስለማይቆጠር:: መቆጠር ከጀመረ ደግሞ ክርስቶስ ለተወሰኑ ሰወች መሞቱ ግቡን አልመታም ማለት ነው::

በውሱን ቤዘወት መሰረት የክርስቶስ ትንሳኤ አላማ ቤትኛውም መሰፈርት ግቡን አይመታም:: የክርስትና አስኳል አላማ የእርሱና የምእመናን ትንሳኤ ስለሆነ በካልቪኒዝም መሰረት ክርስትና ከንቱ ነው:: ክርስቶስን ማመናችንም ከንቱ ነው ማለት ነው::

2.5 የኢየሱስ ሞት ማንንም አይጠቅምም::

በውሱን ቤዘወት መሰረት የኢየሱስ ቤዘወት የተወሰኑ ለሚባሉት እንኳ የሚጠቅም ሁኖ አናገኘውም የዚህ ምክንያቱ ደግሞ እግዚአብሔር ከአለም አስቀድሞ ለጽድቅ የወሰናቸው ሰወች አሉ እነዚህን ሰወች ደግሞ የኢየሱስ ሞት ሳይሆን የእግዚአብሔር ቅድመ ውሳኔ ከክርስቶስ ሞት በፊት ስላጸደቃቸው እና በቁጥር እና በማንነት ስለሚያውቃቸው የክርስቶስ

ሞት ሊያመጣው የሚችለው ለውጥ አይኖርም::

2.6 በሰው እና በእግዚአብሔር መካከል ፍቅር አይኖርም ነበር

ፍቅር የሚጸናው በሁለት አካላት አጸፋ ነው ሙሽራው ሙሽሪትን: ሙሽሪትም ሙሽራውን በመውደድ የተመሰረተ ነው:: አንዱ ብቻ ወዶ ሁለተኛው ካልወደደ ፍቅር አደለም:: ፍቅር በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ነው:: እንግዲህ በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ያለውም ፍቅር ይህን ይመስላል:: 1ኛ ዮሐ 4:19 እርሱ አስቀድሞ.ወደደን ከዛም እኛ እንወደዋለን:: ነገር ግን አንድ ሰው እግዚአብሔር አስቀድሞ ወሰኖ ቢቤዠው እንዴት ይህ ፍቅር እንዴት ይባላል? የተወሰኑት ሰወች ያለመውደድ ምርጫ የላቸውም ማለት ነው:: ምርጫ ከሌላቸው ደግሞ ሲጀመር አፍቅረዋል ማለት እንችልም ፍቅር የምርጫ ጉዳይ ነው እንጅ:: ዮሐንስ ደግሞ አስቀድሞ እሱ ወዶናል ስለሚል ቀድመን አንወደውም ነበር ኋላ ፍቅሩን አይተን ወደነዋል ማለት ነው ይህ ነው ፍቅር(በምርጫ):: ተገድጀ እኔ ሳልፈልገው ሃሳቤ ተቀይሮ እንድወደው ከተደረገኩ ግን ከሰውነት ወደ ሰሜት አልባ(የመጥላትና የመውደድ ምርጫየና ፍላጎቴ ተነጥቆ) በመለወጤ ሮቦት ሁኛለሁ የሮቦት(ፕሮግራም የተደረገውን ብቻ ሚያረግ) ፍቅር ደግሞ ተሰፋ የለበትም:: ምክንያቱም እርግጡ ሁኗልና:: ፍቅር ደግሞ ሁሉን ተሰፋ ያደርጋል 1 ቆሮ 13:7

እንግዲ ከላይ ባየናቸው አመክንዮታዊ እሳቤወች መሰረት ክርስትና መሰረቶቹ በሙሉ ይናዳሉ ማለት በውሱን ቤዞወት የሚጸና የእምነት ክፍል የለም:: ሁሉም ፈርሰዋል::

"መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?"

በመጽሐፍ ቅዱስ በአንድ ሰፍራ እንኳ ክርስቶስ ለተወሰኑት ብቻ ቤዛነት ከፈለ ሚል በአንድ ሰፍራ በአንድ ጥቅስ እንኳ አናገኝም:: በተቃራኒው ግን በቅዱሱ መጽሐፍ ክርስቶስ ስለ ሁሉ እንደሞተ ይናገራል:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዳውም በማያሻማ ሁኔታ እንዲህ ያለውን ትምህርት ድምጥማጡን ያወጣዋል:: ለዚህ ይመስለኛል ብዙ ካልቪኒስቶች "ባለ 4 ነጥብ ካልቪናውያን ብለው ይህን ነጥብ የጣሉት:: በእርግጥ ይህ ባለ አራት ነጥብ ካልቪናዊነት በባለ 5 ነጥብ ካልቪናውያን ዘንድ "ቅዱስ ኢተደጋጋፊነት" ተብሎ ተተችቷል:: ወደምጽሐፍ ቅዱስ ሰናልፍ::

1.ኛ "ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ ስለ ሰው ሁሉ ሞትን ይቀምስ ዘንድ፥ ከመላእክት ይልቅ በጥቂት አንሶ የነበረውን ኢየሱስን ከሞት መከራ የተነሣ የክብርና የምስጋናን ዘውድ ተጭኖ እናየዋለን።"
— ዕብራውያን 2፥9

በዚህ ክፍል ሐዋርያው "ስለሰው ሁሉ ሞትን ይቀምስ ዘንድ" በማለት ሞቱ ያለምንም ልዩነት ለሰው ሁሉ የተሰጠ ስጦታ እንጅ ለጥቂቶች ብቻ ወይንም አስቀድመው ለተወሰኑት ሁሉ አይልም:: ኢየሱስ ከመላእክት አንሶ ሞትን የቀመሰው ለሰው ዘር ነው ብሎ ሐዋርያው ጳውሎስ በግልጽ ባብራራበት ሁኔታ እኛ የራሳችንን ፍልስፍና በመጨመር ለጥቂቶች ነው ማለት ከላይ ካየናቸው የክርስትና መሰረቶች በተጨማሪ እግዚአብሔርንና ቃሉን ምስክሮቹንም ሐሰተኛ በማለት ለስህተት መዳረግ ነው::

2.ኛ "ይህን ስለቆረጥን የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናልና፤ አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ፤ እንግዲያስ ሁሉ ሞቱ፤"
— 2ኛ ቆሮ 5፥14

ክርስቶስ ሲሞት ይዞት የሞተው የሰው ልጆችን ህይወት ነው ምክንያቱም ሁሉ ሞተዋልና ያንን ሞታቸውን ስለተሸከመ:: ክርስቶስ የሁላችንን ሞት እንደሞተ ትንሳኤው ደግሞ በእርሱ በማመን ይቆጠርልናል ስለዚህም እኛ በክርስቶስ መኖር እንችላለን:: እንግዲህ በጳውሎስ ትምህርት መሰረት ክርስቶስ የሞተው ስለሁሉ ነው: እንጅ ስለተወሰኑ ምርጦች ብቻ ነው የሚል ምንማ አይነት ክፍልም ሆነ ቦታ አናገኝም::

3.ኛ "እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፥ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት

እንዲሽር፥ ይኸውም ዲያብሎስ ነው፥ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ፥ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ።”
— ዕብራውያን 2፥14-15

ክርስቶስ ማንን ነጻ እንዲያወጣ ነው በስጋና በደም የተካፈለው ብለን ሐዋርያውን ብንጠይቀው ምን የሚመልስ ይመስላችኋል? “በሕይወታቸው ሁሉ ስለሞት ፍርሃት በባርነት የታሰሩትን ሁሉ” ይለናል:: ታዲያ ማን ነበር ስለሞት ፍርሐት በባርነት ያልተያዘ? ሃጢያትን ያልሰራ ነበርን? ስለሞትስ ፍርሃታ ያልታሰሩ ክሌሉ እንኪያስ ክርስቶስ ያለ ልዩነት ስለሁሉ ሙቷል:: ከዚህ ማምለጥ የምንችልበት መንገድ የለም ምክንያቱም ክርስቶስ ስለሁሉ ሞቷል ምክንያቱ ደግሞ ሃጢያታቸው ነው ካለን ያልሞተላቸው አሉ ለማለት ሃጢያት የሌለባቸው ስለሞትም ፍርሐት የሌለባቸው መሆናቸው ግድ ነው:: እንዲያስ ከሆነ ክርስቶስ ለማንም አልሞተም:: እኒህም አሰቀድመው በእግዚአብሔር ተመርጠዋልና:: እነዛም በሂውታቸው ጻድቅ ናቸውና:: ነገር ግን ለሁሉም ስለሚያስፈልግ “ሁሉ” ብሎ አሰመረ::

4ኛ. “እርሱም የኃጢአታችን ማስተሰሪያ ነው፥ ለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ኃጢአት እንጂ።”
— 1ኛ ዮሐንስ 2፥2

ሐዋርያው የኃጢአታችን ማስተሰረያ ነው ካለ በኋላ በቃ ለዳንነው ብቻ ነው አበቃ አለቀ አላለም ለአለም ሁሉ ነው እንጀ በማለት ይጨምራል ለተወሰኑት ብቻ ነው የሚለውን ትምህርት ፈጽሞ ሚደመሰስ ትምህርት ነው:: ክርስቶስ ለተወሰኑት ብቻ ሞተ ሚለው ትምህርት ይቀብረዋል “ለኛ ብቻ አደለም” በማለቱ:: እንኪያስ ለአለም ሁሉ መሆኑን እንመን ወንጌልንም ስንሰብክ ለሁሉም መሆኑን በአንቅአዶ ህሊና ይህ የአብ ፍቅር ለአለም ሁሉ የተገለጠ መሆኑን በአንዳች አንጠራጠር:: ለእኛ ብቻ አደለምና:: ለአለም ሁሉ እንጅ::

5ኛ. “በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።”
— ዮሐንስ 3፥16

እግዚአብሔር አለሙን ብሎ በአንደ ቃል ዘጋው:: አለሙን(THE WORLD) ብሎ ይህን አለም አመለከተ ሌላ አለምን እንዳንል የላከው የሰው ልጆችን መሆኑን ለማመልከት “አለምን” አለ ጆን ማካርተር ይህንን ቃል ሰውን ሁሉመሆኑን መካድ አልቻለምና ይህን ሲያብራራ “ሰወችን ሁሉ ሕይወትን እንዲካፈሉ ይጋብዛልና ስለዚህም ያላመኑትን ምክንያት ሁሉ በዚህ ያጠፋል”(Love of God ገጽ 195) ብሏል ነገር ግን ጆን አሰቀድሞ የወሰናቸው ብቻ እንደሚያድን እያመነ እንዴት ይህን ሊል ቻለ?(እንግዳ ነው) እኔ እሱን ብሆን “የእኛን ውሰን ቤዘወት አማኞችን ምክንያት በዚህ ያጠፋል” ብየ እተረጉም ነበር::

6ኛ “እንግዲህ በአንድ በደል ምክንያት ፍርድ ለኵነኔ ወደ ሰው ሁሉ እንደ መጣ፥ እንዲሁም በአንድ ጽድቅ ምክንያት ስጦታው ሕይወትን ለማጽደቅ ወደ ሰው ሁሉ መጣ።”
— ሮሜ 5፥18

የእግዚአብሔር ስጦታ ይህ ነው በደል ወደ ሰው ሁሉ መጥቷል:: ያልበደለ ማንም የለም:: ሁሉም ለበደል ተላልፎ ተሰጥቷል በዚህም ሰው ሁሉ ወደ ኩነኔ ገባ:: ስለዚህም ሰውን ሁሉ ደግሞ ለማጽደቅ ደግሞ የእግዚአብሔር ስጦታ ክርስቶስ ነበር:: እንግዲህ ኩነኔ ያለውም ሕይወትን ለማጽደቅ ያለውም ሰው ሁሉ ማለቱን ልብ እንበል:: እንጅ ከሰው ደግሞ ለተመረጡት ብቻ ስጦታው መጣ አላለም:: ሰው ሁሉ በማለት ዘጋው እንጅ:: እንግዲህ ማንም የተጠማ ቢኖር(ያለተጠማ የለም) ወደዚህ የአብ ስጦታ ይምጣ:እንዲያው በነጻም በእምነት ብቻም ይውሰድ::

7ኛ. "አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥

እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ፥ ይህም በገዛ ዘመኑ ምስክርነቱ ነበረ፤"
1ኛ ጢሞቴዎስ 2፥5-6

“በእግዚአብሔርና በሰው” መካከል አለ እንጅ በእግዚአብሔርና በተመረጡ ሰዎች መካከል አላለም:: ቀጥሎም ራሱን ለሰው ሁሉ ሰጠ በማለት ስጦታው ለሰው ያለውን ደግሞ ሁሉ በማለት አጸናው:: ከሰዎች መካከል ቤዛነቱ ያልደረሰው ማንም የለምና ሁሉም የቤዛነቱ ተጠሪዎች ናቸው:: ቤዛነት ያልተሰጠው ከሰው ወገን አንድ እንኳ የለም:: ሁሉ በማለት የተዘጋውን: የተወሰኑ በማለት ደግሞ ማንም ቃሉን አይሻር ይህ ክርስቶስን ቤዛነቱን ማሳነስ ደሙንም ማክፋፋት ነውና::

“ነገር ግን ሐሰተኞች ነቢያት ደግሞ በሕዝቡ መካከል ነበሩ እንዲሁም በመካከላችሁ ደግሞ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ይሆናሉ፤ እነርሱም የዋጃቸውን ጌታ እንኳ ክደው የሚፈጥንን ጥፋት በራሳቸው ላይ እየሳቡ የሚያጠፋ ኑፋቄን አሾልከው ያገባሉ፤”
— 2ኛ ጴጥሮስ 2፥1

ማንም በክርስቶስ ያልተዋጀ የለም ሁሉም ተዋጅቷል: ሐሰተኛ ነብያትና ሐሰተኛ አስተማሪዎች እንኳ ተዋጅተው ከሆነ ማን ነው ክርስቶስ ለተወሰኑት ብቻ ነው የሞተው ብሎ ሚደፍረው? እኒህ ሐሰተኛ ነብያትና ሐሰተኛ አስተማሪዎች ከተመረጡት ናቸው ማለት ነው? እንኪያስ ከኩርንችት የወይን ፍሬ ይለቀማልን? እንዴትስ እነዚህ የክርስቶስ ቤዛነት ለእነርሱ ነው ተባለ? ሐሰተኞች እንኳ ሁነው ሐዋርያው ክርስቶስ ለእነርሱም ቤዛነት መመቱን አልካደም:: ሞቱ ስለኛ ስለ ሃጢያተኞች ነውና:: ይህም ሰውን ሁሉ ይልቁንም የሚያምኑትን(FAITH THAT WORKS WITH LOVE IS THE CONDITION) የሚያድን ህያው አምላክ ልጁን ሰጥቶናል “ይህን ለማግኘት እንደክማለንና፥ ስለዚህም እንሰደባለን፤ ይህም ሰውን ሁሉ ይልቁንም የሚያምኑትን በሚያድን በሕያው አምላክ ተስፋ ስለምናደርግ ነው።”
— 1ኛ ጢሞቴዎስ 4፥10

ተጨማሪ ከጸሎት ጋር ማንሰላሰያወች::

“የእግዚአብሔር እንጀራ ከሰማይ የሚወርድ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ ነውና አላቸው።”
— ዮሐንስ 6፥33
“ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው(anyone) ከዚህ እንጀራ ቢበላ(If...eats of) ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።”
— ዮሐንስ 6፥51

በእኔ የሚያምን ሁሉ በጨለማ እንዳይኖር እኔ ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቻለሁ። ዓለምን ላድን እንጂ በዓለም ልፈርድ አልመጣሁምና ቃሌን ሰምቶ የማይጠብቀው ቢኖር የምፈርድበት እኔ አይደለሁም።
-- ዮሐንድ 12፥46-47

“ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።”
— ሮሜ 5፥8
“እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደ ሆነ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ።”
— ዮሐንስ 12፥32

“ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተስፋ ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሣል።”
— 2ኛ ጴጥሮስ 3፥9

“ካልቪናዊነት ወይስ ክርስቶሳዊነት?”
Limited Atonement(ውሱን ቤዘወት)

በዴቭ ሃንትና በ C. H. Supergeon አባባል ልጀምር:: አንድ ከካልቪናዊና አንድ ከአርሜነሳዊ (ፍትሃዊ ክፍፍል ;-) )
ዴቭ ሀንት እንዲህ ብለው ካልቪናውያንን ይሞግታሉ "የቱጋ ይሆን በቅዱሳት መጻህፍት ክርስቶስ ከሞቱ ጥቅም ለማያገኙት አይሞቱም ሚለው?" የትም! ነገር ግን ይህ ልቦለድ የ"ውሱን ቤዛወት አስተምህሮ መሰረት ነው" (TULIP ገጽ 126)

C. H. Supergeon "ሃጢያተኞችን 'ንሰሃ መግባት እና ማመን የእናንተ ተግባር አደለም' ብሎ እንደሚሰብክ ሰባኪ ከዛ ደግሞ በትእቢት ራሱን 'የወንጌሉ አገልጋይ' ብሎ ከሚጠራ በላይ በሰይጣን እጅ የተዘጋጀ መሳሪያ ማሰብ ያዳግተኛል" (New Park Street Pulpit Vol 6 page 28)

ይህንን ክፍል መልስ ለካልቪናውያን ውሱን ቤዛወት ያልኩበት ወይንም "ካልቪናውያን ለሚጠቅሱት ጥቅስ መልስ" ያላልኩበት በቸኛው ምክንያት ካልቪናውያን ለዚህ ክፍል ምንም አይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅስ ሰለ ሌላቸው ነው:: ምንም "ሚጠቅሱት የለም ወይ?" ከተባለ መልሴ "አለ"ነው፤ ታዲያ ምን ከዚ በፊቱ ምን ሚለየው ነገር አለ ቢባል መልሱ በዚህ ክፍል ላይ እንደሌላው ሃሳቡን ብቻ ከአውዱ በማውጣት ሳይሆን የአመክንዮ እና የቃላት ጨዋት ሰለሚጫወቱ ነው ሰለዚህ በዚህ ክፍል ጥቅሶቻቸውን ሳይሆን(ጥቅስ ሰለሌላቸው) የቃላት ጨዋታቸውን ነው ምናፈርሰው:: ከሚጫወቱባ ቸው ቃላት ደግሞ "ብዙወች" እና "ሁሉ" ሲሆኑ ሌላው ደግሞ የቃላት ጭማሪወች ናቸው::

1. የአመክንዮ ጨዋታ

በዚህ ጨዋታቸው ላይ እንደተረዳሁት ካልቪናውያን መዳንን አጥበው የሚያዩት ይመስለኛል: መዳን ለነሱ የአንድ ቀን ክስተት ይመስላል:: ለምን ሚለውን እንመልከት::

ማይክል ሆርተን "ክርስቶስ ለሁሉ ከሞተ ነገር ግን ሁሉም ካልዳኑ ክርስቶስ ማንንም አላዳነም ማለት ነው... ክርስቶስ በገሃነም ለሚጣሉትም ከሞተማ ይህ ድካሙ በትክክል የማዳን ስራ አይባልም ምንም አይነት እውነተኛ የማዳን ሃይል በደሙ የለም እንዳውም፤ የፍጥረታት ፍቃድ ላይ ነው ሃይሉ ያለ ሚመሰለው" (Putting Amaizing Back Into Grace 89)
እንደ ማይክል አስተሳሰብ ክርስቶስ ላልዳኑት አልሞተም ምክንያቱም ክርስቶስ የሞተላቸው በጭራሽ ገሃነም ሊገቡ አይገባም አለዚያ ግን የክርስቶስ ሞት ገሃነም የሚገቡትን ማዳን ካልቻለ ማንንም አያድንም ነው::

ሔርማን ሃንኮ "ክርስቶስ ለሁሉ ከሞተ ነገር ግን ሁሉ ካልዳኑ የክርስቶስ መሰቀል ከንቱ ነው: ሕማማቱም ፌዝ ነው"(Gods Everlasting Covenant of grace page 15)
እን ሔርማን ደግሞ ክርስቶስ ለሁሉ ሞተ ብሎ ማሰብ ፌዝ ነው ይላል(1 ቆሮ 1:18 ን አስታወሰኝ)

W. J. Seaton "ክርስቶስ የሁሉን የሃጢያትን እዳ ከከፈለ፣ ካዳነ: ከተቤዠ: ህይወቱን ከሰጠ ሁሉ ሰው ድኗል::"(the five points of calvinism page 15)
ሲያተን ትንሽ ብልጥ ለመሆን ሞክሯል እዚጋ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሌለን ቅመም እንደሚጨምር ሁሉ የአለም አቀፍ ቤዛወት አማኞችን ለመሸወድ በራሱ የሎጅክ እሳቤወች መካከል "ካዳነ" ምትል ያልተመጠነች ቅመም ይጨምራል:: ማን ሞኝ ነው አዳነ ብሎ አላዳነም ሚል? የክርስቶስ መሰቀል ሁሉን አድኗል ብሎ ሚያምን የለም'ኮ: ክርክሩ ያለው ክርስቶስ ሁሉን ለማዳን ወይ የሞተው የሚል እንጅ "ክርስቶስ ሁሉን አድኗል አላዳነም?" ሚል አደለም"

ለዚህ ጨዋታ መልስ ለመስጠት በቀላሉ አስተሳሰቡን ምንድን ነው ሚለውን ማየት ያስፈልጋል ይህ ኢ-አመክንዮታዊ አስተሳሰብ ሁለት ነው:: "ነገረ_ድህነት" የመሰቀሉ ስራ ብቻ ነው "መዳንም የሃጢያት ሰርየት ብቻ ነው" ብሎ ከማሰብና ይህ "ኢየሱስ EFFECTIVELY" በመሰቀሉ የሃጢያተኞችን ሃጢያት ደምስሷል ብሎ ከማሰብ ነው የሚመነጭ :: እንዲህ ያለ ነገር ደግሞ ፈጽሞ በመጽሐፍ ቅዱስ የለም:: ሲጀመር ነገረ ድህነት የሚጀምረው ከዘላለም ከአለም አስቀድሞ እግዚአብሔር አምላክ በቅድመ እውቀቱ ሰው እንደሚወድቅ ሰለሚያውቅ በፈቃዱ ምክር ያዘጋጀልን አብርሐምን በመጥራት መሲሁ የሚወለድበትን ህዝብ በመምራት ህግ በመስጠት በመንከባከብ የቀጠለ መሲሁ ደግሞ ከውልደት እስከ ሞጽአት

የሚፈጽመው “የነብይነት: የመሰዋእት በግነት: የክህነት: የንግሰና” ተግባር እንጅ የአንድ ቀን የመስቀሉ ስራ ብቻ አደለም:: ስለዚህ ይህ ስፍራ እንደው በደምዳሜው ክርስቶስ ከሞተላቸውማ ድነዋል የምንለው አደለም:: ለመዳን ከመስቀሉ በተጨማሪ: ትንሳኤው በሰማያዊቱ መቅደስ የክህነት አገልግሎቱ: እንዲሁም ጠበቃነቱ: ጭምር እንጅ እንዲሁ ከመሬት ተነስተን መስቀሉ ላይ ብቻ ምንደፈድፈው ነገር አደለም:: ይህ ከላይ ያብራራናቸው የአምላክ ብቻ ስራወች ሲሆኑ ከእኛ ደግሞ አንድ ሚጠበቅ ነገር አለ: ይህም “እምነት” ይባላል እኛ ለመዳን በማመን ድርሻችንን መወጣት አለብን አለዚያ ግን ያለ ፍላጎታችን (በክፍል አራት ምናየው አሰገዳጅ ጸጋ) አደለም:: የሃጢያት ሰርየቱም ደግሞ ክርስቶስ እንደሞተ ሳይሆን በማመን በምንቀበለው የደሙ ማህተም የሚሰጠ ፍጹም የአምላክ በጎነት ነው:: በሐዋርያት ስራ ላይ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ሰብከቱን በጨረ ጊዜ ተሰባኪወቹ “ልባቸው ተነካ” ስለዚህም መጥተው “ወንድሞች ሆይ ምን እናድርግ?” አሏቸው ጴጥሮስም:- ንስሃ ግቡ ሃጢያታችሁ ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ: የመንፈስ ቅዱስንም ሰጦታ ትቀበላላችሁ::” አላቸው:: እዚህግ ጴጥሮስ “ንስሃ ግቡ:” “ሃጢያታችሁ ይሰረይ ዘንድ” ያላቸውን ልብ ብላችሁ ተመልከቱ:: ኢየሱስ ሃጢያታችሁን ሰላስተሰረላችሁ ሃጢያታችሁ ተሰርዮላችኋል አላላቸውም:: እንዲሁም ደግሞ በቃ ችግር የለም የተመረጣችሁ ሰለሆናችሁ አታሰቡ አላላቸውም “ንሰሃ ግቡ” አላቸው እንጅ:: ተመልከት ኢየሱስ የሁላችንን ሃጢያት በመሰቀል ሞትን ቀምሷል ነገር ግን ይህን ሰርየት ለመቀበል የተመረጠ መሆን ነደለም:: ቅድመ ሁኔታ አለው እርሱም አምኖ “ንስሃ መግባት” ነው::

ካልቪኒስቱ Arthur W. Pink “የአዳኙ መግቦት ብቻውን በቂ አደለም: ተቀባይነት ደግሞ ሊያገኝ ይገባል፤ በደሙ እምነት ሊኖር ይገባል(ሮሜ 3:25) እምነት ደግሞ የግል ነው እምነትን መለማመድ ይኖርብኛል” (Gleaning in Exodus page 84) በማለት እርግጡን መሰክሯል::

የሃጢያት ሰርየት ብቻም ደግሞ መዳን አደለም:: ከዛ ደግሞ በቅድሰና የመኖር በእለት ተእለት ሂወታችን በንሰሃ በመመላለስ (1ኛ ዮሐ 1:7-10) በትንሳኤ የሚፈጸም እንጅ የአንድ ቀን ቅጽበታዊ አደለችም:: አሁን ያለን መዳን “የተሰፋ መዳን”(በክርስቶስ ከጸናን ለማግኘት እርግጡ የታወቀ) ነው::

ያዘጋጁትን ጦር ራሳቸውን ሲወጋ

የሆነው ሁኖ የሲያተን ሙግት ደግሞ “ለሁሉ ሙቶ ሁሉ ካልዳነ መሰቀሉ ከንቱ ነው” ያለው ምናልባት እሱ FRAME በተደረገበት ካልቪኒስቲክ WORLD VIEW እይቶት እንጅ በጭራሽ ሃሳቡ ልክ አደለም ሲጀመር ይህ ሃሳብ ከላይ የመለሰነው የክርስቶስ መሰቀል EFFECTIVELY ሃጢያትን አስተሰርየዋል ብሎ ከሚያምነው በመነሳቱ የተነሳ ቢሆንም ይህ ሃሳብ ወደራሱ መልሶ ቢጠየቅ መሰቀሉ ከንቱ የሚያደርገው ክርስቶስ የሞተው ለተመረጡት ብቻ ነው ሚለው ትምህርት ነው:: ምክንያቴን ላቅርብ: ከዛበ ፊት ግን ሰፕራውልና ጆን ፓይፐር ያሉትን እንይ

R. C. Sproul “የክርስቶስ የቤዛነት ዋጋ የአለምን ሁሉ ሃጢያት ለመሸፈን በቂ ነው::” (Grace Unknown ገጽ 165)

John Piper 1 ጢሞ 4:10 ሲያብራራ “የክርስቶስ ሞት የእግዚአብሔርን ሃጢያትን በመጥላት ያለውን ጽድቁን : እርሱም ጽድቁን ሳይበድል ምህረት አለምን በምህረት መቀበል እንደሚች ል ያሳየ ነው:: በዚህ ሃሳብ መሰረት ክርስቶስ ለሁሉም ሙቷል: ነገር ግን ነገር ግን በተለየ ለሚያምኑት አዳኝ ነው፤ በተመሳሳይ ሃሳብ ደግሞ ክርስቶስ ለሁሉ አልሞተም::” (TULIP: what we believe about the five points of Calvinism: page 16-17)

እንደ ሰፕራውል ከሆነ የክርስቶስ ሞት ለአለም ሃጢያት በቂ ነው: ታዲያ ለምን ይሆን በቂነቱ ሁኖ ሳለ ከዋጋው በታች ወርዶ ለጥቂቶች ብቻ የዋለው? እግዚአብሔር ሰው ሁሉ እንዲድን ሰላልወድደ ነውን? አደለም..

“ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና

ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው።”
— 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፥3-4

ሃጢያተኛው እንዲሞት ፈቅዶ ነውን? አደለም

“በውኑ ኃጢአተኛ ይሞት ዘንድ እፈቅዳለሁን? ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ ከመንገዱስ ይመለስና በሕይወት ይኖር ዘንድ አይደለምን?”
— ሕዝቅኤል 18፥23
ታዲያ ለአለም ሁሉ በቂ የሆነ ደምን ለጥቂቶች ብቻ ማድረግ ማባከንና ከንቱ ማድረግ አይደለምን?

ነገር ግን የክርስቶስ የመስቀሉ አላማ እንጅ ብዛት አደለም መለኪያው:: አላማው ምንድን ነው ያልን እንደሆነ ቃሉ እንዲህ ይለናል ...
“በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።”
— ዮሐንስ 3፥16
ስለዚህ መለኪያው አላማው ከሆነ ዘንዳ ማለት የሚገባን “በእርሱ ያመኑ(አስቀድመው የተወሰኑት ስለማይል) የዘላለም ህይወት አግኝተዋልን?” ነው አው መስቀሉንም ከንቱ ሆነ ምንለው ይህ አላማ ግቡን ያልመታ ከሆነ ነው::

2. የቃላት ጨዋታ
2.1 “ብዙ”
ካልቪናውያን ይችን የቃላት ጨዋታ ሲጀምሩ ብዙ ማለት ሁሉ ማለት ነው ወይ? በማለት ቅድመ ሁኔታ ያበጁልሃል: በወጥመዳቸው ከገባህ “አደለም ትላለህ” አመክንዮታዊ አሳቢ ከሆንክም ወይ “እንጻራዊ ነው” ትላለህ ወይ “እውዱ ይወስነዋል” ትላለህ::
ወደ ቁም ነገራችን ስንመለስ ከቅዱስ ቃሉ ጫዋታውን ሚጀምሩበትን ከማየታችን በፊት የካልቪናውያንን ክልኤ-መድሎታዊነት(DOUBLE-STANDARD እንሂድ:: አንድን ካልቪናዊ ሂደህ በፍጻሜ ዘመን ስንት ሰው ይነሳል ብትለው ሁሉም ይነሳሉ: ይልሃል እንግዲያው በዚህ የቃል ቀመራቸው መሰረት ትንቢተ ዳንኤል ላይ

“በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉቱ ብዙዎች ይነቃሉ፤ እኩሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት፥ እኩሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም ጉስቍልና።”
— ዳንኤል 12፥2

ስለሚል ብዙወች ሚለውን አይ ሁሉ አይነሱም ማለት ነዋ ብለህ ውይይቱን በእጅህ ታስገባለህ:: ክልኤ-መድሎታዊነት ጣጣው ብዙነው::
የቃላት ጨዋታ ወደሚጫወቱበት ቅዱስ ቃሉ ሰናልፍ በቀደምትነት ሚጠቀሰው
ኢሳይያስ 53:1-11 “የሰማነውን ነገር ማን አምኖአል? የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገልጦአል? በፊቱ እንደ ቡቃያ ከደረቅም መሬት እንደ ሥር አደገአል፤ መልክና ውበት የለውም፥ ባየነውም ጊዜ እንወድደው ዘንድ ደም ግባት የለውም። የተናቀ ከሰውም የተጠላ፥ የሕማም ሰው ደዌንም የሚያውቅ ነው፤ ሰውም ፊቱን እንደሚሰውርበት የተናቀ ነው፥ እኛም አላከበርነውም። በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸክሞአል፤ እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው። እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን። እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ። ተጨነቀ ተሣቀየም አፉንም አልከፈተም፤ ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት፥ በሸላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ፥ እንዲሁ አፉን አልከፈተም። በማስጨነቅና በፍርድ ተወሰደ፤ ስለ ሕዝቤ ኃጢአት ተመትቶ ከሕያዋን ምድር እንደ ተወገደ ከትውልዱ ማን አስተዋለ?... ከነፍሱ ድካም ብርሃን ያያል ደስም ይለዋል፤ ጻድቅ ባሪያዬም በእውቀቱ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል፥ ኃጢአታቸውን ይሸከማል።” ሚለው ነው::

በዚህ ቃል ላይ ሚጫወቱት የቃላት ጭማሪና የቃል ጨዋታ ነው:: ይህንን ለመቃወም እንዲመቸኝ እዚሁ

በፌስቡክ መንደር ትንሽ ለያዥ ለገናዥ ያስቸገረ ካልቪናዊ ከሁለት አመት በፊት ያስቀመጠውን ትንታኔ ላስነብባችሁ ::
ልጁ እንደሚከተለው ነው ክፍሉን ያብራራው::

“ኢሳይያስ 53 የምወደው የመሲሁ ምዕራፍ በመባል የምናውቀው ሲሆን ይህ ክፍል መሲሁ መጥቶ ለማን እንደሚሞት ፍንትው አድርጎ ያሳያል::
ቁ.4 "በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸክሞአል እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው።" እዚህ ላይ በርግጥ ስለሆኑ ስለተወሰኑ አካላት ደዌ ስለመቀበሉ እና ህመም መታመሙን ቀጥታ አያሳይም:: ነገር ግን "ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸክሞአል" ሲባል የማንን? የሚል ጥያቄ ያስነዳል:: የማንን ተሸከመ? እሰቲ እንቀጥል:-

ቁ.6 "እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።" ያላል:: ዕኛ ሁላችን" እና "የሁላችንን በደል" የሚል ቃል አሁን አለ:: እነዚህ "እኛ" እና "ሁላችን" የተባሉት እነማን ናቸው? እንቀጥል:-

ቁ.8 "በማስጨነቅና በፍርድ ተወሰደ ስለ ሕዝቤ ኃጢአት ተመትቶ ከሕያዋን ምድር እንደ ተወገደ ከትውልዱ ማን አሰተዋለ?" ይላል:: በደንብ አስተውሉ ምን እንደሚል:- "ስለ ህዝቤ ሃጥያት" ኢየሱስ ሞተ ይላል:: የሞተው ስለሆነ ህዝብ ነው::

ቁ.11 "ከነፍሱ ድካም ብርሃን ያያል ደስም ይለዋል ጻድቅ ባሪያዬም በእውቀቱ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል፥ ኃጢአታቸውን ይሸከማል።" ታላቁ ሚስጥር እዚህ ውስጥ አለ:: ቁ. 11 ላይ ከላይ ጀምሮ የተደገሙ ሃሳቦች እና ፍሰቶች አሉ እነዚህም "እኛ ሁላችን" "የሁላችን በደል" እና እዚህ ክፍል ላይ ደግሞ ኢየሱስ ሲሞት "ብዙዎች ይጸድቃሉ" ሃጥያጥያታቸውንም የሚሸከመው "የብዙዎችን" ነው:: እነዚህ ብዙዎች ከላይ "ሁላችን" የተባሉት ናቸው:: እንግዲ ቃሉ ኢየሱስ የሚሞተው ለብዙዎች እንጂ ለሁሉም አይደለም ማለት ነው:: ምክኒያቱም በብዙ እና በሁሉም መካከል ልዩነት ሰላለ::

ቁ.12 "ስለዚህም እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል፥ ከኃያላንም ጋር ምርኮን ይከፋፈላል ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና፥ ከዓመፀኞችም ጋር ተቈጥሮአልና እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ፥ ስለ ዓመፀኞችም ማለደ።" ይገርማል:- የሚሞተው ለብዞዎች ነው: ሐጥያታቸውን የሚሸከመው የብዞዎችን ነው: የሚወርሰው ብዞዎቹን ነውየሚማልደውም ለብዞዎች ነው:: ለሁሉም አይደለም::

ኢሳይያስ 53 በፍጹም ኢየሱስ ለዓለም ህዝብ ሁሉ ይሞታል የሚል ፍንጭ አይሰጥም:: ኢየሱስ በራሱ አንደበት ምን አለ? ማቴ 26:27-28 "ጽዋንም አንሥቶ አመሰግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ፦ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ #ስለ_ብዞዎች_ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።" ስለ ስንቶች ሐጥያት? ለሁሉም ሳይሆን ለብዞዎች ሐጥያት ነው::”

በዚህ ልጅ ማብራሪያ መሰረት ባጭሩ አኛ ያለው “የተመረጡትን ብቻ” ወይም “ሕዝቡን ብቻ” ወይም “እኛን ብቻ” የሚል ነው:: “ስለህዝቤ” ምትለዋን ቃል በማንጠልጠል ኢየሱስ የሞተው ሰለ ሆነ ህዝብ ነው አለ: ባልሳሳት ሰለተመረጡት ብቻ ማለቱ መሰለኝ DEFINE ሰላላረገው ይህ ነው ማለት አልችልም ግን POSSIBILITY ው እሱ ብቻ ነው ሊሆን ሚችለው:: ለዚህ ሁለት POSSIBLE መልሶች እሰጣለሁ አንደኛው ሕዝቡ የተባሉት እስራኤላውያን መሆናቸው ነው በትንቢተ ኢሳያስ መሰረት ሁለት ሕዝቦች ብቻ ህዝቤ ተብለው ተጠርተዋል አንደኛውና ሚታወቀው እስራኤላውያን ሲሆኑ::(ኢሳ 1:3) ሁለተኛው ደግሞ ግብጽ ነው::(ኢሳ 19:24) ነገር ግን “ሕዝቡ” ምተለው ቃል ለእስራኤል ብቻ ነው የዋለችው:: ስለዚህ በዚህ ክፍል “እኛ” ስለሚል እስራኤላውያንን እንደሆነ መመልከት እንችላለን:: ታዲያ ብዘወች ማለቱ ምን ሊሆን ይችላል? ይህ አገላለጽ “የሁሉን” ብዛት ማጉላቱ ነው ሁሉ ብሎ ብዙ ቢል ሁሉ ብዙ መሆናቸውን ሚያሳይ ነው:: ብዙ ብሎ ሁሉን ቢያስከትል ብዙ የተባሉትን በጠቃላላ ማመላከቱ ነው:: እንጅ ብዙ ና ሁሉ ለአንድ አገባብ አይውሉም ብሎ ማሰብ ቂልነት ነው ውለው እያየን አደል?

ሁለተኛው POSSIBLE መልስ ደግሞ ያልተባለን እንደ ተባለ አድርጎ ማቅረብ ይመስላል የሚወራላቸው ሰዎች ሁሉ ብዙ ከሆኑ ከብዛኣት አንጻር ሲታይ “ብዙ” መባል እንደሚቻል ካየን “ለእነዚህ ለብዙዎች ብቻ ነው ወይ የሞተው?” ብንል ፈጽሞ ስህተት ነው:: ለብዙዎች ሞተ ተብሎ ተገለጸ ማለት ሌሎችን EXCLUDE ያደርጋል ማለት አይደለም:: ለምሳሌ ጌታ ኢየሱስ “ከብዙ ድንቢጦች እናንተ ትበልጣላችሁ” ማቴ 10:31 ብሏል ታዲያ ከብዙ ድንቢጦች ስላለ የተወሰኑ ድንጦችን ቆጥሮ ከነዚህ ትበልጣላችሁ ከሌሎች ግን አትበልጡም ብሎ EXCLUDE እየደረገ ነውን? አይለም:: ከሁሉም ድንቢጦች እንበልጣለን እንጂ:: እንግዲህ ለብዙዎች ሞተ ማለት ሌላውን ማግለል ሚሆንበት ምንም መንገድ የለም:: እንግዲህ ካልቪናውያን እንደለመዱት “ለብዙዎች” ያለውን “ለብዙዎች ብቻ” ብለው የሌለ ቃል ጨምረው እያነበነቡ መሳታቸው ግልጽ ነው:: ለምሳሌ ጳውሎስ በገላትያ 2:20 ላይ “አሁን እኔ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝ ሰለኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው” በማለት ገልጿል ታድያ ጳውሎስ ለኔ ሙቷል ሰላለ ሌሎችን አግልለን ኢየሱስ ለጳውሎስ ብቻ ነው የሞተው እንበልን? ለጳውሎስ ሞተ ማለት ለሌላው አልሞተም ማለት እንዳልሆነው ሁሉ ሰለህዝቡ ሞተ ወይም የህዝቡን ሃጢያት ተሸከመ ማለት ሰለሌላው አልሞተም ወይም የህሌላውን ሃጢያት አልተሸከመም ማለት አይደለም::

ሌላው ይህ ልጅ እንደ ማጣቀሻ የተጠቀመው ተመሳሳይ ቃል እርሱም በዚሁ መንገድ የሚታይ ነው::

ወደ ዋናው ርእሰ ጉዳይ ከመግባቴ በፊት በመጀመሪያ በመግቢያየ ላይ: የቃላት አረዳዶች ላይ ማስተካከያ ማድረግ እፈልጋለሁ: ወይንም ወደትክክለኛ የቃላት አረዳድ ሁላችንም እንድንመጣ ማገዝ እፈልጋለሁ: ከነዚህ ውሰጥ “እውቀት” ወይም “ማውቅ” : የሚለውን የቅዱስ ቃሉን አረዳድ ከዛም “አለም” ሚለው የትኛውን ነው ሚለውን በመቀጠልም “ምርጫ” የሚለውን ቃል በደንብ እንድንረዳ እሰባለሁ:: በመጀመሪያ አለም ሚለውን እንይ፤ አለም ሚለውን ሰናሰብ ብዙ አይነት የአለም አገላለጽ ቢኖርም አሁንም ይህን ሰናይ የውይይታችንን አውድ ያልሳተ እና የተመለከተውን የአለም ክፍል ማሰብ እንዳለብን አሰባለሁ። ስለዚህ አለም ሰንል ሁለት አይነት አለም ማሰብ ይገባናል። ይህ አሁን ምንኖርበት እና ሚመጣው አለም ሚባሉትን ማለት ነው። ሁለቱም የተፈጠሩ ናቸው።

ሁለቱን አለማት ሚያነጻጽሩ ቃላት::

“በሰው ልጅ ላይ ቃል የሚናገር ሁሉ ይሰረይለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ግን የሚናገር ሁሉ በዚህ ዓለም ቢሆን ወይም በሚመጣው አይሰረይለትም።”
— ማቴዎስ 12፥32

“ስለ እርሱ የምንናገርበትን የሚመጣውን ዓለም ለመላእክት ያስገዛው አይደለምና።”
— ዕብራውያን 2፥5

“መልካሙንም የእግዚአብሔርን ቃልና ሊመጣ ያለውን የዓለም ኃይል የቀመሱትን”
— ዕብራውያን 6፥5

“ክርስቶስንም ከሙታን ሲያስነሣው ከአለቅነትና ከሥልጣንም ከኃይልም ከጌትነትም ሁሉ በላይና በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሊመጣ ባለው ዓለም ደግሞ ከሚጠራው ስም ሁሉ በላይ በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ሲያስቀምጠው በክርስቶስ ባደረገው ሥራ የብርታቱ ጉልበት ይታያል፤”
— ኤፌሶን 1፥20-21

የአሁኑ አለም መጨረሻ የጀመረው መቸ ነው?

“ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤”
— ገላትያ 4፥4

“እንዲህ ቢሆንስ፥ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ብዙ ጊዜ መከራ ሊቀበል ባስፈለገው ነበር፤ አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጦአል።”
— ዕብራውያን 9፥26

የሚመጣው አለም መፈጠር የጀመረው መቸ ነው?

ክርስቶስ ከተሰቀለባት እለት እንስቶ አዲሱ አለም መፈጠር ጀምሯል።

“ከዓለምም ፍጥረት ጀምሮ በታረደው በግ፥ ሕይወት መጽሐፍ ስሞቻቸው ያልተጻፉ በምድር የሚኖሩ ሁሉ ይሰግዱለታል።”
— ራእይ 13፥8

ክርስቶስ የተሰቅለው ይህ አለም ወይም የበከለው አለም ሲፈጠር ሳይሆን የሚመጣው አለም፥ መፈጠር ከጀመረባት ጊዜ አንስቶ ነው። ማለት ነው።

“ያየኸው አውሬ አስቀድሞ ነበረ፥ አሁንም የለም፥ ከጥልቁም ይወጣ ዘንድ አለው፥ ወደ ጥፋትም ይሄዳል፤ ስሞቻቸውም ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ በሕይወት መጽሐፍ ያልተጻፉ በምድር የሚኖሩ አውሬው አስቀድሞ እንደነበረ አሁንም እንደሌለ፥ ነገር ግን እንዳለ ሲያዩ ያደንቃሉ።”
— ራእይ 17፥8
“ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፦ እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ።”
— ማቴዎስ 25፥34
“ሄጄም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ፥ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ።”
— ዮሐንስ 14፥3

መጽሐፍ ቅዱስ መታደስ በሚል የዚህን አለም ድጋሚ መፈጠር ሲገልጽ እንዴት ነበር?

“እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ፥ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለ ነበረው ሥራ አይደለም፤”
— ቲቶ 3፥5

ኤፌሶን 2
----------

9 ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።
10 እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።

“ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።”
— 2ኛ ቆሮ 5፥17

“ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ።”

— ኤፌሶን 4፥24

የሚ

2ኛ ጴጥሮስ 3
----------

6 በዚህም ምክንያት ያን ጊዜ የነበረ ዓለም በውኃ ሰጥሞ ጠፋ፤
7 አሁን ያሉ ሰማያትና ምድር ግን እግዚአብሔርን የማያመልኩት ሰዎች እስከሚጠፉበት እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ተጠብቀው በዚያ ቃል ለእሳት ቀርተዋል።

ራእይ 21
----------

1 አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርንም አየሁ፥ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፥ ባሕርም ወደ ፊት የለም።

...
5 በዙፋኑም የተቀመጠው፦ እነሆ፥ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለ። ለእኔም፦ እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኛዎች ናቸውና ጻፍ አለኝ።

ማወቅ ሚለው ቃል በእብራይስጡ "ያዳህ" በግሪኩ "ጊኖስኮ" ተብሎ የሚታወቀው ማለት ነው:: ማውቅ ወይም ጊኖስኮ በቅዱሳት መጸህፍት በሰባት መንገድ የተገለጸ ቢሆንም ርእሳችንን በሚመጥንና በሚመለከት መልኩ ሶስቱን ከቅዱሳት መጸህፍት መዳሰስ እፈልጋለሁ:: ከነዚህም ውስጥ አንደኛው እና የመጀመሪያው የሚሆነው

1. በእይታ ማወቅ ሚለው ነው::

   "ምሳሌውንም ከበለስ ተማሩ፤ ጫፍዋ ሲለሰልስ ቅጠልዋም ሲያቈጠቍጥ፥ ያን ጊዜ በጋ እንደ ቀረበ ታውቃላችሁ፤" — ማርቆስ 13፥28

2. ነገርን መረዳት

   "ዓለም ቢጠላችሁ ከእናንተ በፊት እኔን እንደ ጠላኝ እወቁ።"
   — ዮሐንስ 15፥18

   "ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ነገራቸው፤ እነርሱ ግን የነገራቸው ምን እንደ ሆነ አላስተዋሉም።"— ዮሐንስ 10፥6

3. የሰውን ማንነት መረዳት

   "አንድ መክሊትም የተቀበለው ደግሞ ቀርቦ፦ ጌታ ሆይ፥ ካልዘራህባት የምታጭድ ካልበተንህባትም የምትሰበስብ ጨካኝ ሰው መሆንህን አውቃለሁ"— ማቴዎስ 25፥24

   "ነገር ግን ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ያውቅ ነበር፤ ስለ ሰውም ማንም ሊመሰክር አያስፈልገውም ነበርና አይተማመናቸውም ነበር፤ ራሱ በሰው ያለውን ያውቅ ነበርና።"— ዮሐንስ 2፥24-25

   "የጠራው ፈሪሳዊም አይቶ፦ ይህስ ነቢይ ቢሆን፥ ይህች የምትዳስሰው ሴት ማን እንደ ሆነች እንዴትስ እንደ ነበረች ባወቀ ነበር፥ ኃጢአተኛ ናትና ብሎ በልቡ አሰበ።"
   — ሉቃስ 7፥39

4. ልዩ ግንኙነት ወይንም መቀራረብ

"እንዲህም ብሎአል፦ እኔ ከምድር ወገን ሁሉ እናንተን ብቻችሁን አውቄአችኋለሁ፤ ስለዚህ ስለ ኃጢአታችሁ ሁሉ እበቀላችኋለሁ።" — አሞጽ 3፥2

"አውቄዋለሁ የሚል ትእዛዛቱንም የማይጠብቅ ውሸተኛ ነው እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም።" — 1ኛ ዮሐንስ 2፥4

"ወዳጆች ሆይ፥ ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለ ሆነ፥ የሚወደውም ሁሉ ከእግዚአብሔር ስለ ተወለደ እግዚአብሔርንም ስለሚያውቅ፥ እርስ በርሳችን እንዋደድ።" — 1ኛ ዮሐንስ 4፥7

"አዳምም ሚስቱን ሔዋንን አወቀ፤ ፀነሰችም፥ ቃየንንም ወለደች። እርሰዋም፦ ወንድ ልጅ ከእግዚአብሔር አገኘሁ አለች።" — ዘፍጥረት 4፥1

"ቃየንም ሚስቱን አወቀ ፀነሰችም፥ ሄኖሕንም ወለደች። ከተማም ሠራ፥ የከተማይቱንም ስም በልጁ ስም ሄኖሕ አላት።" — ዘፍጥረት 4፥17

"የዚያን ጊዜም፦ ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።" — ማቴዎስ 7፥23

"እርሱ ግን መልሶ፦ እውነት እላችኋለሁ፥ አላውቃችሁም አለ።" — ማቴዎስ 25፥12

"እግዚአብሔርን ፊት ለፊት እንዳወቀው እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ ከዚያ ወዲህ በእስራኤል ዘንድ አልተነሣም፤"— ዘዳግም 34፥10

**ምርጫ**

ምርጫን ሰናሰብ የተለያየ ምርጫ እናሰባለን (1ኛ ዘፈቀደ ወይም RANDOM ምርጫ) 2ኛ: ለአንድ የተለየ አላማ መምረጥ: አሮንን ለክህነት: ሳሙኤልን ለነብይነት: ዳዊትን ለንግሰና መጥሙቁ ዮሐንስን: መንገድ ለማቅናት(ይህ አይነቱ ምርጫ በዘርና እንዲሁም እግዚአብሔር ከማህጸን ወይም ከማህጸን በፊት ሊመርጥ ሚችለው ምርጫ ነው:: 3ኛ/ በአንክሮ እና በተለየ ጥራት መምረጥ ሲሆን 4ኛ ደግሞ እቃወችን ለእግዚአብሔር ለቅድሰና ሰራ መምረጥ ነው::

ምርጫ ሰንልም በተመሳሳይ ግሪኩ በሶሰት የቋንቋ አጠቃቀም ያቀርብልናል በግሰ(VERB) ገላጭ(ADJECTIVE) እና ሰም(NOUN) ግሱ "ኤክልጎማይ" ገላጩ "ኤክሌክቶስ" እና ሰሙ "ኤክሎግኤ" ሲሆኑ:: እንደየ አገባባቸው የተለያየ ትርጉም ይሰጣሉ::

እዚጋ ግሱን ለማየት ያክል: እናንተም በዚህ "ኤክልጎማይ" የሚለው የግሪክ ቃል ላይ መጠነኛ ታደርጉ ዘንድ እግብዛለሁ:: ይህ ግሰ ሚገልጸው የእንግሊዘኛውን FAVOUR የሚለውን ነው ለአማረኛው "ምራጫ" ከሚለው አሻሚ ቃል ውጭ አማራጭ ቃል አጥቸለታለሁ ነገር ግን "እድሎ: ወይን ማዳላት" የሚለው ቃል በተሻለ ይገልጸዋል:: ይህ የግሪክ ቃል የሚወክለው ደግሞ ዝም ብሎ RANDOMLY ወይም በዘፈቀደ ማድላትን ወይም መምረጥን ሳይሆን በጣም ጥንቃቄ የሞላበት ጥራትን ያማከለ ምርጫ ማድረግን ነው::

ከዚህ ተነሰተን አንዳንድ ሃሳቦችን እያነሳን እንመልሰ::

የተመረጠ መመረጡ ከምን ይመነጫል? ይህ ምርጫ የሚመጣው እግዚአብሔር ከሚያሰቀምጠው ቅድመ ሁኔታ ብቻ ነው ምክንያቱም ማንም እግዚአብሔርን እንዲ አድርግ እንዲ አታድርግ ሊለው አይችልም:: ያእቆብን ወደድሁ ኤሳውን ጠላሁ በማለት እግዚአብሔር ገና ልጆቹ ሳይወለዱ አሰቀድሞ የእርሱ ምርጫ ብቻ እንደሚጸና ይናገራልና:: እንዴት ለሚለው ምናልባት መጨረሻ ላይ በመልሰ ክፍሌ አብረን እናየዋለን::

የተመረጠ መመረጡ ሊቀር ይችላል? አወ እግዚአብሔር ካሰቀመጠው ቅድመ ሁኔታ ካፈነገጠ ወይም ግቡን ካልመታ ሊቀር ይችላል:: ለምሳሌ የአሮን ክህነት ለዘላለም የተሰጠ ሰርአት ነበር::

"እርሱ ከልጆቹ ጋር ተነሥቶ በእግዚአብሔር ስም ለዘላለም ያገለግል ዘንድ አምላክህ እግዚአብሔር ከነገዶችህ ሁሉ ስለ መረጠው ነው።"— ዘዳግም 18፥5

ነገር ግን የተሰጠውን አላማ ከግብ ማድረሰ ሰላልቻለ ለዘላለም እንዲያገለግል በእግዚአብሔር የተመረጠው የአሮንና ልጆቹ ክህነት ተሸሯል::

"ሕጉ ምንም ፍጹም አላደረገምና፥ ስለዚህም የምትደክም የማትጠቅምም ስለሆነች የቀደመች ትእዛዝ ተሽራለች፥ ወደ እግዚአብሔርም የምንቀርብበት የሚሻል ተስፋ ገብቶአል።"— ዕብራውያን 7፥18-19

እግዚአብሔር ሳይመርጥ የሚቆይበት ጊዜ አለውን?
2 ዜና 6:5-6 “5 እርሱም፦ ሕዝቤን ከግብጽ ካወጣሁበት ቀን ጀምሮ ስሜ የሚጠራበት ቤት በዚያ ይሠራልኝ ዘንድ ከእስራኤል ነገድ ሁሉ ማንኛውንም ከተማ አልመረጥሁም በሕዝቤም በእስራኤል ላይ አለቃ ይሆን ዘንድ ማንንም አልመረጥሁም፤ ነገር ግን ስሜ በዚያ እንዲጠራባት ኢየሩሳሌምን መርጫለሁ፥ በሕዝቤም በእስራኤል ላይ እንዲሆን ዳዊትን መርጫለሁ ብሎአልና።”
ምርጫ የሚሉትን ቃላት ተደጋጋሚ ለክርስቲያኖች ይውላልና እንዴት እንረዳው? በመጀመሪያ ማስተዋል የሚገባን ነጥብ፥ የትም ብትፈልጉ ምርጫን ለግለሰብ ውሎ አታገኙትም በአንድ ቦታ እንኳ ምርጫ ሚለው ቃል ለግለሰብ አልዋለም። ለምሳሌ ጳውሎስ ሶስት የግል ደብዳቤ ጽፏል። ነገር ግን ለአንዱም ስለመመረጡ አልጻፈለትም፥ እንዳውም ጭራሽ አያነሳለትም። ሁሉም ምርጫ ሚሉ ቃላት ያሉት ለአለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን እና በአይሁድና በአህዛብ መካከል ክርክር ባለባቸው ስፍራወች ነው ይህን ክፍል ምናገኘው። ይህም አይሁዶች እኛ ኪዳኑ ያለን፥ እግዚአብሔርን ምናውቅ፥ ሕጉ ያለን በእግዚአብሔር የተመረጥን ነን ብለው ስለሚመኩ ቤተ ክርስቲያን እንጅ የአይሁድ ምርጫ የበለጠ እንዳልሆነ ለማሳየት ነው።
በአንድም ቦታ እንዲያምኑ የተመረጡ እንዳሉ በመጽሐፍ ቅዱስ አይናገርም። ሰው ደግሞ የሚድነው በእምነት ነው እንጅ በምርጫ አደለም። ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲያምኑ የመረጣቸው የሉም።

**በጌታ ትምህርት መሰረትም የክርስቲያኖች መመረጥ መጠራትን የሚከተል እንጅ መጠራት መመረጥን የሚከተል አደለም ወይንም መመረጥ መጠራትን አይቀድምም፤**

ማቴዎስ 22
----------
3 የታደሙትንም ወደ ሰርጉ ይጠሩ ዘንድ ባሮቹን ላከ ሊመጡም አልወደዱም።
4 ደግሞ ሌሎችን ባሮች ልኮ፦ የታደሙትን፦ እነሆ፥ ድግሴን አዘጋጀሁ፥ ኮርማዎቼና የሰቡት ከብቶቼ ታርደዋል፥ ሁሉም ተዘጋጅቶአል፤ ወደ ሰርጉ ኑ በሉአቸው አለ።
5 እነርሱ ግን ቸል ብለው አንዱ ወደ እርሻው፥ ሌላውም ወደ ንግዱ ሄደ፤
6 የቀሩትም ባሮቹን ይዘው አንገላቱአቸው ገደሉአቸውም።
7 ንጉሡም ተቈጣ፥ ጭፍሮቹንም ልኮ እነዚያን ገዳዮች አጠፋ፤ ከተማቸውንም አቃጠለ።
8 በዚያን ጊዜ ባሮቹን፦ ሰርጉስ ተዘጋጅቶአል፥ ነገር ግን የታደሙት የማይገባቸው ሆኑ፤
9 እንግዲህ ወደ መንገድ መተላለፊያ ሄዳችሁ ያገኛችሁትን ሁሉ ወደ ሰርጉ ጥሩ አለ።
10 እነዚያም ባሮች ወደ መንገድ ወጥተው ያገኙትን ሁሉ ክፉዎችንም በጎዎችንም ሰበሰቡ፤ የሰርጉንም ቤት ተቀማጮች ሞሉት።
11 ንጉሡም የተቀመጡትን ለማየት በገባ ጊዜ በዚያ የሰርግ ልብስ ያለበሰ አንድ ሰው አየና፦ ወዳጄ ሆይ፥
12 የሰርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት ወደዚህ ገባህ? አለው እርሱም ዝም አለ።
13 በዚያን ጊዜ ንጉሡ አገልጋዮቹን፦ እጁንና እግሩን አስራችሁ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል አለ።
14 የተጠሩ ብዙዎች፥ የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸውና።
እዚህጋ የተመረጡ የተባሉት የምናያቸው ሰወች ለእግዚአብሔር ጥሪ በጎን ምላሽ የሰጡ ናቸው እንጅ በዘፈቀደ ከዚህኛው አለም አስቀድመው የተመረጡ መሆናቸውን አያሳይም። ከዚህ ተነስተን የተመረጡ የተባሉት እጩነታቸውና ዝግጅታቸው ተመረጡ የተባሉት የሚመጣው አለም ሳይፈጠር እንጅ ያሁኑ አለም ሳይፈጠር አደለም።

1.እግዚአብሔር ሉአላዊ ነው።
1.1 እግዚአብሔር ብቸኛ ፈጣሪ ነው።
“ከማኅፀን የሠራህ፥ የሚቤዥህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ሁሉን የፈጠርሁ፥ ሰማያትን ለብቻዬ የዘረጋሁ ምድርንም ያጸናሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ ከእኔ ጋር ማን ነበረ?” — ኢሳይያስ 44፥24

1.2 እግዚአብሔር ብቸኛ መድሐኒት ነው::
"ይናገሩ ይቅረቡም በአንድነትም ይማከሩ፤ ከጥንቱ ይህን ያሳየ ከቀድሞስ የተናገረ ማን ነው? ያሳየሁም የተናገርሁም እኔ እግዚአብሔር አይደለሁምን? ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ እኔ ጻድቅ አምላክና መድኃኒት ነኝ፥ ከእኔም በቀር ማንም የለም።"
— ኢሳይያስ 45፥21
1.4 እግዚአብሔር ፈራጅ የሚባላ የሚያጠፋም እሳት ነው
"አምላክህ እግዚአብሔር የሚበላ እሳት ቀናተኛም አምላክ ነውና።"
— ዘዳግም 4፥24
"አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነውና።"
— ዕብራውያን 12፥29

1.4 እግዚአብሔር ያለፈውንና መጭውን ቀድሞ ያውቃል::
"ይናገሩ ይቅረቡም በአንድነትም ይማከሩ፤ ከጥንቱ ይህን ያሳየ ከቀድሞስ የተናገረ ማን ነው? ያሳየሁም የተናገርሁም እኔ እግዚአብሔር አይደለሁምን? ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ እኔ ጻድቅ አምላክና መድኃኒት ነኝ፥ ከእኔም በቀር ማንም የለም።"
— ኢሳይያስ 45፥21

2 ሉአላዊነቱ ኩሩነት አደለም ወይንም ሉአላዊነቱ ብቻ የእግዚአብሔር የእግዚአብሔር መገለጫ አደለም::
2.1 እግዚአብሔር ፍቅር ነው::
"ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፥ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና።"
— 1ኛ ዮሐንስ 4፥8
"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።"
— ዮሐንስ 3፥16
"ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።"
— ሮሜ 5፥8
ስለዚህም ሰው ሁሉ እንዲድን ይወዳል:
"ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው።"
— 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፥3-4
ፈቃዱም ሃጢያተኛው ከሃጢያቱ እንዲመለስ እንጅ እንዲጠፋ አደለም።
"በውኑ ኃጢአተኛ ይሞት ዘንድ እፈቅዳለሁን? ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ ከመንገዱስ ይመለስና በሕይወት ይኖር ዘንድ አይደለምን?"
— ሕዝቅኤል 18፥23
የሰውን ልጆች ሚያሳዝንና ሚያሰጨንቅ አደለም።
"የሰውን ልጆች ከልቡ አያስጨንቅም፥ አያሳዝንምም።"
— ሰቆ. 3፥33
ማቴዎስ 11
----------

[28] "እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ።
[29] ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤"

2.1 እግዚአብሔር የሰው ልጅ ጓደኛ ነው::
"መጽሐፍም፦ አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት ያለው ተፈጸመ፤ የእግዚአብሔርም ወዳጅ ተባለ።"

— ያዕቆብ 2፥23
በዚህ ቃል የተጠቀሰው ወዳጅ ተብሎ የተጠቀሰው የግሪክ ቃል ፊሎስ ጓደኛ ማለት ነው::

2.2 እግዚአብሔር የሰውን ቃል ይሰማል።
“እግዚአብሔር ለእስራኤል ይዋጋ ነበርና እግዚአብሔር የሰውን ቃል የሰማበት እንደዚያ ያለ ቀን ከዚያም በፊት ከዚያም በኋላ አልነበረም።”— ኢያሱ 10፥14
“እንዳያጠፋቸው ቍጣውን ይመልስ ዘንድ የተመረጠው ሙሴ በመቅሠፍት ጊዜ በፊቱ ባይቆም ኖሮ፥ ያጠፋቸው ዘንድ ተናገረ።”— መዝሙር 106፥23

2.3 እግዚአብሔር ከሰው ልጅ ጋር አብሮ መስራት የሚወድ አምላክ ነው::

“ለጣዖት ከተሠዋ፥ ከደምም፥ ከታነቀም፥ ከዝሙትም ትርቁ ዘንድ ከዚህ ከሚያስፈልገው በቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናልና፤ ከዚህም ሁሉ ራሳችሁን ብትጠብቁ በመልካም ትኖራላችሁ። ጤና ይስጣችሁ።”— ሐዋርያት 15፥28-29
“እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤” — ሮሜ 8፥26
“የእግዚአብሔር እርሻ ናችሁ፤ የእግዚአብሔር ሕንፃ ናችሁ፤ ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነንና።”
— 1ኛ ቆሮንቶስ 3፥9
“ከእግዚአብሔር ጋር አብረን የምንሠራ እንደ መሆናችን መጠን፣ የተቀበላችሁትን የእግዚአብሔርን ጸጋ ከንቱ እንዳታደርጉት ዐደራ እንላችኋለን።”
— 2ኛ ቆሮንቶስ 6፥1 (አዲሱ መ.ት)
ከዚህ የምንረዳው እኔ ሉአላዊ ነኝና እናንተ የምታስፈልጉኝ አደላችሁም ብሎ የሚገፋ የሚኮራ አምላክ ሳይሆን ከሰው ጋር በፍቅርና በቸርነት በትህትና አብሮ መስራት የሚወድ አምላክ መሆኑን እንረዳለን::

2.4 እግዚአብሔር ፈራጅ አምላክ ስለሆነ ሃጢያተኛን እንዳይቀጣ መካከለኛ ሰው ይፈልጋል::

“አሁንም የሰውዬውን ሚስት መልስ ነቢይ ነውና፥ ስለ አንተም ይጸልያል፥ ትድናለህም። ባትመልሳት ግን አንተ እንድትሞት ለአንተ የሆነውም ሁሉ እንዲሞት በእርግጥ እወቅ።”
— ዘፍጥረት 20፥7
“አሁን እንግዲህ ሰባት ወይፈኖችና ሰባት አውራ በጎች ይዛችሁ ወደ ባሪያዬ ወደ ኢዮብ ዘንድ ሂዱ፥ የሚቃጠልንም መሥዋዕት ስለ ራሳችሁ አሳርጉ፤ ባሪያዬም ኢዮብ ስለ እናንተ ይጸልያል፥ እኔም እንደ ስንፍናችሁ እንዳላደርግባችሁ ፊቱን እቀበላለሁ፤ እንደ ባሪያዬ እንደ ኢዮብ ቅን ነገር ስለ እኔ አልተናገራችሁምና።”
— ኢዮብ 42፥8
“አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤”
— 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፥5

3፣ እግዚአብሔር የሰውን ምርጫ ያከብራል።
ዘጸአት 12
----------
21 ሙሴም የእስራኤልን ሽማግሌዎች ጠርቶ አላቸው፡- በየቤታችሁ ጠቦት ምረጡ፥ ወስዳችሁም ለፋሲካ እረዱት።
22 ከሂሶጵ ቅጠልም ጭብጥ ውሰዱ፥ በዕቃ ውስጥ ባለውም ደም ንከሩት፥ በዕቃውም ውስጥ ካለው ደም ሁለቱን መቃኖችና ጉበኑን እርጩ ከእናንተም አንድ ሰው ከቤቱ ደጅ እስኪነጋ ድረስ አይውጣ።
23 እግዚአብሔር ግብፃውያንን ይመታ ዘንድ ያልፋልና፤ ደሙንም በጉበኑና በሁለቱ መቃኖች ላይ ባየ ጊዜ እግዚአብሔር በደጁ ላይ ያልፋል፥ አጥፊውም ይመታችሁ ዘንድ ወደ ቤታችሁ እንዲገባ አይተውም።
24 ለእናንተ ለልጆቻችሁም ለዘላለም ሥርዓት አድርጋችሁ ይህችን ነገር ጠብቁ።"
እግዚአብሔር እስራኤልን እንዲመራ ሙሴን ብቻ መረጠ ነገር ግን በዮቶር ምክር ሌሎችም መሪወች

ተመረጡ።
“አንተም ከሕዝቡ ሁሉ አዋቂዎችን፥ እግዚአብሔርን የሚፈሩትን፥ የታመኑ፥ የግፍንም ረብ የሚጠሉትን ሰዎች ምረጥ፤ ከእነርሱም የሺህ አለቆችን፥ የመቶ አለቆችን፥ የአምሳ አለቆችን፥ የአሥርም አለቆችን ሹምላቸው።”
— ዘጸአት 18፥21
“ከየነገዱ ሁሉ ሦስት ሦስት ሰዎች ምረጡ፥ እኔም እልካቸዋለሁ፤ ተነሥተውም አገሩን ይዞራሉ፥ እንደ ርስታቸውም መጠን ይጽፉታል ወደ እኔም ይመለሳሉ።”
— ኢያሱ 18፥4
“በዚያም ዘመን በእስራኤል ዘንድ ንጉሥ አልነበረም፤ ሰውም ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር።”
— መሳፍንት 17፥6
“በዚያም ዘመን በእስራኤል ዘንድ ንጉሥ አልነበረም፤ ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር።”
— መሳፍንት 21፥25
“ሂድ ለዳዊት፦ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ሦስት ነገሮች በፊትህ አኖራለሁ፤ አደርግብህ ዘንድ ከእነርሱ አንዱን ምረጥ ብለህ ንገረው አለው።”
— 2ኛ ሳሙኤል 24፥12

1.3 እግዚአብሔር ምርጫን አስቀምጧል
“በፊታችሁ ሕይወትንና ሞትን በረከትንና መርገምን እንዳስቀመጥሁ እኔ ዛሬ ሰማይንና ምድርን በአንተ ላይ አስመሰክራለሁ፤ እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ፤”
— ዘዳግም 30፥19
“እግዚአብሔርም ለአባቶችህ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም እንዲሰጣቸው በማለላቸው በምድሪቱ ትቀመጥ ዘንድ፥ እርሱ ሕይወትህ የዘመንህም ርዝመት ነውና አምላክህን እግዚአብሔርን ትወድደው ትጠባበቀውም ቃሉንም ትሰማ ዘንድ ምረጥ።”
— ዘዳግም 30፥20
“እግዚአብሔርንም ማምለክ ክፉ መስሎ ቢታያችሁ፥ አባቶቻችሁ በወንዝ ማዶ ሳሉ ያመለኩአቸውን አማልክት ወይም በምድራቸው ያላችሁባቸውን የአሞራውያንን አማልክት ታመልኩ እንደ ሆነ፥ የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን።”
— ኢያሱ 24፥15
1 ዜና 21
----------

10 ሂድ፥ ለዳዊት፦ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ሦስቱን ነገሮች በፊትህ አኖራለሁ፤ አደርግብህ ዘንድ ከእነርሱ አንዱን ምረጥ ብለህ ንገረው ብሎ ተናገረው።
11 ጋድም ወደ ዳዊት መጥቶ፦ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ የምትወድደውን ምረጥ፤

...
15 እግዚአብሔርም ያጠፋት ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም መልአክን ሰደደ፤ ሊያጠፋትም በቀረበ ጊዜ እግዚአብሔር አይቶ ስለ ክፉው ነገር ተጸጸተ፥ የሚያጠፋውንም መልአክ፦ በቃህ አሁን እጅህን መልስ አለው። የእግዚአብሔርም መልአክ በኢያቡሳዊው በኦርና አውድማ አጠገብ ቆሞ ነበር።
“ብንጸና፥ ከእርሱ ጋር ደግሞ እንነግሣለን፤ ብንክደው፥ እርሱ ደግሞ ይክደናል፤”
— 2ኛ ጢሞቴዎስ 2፥12
“በጽድቅ የሚጸና በሕይወት ይኖራል፤ ክፉትን የሚከተል ግን ለሞቱ ነው።”
— ምሳሌ 11፥19
“በሁሉም ስለ ስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፤ እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል።”
— ማቴዎስ 10፥22
ማቴዎስ 24
----------

[12] ከዓመፃም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች።
[13] እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል።
እዚህጋ ፍቅር ተብሎ የተገለጸው አጋፒ ሚለው የግሪክ ቃል ነው ይህም  እግዚአብሔር በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ፍቅር ነው።
“ልትቀበለው ያለህን መከራ አትፍራ። እነሆ፥ እንድትፈተኑ ዲያብሎስ ከእናንተ አንዳንዶቻችሁን በወኅኒ ሊያገባችሁ አለው፥ አሥር ቀንም መከራን ትቀበላላችሁ። እስከሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ።”
 — ራእይ 2፥10
ራእይ 3
----------

[15] በራድ ወይም ትኩስ እንዳይደለህ ሥራህን አውቃለሁ። በራድ ወይም ትኩስ ብትሆንስ መልካም በሆነ ነበር።
[16] እንዲሁ ለብ ስላልህ በራድም ወይም ትኩስ ስላልሆንህ ከአፌ ልተፋህ ነው።
“ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ።”
 — 1ኛ ቆሮንቶስ 10፥12

ሮሜ 11
----------

[21] እግዚአብሔር እንደ ተፈጥሩት ለነበሩት ቅርንጫፎች የራራላቸው ካልሆነ ለአንተ ደግሞ አይራራልህምና።
[22] እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጭከና ተመልከት፤ ጭከናው በወደቁት ላይ ነው፥ በቸርነቱ ግን ጸንተህ ብትኖር የእግዚአብሔር ቸርነት በአንተ ላይ ነው፤ ያለዚያ አንተ ደግሞ ትቆረጣለህ።

“እነሆ በደጅ ቆሜ እንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።”
 — ራእይ 3፥20

“መንፈሱና ሙሽራይቱም፦ ና ይላሉ። የሚሰማም፦ ና ይበል። የተጠማም ይምጣ፥ የወደደም የሕይወትን ውኃ እንዲያው ይውሰድ።”
 — ራእይ 22፥17

4. እግዚአብሔር ሉአላዊነቱን ከኩራት ጋር ወይንም ከሌሎች ባህርያቱ ነጥሎ ሚያጎላ ሚያይን ሰው አይታገሰም::
ኤለፋዝና ጓደኞቹ ለእዮብ የእግዚአብሔርን ሉአላዊነት ከፍቅሩና ለሰው ልጅ ካለው ጉድኝት አርቀው ስለ እግዚአብሔር ሉአላዊነት ብቻ በሚደንቅ ሁኔታ አጉልተው ይናገራሉ:: ኤልፋዝ ዋናቸው ስለሆነ ለናሙና ምስክር በሶስት ይጸናልና ሶስት እንውሰድ: ሌላውን አንነተው ሙሉውን መጽሐፈ እዮብን በማንበብ መረዳት ትችላላችሁ::

“እነሆ፥ በባሪያዎቹ አይታመንም፤ መላእክቱንም ስንፍና ይከሰሳቸዋል፤”
 — ኢዮብ 4፥18
ኢዮብ 22
----------

[2] በውኑ ሰው እግዚአብሔርን ይጠቅመዋልን? በእውነት ጥበበኛ ሰው ራሱን ይጠቅማል።
[3] ጻድቅ መሆንህስ ሁሉን የሚችለውን አምላክ ደስ ያሰኘዋልን? መንገድህን ማቅናትህስ ይጠቅመዋልን?

“ጻድቅስ ብትሆን ምን ትሰጠዋለህ? ወይስ ከእጅህ ምንን ይቀበላል?”
 — ኢዮብ 35፥7

በማለት ኤልፋዝ የእግዚአብሔርን ሉአላዊነት ከሌሎች ባህርያቱ ነጥሎ ያሰቀምጠዋል:: ለዚህ የእግዚአብሔር መልስ እጅግ ሚያስደንቅ ነው:: ኤልፋዝን ምን እንዳለው ተመልከቱ

“እግዚአብሔርም ይህን ቃል ለኢዮብ ከተናገረ በኋላ እግዚአብሔር ቴማናዊውን ኤልፋዝን፦ እንደ ባሪያዬ እንደ ኢዮብ ቅንን ነገር ስለ እኔ አልተናገራችሁምና ቍጣዬ በአንተና በሁለቱ ባልንጀሮችህ ላይ ነድዶአል።”
— ኢዮብ 42፥7

ፍቃድ አለው።
“በምክራቸው፥ ነፍሴ፥ አትግባ፤ ከጉባኤአቸውም ጋር፥ ክብሬ፥ አትተባበር፤ በቍጣቸው ሰውን ገድለዋልና፥ በገዛ ፈቃዳቸውም በሬን አስነክሰዋልና።”
— ዘፍጥረት 49፥6
“ከእናንተ ዘንድ ለእግዚአብሔር ቍርባንን አቅርቡ፤ የልብ ፈቃድ ያለው የእግዚአብሔርን ቍርባን ያምጣ፤ ወርቅና ብርም ናስም፤”
— ዘጸአት 35፥5

“ከእስራኤል ልጆችም ያመጡ ዘንድ ልባቸው ያስነሣቸው ወንዶችና ሴቶች ሁሉ ሙሴ ይሠራ ዘንድ እግዚአብሔር ላዘዘው ሥራ ሁሉ ለእግዚአብሔር ስጦታ በፈቃዳቸው አመጡ።”
— ዘጸአት 35፥29
“እነርሱም የእስራኤል ልጆች ለመቅደስ ማገልገያ ሥራ ያመጡትን ስጦታ ሁሉ ይሠሩ ዘንድ ከሙሴ ተቀበሉ። እነዚያም እንደ ፈቃዳቸው ማለዳ ማለዳ ስጦታውን ገና ወደ እርሱ ያመጡ ነበር።”
— ዘጸአት 36፥3
“ለአሮንና ለልጆቹ ለእስራኤልም ልጆች ሁሉ እንዲህ ብለህ ንገራቸው፦ ከእስራኤል ቤት ወይም ከእናንተ መካከል ከሚቀመጡት እንግዶች ማናቸውም ሰው ስእለቱን ሁሉ፥ በፈቃዱም የሚያቀርበውን ሁሉ፥ ለእግዚአብሔር ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚያቀርበውን ቍርባን ቢያቀርብ፥”
— ዘሌዋውያን 22፥18
“ወደዚያም የሚቃጠለውን መሥዋዕታችሁን፥ ሌላ መሥዋዕታችሁንም፥ አሥራታችሁንም፥ በእጃችሁም ያነሣችሁትን ቍርባን፥ ስእለታችሁንም፥ በፈቃዳችሁ የምታቀርቡትን፥ የላማችሁንና የበጋችሁንም በኩራት ውሰዱ።”
— ዘዳግም 12፥6
“አምላክህ እግዚአብሔር በባረከህ መጠን በፈቃድህ የምታቀርበውን አምጥተህ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር የሰባቱ ሱባዔ በዓል ታደርጋለህ።”
— ዘዳግም 16፥10
“በአፍህ የተናገርኸውን ለአምላክህ ለእግዚአብሔር በፈቃድህ ተስለሃልና ከከንፈርህ የወጣውን ታደርግ ዘንድ ጠብቅ።”
— ዘዳግም 23፥23
“አዲስ ሚስትም ያገባ ሰው ወደ ጦርነት አይሂድ፥ ነገርም አይጫኑበት፤ ነገር ግን አንድ ዓመት በቤቱ በፈቃዱ ይቀመጥ፥ የወሰዳትንም ሚስቱን ደስ ያሰኛት።”
— ዘዳግም 24፥5
መሳፍንት 5
----------

7 አንቺ፥ ዲቦራ፥ እስክትነሺ ድረስ፥ ለእስራኤልም እናት ሆነሽ እስክትነሺ ድረስ፥ ኃያላን በእስራኤል ዘንድ አነሱ፥ አለቁም።
8 አዲሶች አማልክትን መረጡ፤ በዚያ ጊዜ ሰልፍ በበሮች ሆነ፤ በአርባ ሺህ በእስራኤል ዘንድ ጦርና ጋሻ አልታየም።
9 ልቤ ወደ እስራኤል አለቆች ነው፥ በሕዝቡ መካከል ነፍሳቸውን በፈቃዳቸው ወደ ሰጡት፤ እግዚአብሔርን አመስግኑ።

“ኢዮአስም ካህናቱን፦ ወደ እግዚአብሔር ቤት የሚገባውን የተቀደሰውን ገንዘብ ሁሉ፥ ስለ ነፍሱም ዋጋ የሚቀርበውን ገንዘብ፥ በልባቸውም ፈቃድ ወደ እግዚአብሔር ቤት የሚያመጡትን ገንዘብ ሁሉ፥”
— 2ኛ ነገሥት 12፥5
“አንተም፥ ልጄ ሰሎሞን ሆይ፥ እግዚአብሔር ልብን ሁሉ ይመረምራልና፥ የነፍስንም አሳብ ሁሉ ያውቃልና፥ የአባትህን አምላክ እወቅ በፍጹም ልብና በነፍስህ ፈቃድም አምልከው ብትፈልገው ታገኘዋለህ ብትተወው

ግን ለዘላለም ይጥልሃል።”
 — 1 ዜና 28፥9
“በሠራተኞች እጅ ለሚሠራው ሥራ ሁሉ ለወርቁ ዕቃ ወርቁን፥ ለብሩም ዕቃ ብሩን ሰጥቻለሁ። ዛሬ በፈቃዱ ራሱን ለእግዚአብሔር የሚቀድስ ማነው?”
 — 1 ዜና 29፥5
“ሕዝቡም ፈቅደው ሰጥተዋልና፥ በፍጹም ልባቸውም ለእግዚአብሔር በፈቃዳቸው አቅርበዋልና ደስ አላቸው፤ ንጉሡም ዳዊት ደግሞ ታላቅ ደስታ ደስ አለው።”
 — 1 ዜና 29፥9
“የሌዋዊውም የይምና ልጅ የምሥራቁ ደጅ በረኛ ቆሬ የእግዚአብሔርን መባና የተቀደሱትን ነገሮች እንዲያካፍል ሕዝቡ ለእግዚአብሔር በፈቃድ ባቀረቡት ላይ ተሾመ።”
 — 2 ዜና 31፥14
“መሳፍንቱም ለሕዝቡና ለካህናቱ ለሌዋውያኑም በፈቃዳቸው ሰጡ፤ የእግዚአብሔርም ቤት አለቆች፥ ኬልቂያስ፥ ዘካርያስ፥ ይሒኤል፥ ለፋሲካው መሥዋዕት እንዲሆን ሁለት ሺህ ስድስት መቶ በጎችና ፍየሎች፥ ሦስት መቶም በሬዎች ለካህናቱ ሰጡ።”
 — 2 ዜና 35፥8
“በሚኖርበትም ስፍራ ሁሉ ለቀረው ሰው የአገሩ ሰዎች በብርና በወርቅ በዕቃም በእንስሳም ይርዱት፤ ይህም በኢየሩሳሌም ላለው ለእግዚአብሔር ቤት በፈቃዳቸው ከሚያቀርቡት ሌላ ይሁን።”
 — ዕዝራ 1፥4
“በዙሪያቸውም ያሉ ሁሉ በፈቃዳቸው ካቀረቡት ሁሉ ሌላ በብር ዕቃና በወርቅ በገንዘቦችና በእንስሶች በሌላም ስጦታ አገዙአቸው።”
 — ዕዝራ 1፥6
“ንጉሡንና አማካሪዎቹም መኖሪያው በኢየሩሳሌም ለሆነው ለእስራኤል አምላክ በፈቃዳቸው ያቀረቡትን ብርና ወርቅ፥”
 — ዕዝራ 7፥15
“በባቢሎንም አውራጃ ሁሉ የምታገኘውን ብርና ወርቅ ሁሉ፥ ሕዝቡና ካህናቱም በኢየሩሳሌም ላለው ለአምላካቸው ቤት በፈቃዳቸው የሚያቀርቡትን ትወስድ ዘንድ በንጉሡና በሰባቱ አማካሪዎች ተልከሃልና”
 — ዕዝራ 7፥16
“እኔም፦ ለአሕዛብ የተሸጡትን ወንድሞቻችንን አይሁድን በፈቃዳችን ተቤዠን እናንተስ ወንድሞቻችሁን ትሸጣላችሁን? እነርሱስ ለእኛ የተሸጡ ይሆናሉን? አልኋቸው። እነርሱም ዝም አሉ፥ መልሰም አላገኙም።”
 — ነህምያ 5፥8
“ኃጢአተኛ በነፍሱ ፈቃድ ይወደሳልና፥ ዓመፀኛም ይባርካል።”
 — መዝሙር 10፥3
“የሰውን ሥራ አፌ እንዳይናገር ፈቃዴ ነው፤ ስለ ከንፈሮችህ ቃል ጭንቅ የሆኑ መንገዶችን ጠበቅሁ።”
 — መዝሙር 17፥4
“የሐሰት ምስክሮችና ዓመፀኞች ተነሥተውብኛልና ለጠላቶቼ ፈቃድ አትስጠኝ።”
 — መዝሙር 27፥12
“ከፈቃዴ እሠዋልሃለሁ፤ አቤቱ፥ መልካም ነውና ስምህን አመሰግናለሁ፤”
 — መዝሙር 54፥6
“የኀጥኣን ፈቃድ የክፉዎች ወጥመድ ናት፤ የጻድቃን ሥር ግን ፍሬን ያፈራል።”
 — ምሳሌ 12፥12
“በንጉሥ ፊት ብርሃን ዘንድ ሕይወት አለ፥ መልካም ፈቃዱም እንደ በልግ ዝናብ ደመና ነው።”
 — ምሳሌ 16፥15
“ከፍ ያለውን ደግሞ ሲፈሩ፥ ድንጋጤም በመንገድ ላይ ሲሆን፤ ለውዝም ሲያብብ፥ አንበጣም እንደ ሸክም ሲከብድ፥ ፈቃድም ሲጠፋ፤ ሰው ወደ ዘላለም ቤት ሲሄድ፥ አልቃሾችም በአደባባይ ሲዞሩ፤”
 — መክብብ 12፥5
ዳንኤል 11
----------

3 ኃያልም ንጉሥ ይነሣል፥ በትልቅ አገዛዝም ይገዛል፥ እንደ ፈቃዱም ያደርጋል።
4 እርሱም በተነሣ ጊዜ መንግሥቱ ይሰበራል፤ እስከ አራቱ የሰማይ ነፋሳት ይከፋፈላል። ለዘሩ ግን

አይከፋፈልም፥ እንደ ገዛበትም አገዛዝ አይሆንም፤ መንግሥቱ ይነቀላልና፤ ከእነዚህም ለሌሎች ይሆናልና።

“ወደ አውራውም በግ ሲቀርብ አየሁት፤ እርሱም ተመረረበት፥ አውራውንም በግ መታ፥ ሁለቱንም ቀንዶች ሰበረ፤ አውራውም በግ ሊቋቋመው ኃይል አልነበረውም፥ እርሱም በምድር ላይ ጥሎ ረገጠው፤ አውራውንም በግ ከእጁ ያድነው ዘንድ የሚችል አልነበረም።”
— ዳንኤል 8፥7
“እርሾ ካለበትም የምስጋናውን መሥዋዕት አቅርቡ፥ በፈቃዳችሁም የምታቀርቡትን አውጁና አውሩ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።”
— አሞጽ 4፥5
“የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።”
— 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፥16-17
“የጌታን ስም የሚጠራም ሁሉ ይድናል።”
— ሐዋርያት 2፥21
“ፍለጋ የሌለውን የክርስቶስን ባለ ጠግነት ለአሕዛብ እሰብክ ዘንድ፥ ሁሉንም በፈጠረው በእግዚአብሔር ከዘላለም የተሰወረው የምሥጢር ሥርዓት ምን እንደሆነ ለሁሉ እገልጥ ዘንድ ይህ ጸጋ ከቅዱሳን ሁሉ ይልቅ ለማንስ ለኔ ተሰጠ፤”
— ኤፌሶን 3፥8-9
“ይህስ ስለ ምንድር ነው? በሥራ እንጂ በእምነት ጽድቅን ስላልተከተሉ ነው፤ እነሆ፥ በጽዮን የእንቅፋት ድንጋይና የማሰናከያ ዓለት አኖራለሁ በእርሱም የሚያምን አያፍርም ተብሎ እንደ ተጻፈ በእንቅፋት ድንጋይ ተሰናከሉ።”
— ሮሜ 9፥32-33
“እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም፥ እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል እንጂ አላት።”
— ዮሐንስ 4፥14
2ኛ ቆሮ 5
----------

14 ይህን ስለቆረጥን የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናልና፤ አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ፤ እንግዲያስ ሁሉ ሞቱ፤
15 በሕይወትም ያሉት ስለ እነርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጂ ወደ ፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ ስለ ሁሉ ሞተ።
“ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል፤ ስለ እኔ ግን ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ያገኛታል።”
— ማቴዎስ 16፥25
“እርሱም የኃጢአታችን ማስተሰሪያ ነው፥ ለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ኃጢአት እንጂ።”
— 1ኛ ዮሐንስ 2፥2
“ለመታዘዝ ባሪያዎች እንድትሆኑ ራሳችሁን ለምታቀርቡለት፥ ለእርሱ ለምትታዘዙለት ባሪያዎች እንደ ሆናችሁ አታውቁምን? ወይም ለሞት የኃጢአት ባሪያዎች ወይም ለጽድቅ የመታዘዝ ባሪያዎች ናችሁ።”
— ሮሜ 6፥16
ዮሐንስ 3
----------

16 በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን
እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።
17 ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፥ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና።
ሉቃስ 6
----------

47 ወደ እኔ የሚመጣ ሁሉ ቃሌንም ሰምቶ የሚያደርገው፥ ማንን እንዲመስል አሳያችኋለሁ።
48 ቤት ሲሠራ አጥልቆ የቆፈረ በዓለት ላይም የመሠረተ ሰውን ይመስላል፤ ጐርፍም በመጣ ጊዜ ወንዙ ያን
ቤት ገፋው፥ በዓለት ላይም ስለ ተመሠረተ ሊያናውጠው አልቻለም።
49 ሰምቶ የማያደርገው ግን ያለ መሠረት በምድር ላይ ቤቱን የሠራ ሰውን ይመስላል፤ ወንዙም ገፋው

ወዲያውም ወደቀ የዚያ ቤት አወዳደቅም ታላቅ ሆነ።
“ከፈቃዴ እሠዋልሃለሁ፤ አቤቱ፥ መልካም ነውና ስምህን አመሰግናለሁ፤”
— መዝሙር 54፥6
“እግዚአብሔር ሆይ፤ ፈቅጄ ያቀረብሁትን የአፌን የምስጋና መሥዋዕት ተቀበል፤ ሕግህንም አስተምረኝ።”
— መዝሙር 119፥108
“በሬው ወይም በጉ የተጨመረበት ወይም የጐደለበት ነገር ቢሆን፥ ለፈቃድ መሥዋዕት ማቅረብ ትችላለህ፤ ለስእለት ግን አይሠምርም።”
— ዘሌዋውያን 22፥23
“ወንድሞች ሆይ፥ እናንተ ለአርነት ተጠርታችኋልና፤ ብቻ አርነታችሁ ለሥጋ ምክንያትን አይስጥ፥ ነገር ግን በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ።”
— ገላትያ 5፥13
“የቍርባኑም መሥዋዕት የስእለት ወይም የፈቃድ ቢሆን፥ መሥዋዕቱ በሚቀርብበት ቀን ይብሉት፤ ከእርሱም የቀረውን በነጋው ይብሉት፤”
— ዘሌዋውያን 7፥16
“በመንግሥቴ ውስጥ ካሉ ከእስራኤል ሕዝብ ከካህናቱና ከሌዋውያኑም ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ የሚወድድ ሁሉ ከአንተ ጋር እንዲሄድ አዝዣለሁ።”
— ዕዝራ 7፥13
“ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ።”
— ሉቃስ 2፥14
“እርሱም መጥቶ የእግዚአብሔርን ጸጋ ባየ ጊዜ ደስ አለው፥ ሁሉንም በልባቸው ፈቃድ በጌታ ጸንተው ይኖሩ ዘንድ መከራቸው፤”
— ሐዋርያት 11፥23
“እነዚህም በተሰሎንቄ ከሚኖሩት ይልቅ ልበ ሰፊዎች ነበሩና፦ ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን? ብለው ዕለት ዕለት መጻሕፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ።”
— ሐዋርያት 17፥11
“ዳሩ ግን ይህን እንደ ፈቃድ እላለሁ እንጂ እንደ ትእዛዝ አይደለም።”
— 1ኛ ቆሮንቶስ 7፥6
“ይህን በፈቃዴ ባደርገው ደመወዝ አለኝና፤ ያለ ፈቃዴ ግን ባደርገው መጋቢነት በአደራ ተሰጥቶኛል።”
— 1ኛ ቆሮንቶስ 9፥17
“አሁንም ለማሰብ በጎ ፈቃድ እንደ ነበረ፥ እንዲሁ እንዳላችሁ መጠን መፈጸም ደግሞ ይሆን ዘንድ፥ ማድረጉን ደግሞ ፈጽሙ።”
— 2ኛ ቆሮ 8፥11
“ይህም ብቻ አይደለም ነገር ግን የጌታን የራሱን ክብርና የእኛን በጎ ፈቃድ ለማሳየት በምናገለግለው በዚህ ቸር ሥራ ከእኛ ጋር እንዲጓደድ በአብያተ ክርስቲያናት ደግሞ ተመረጠ።”
— 2ኛ ቆሮ 8፥19
“በጎ ፈቃዳችሁን አውቄአለሁና፤ ስለዚህም፦ አካይያ ከአምና ጀምሮ ተዘጋጅቶአል ብዬ ለመቄዶንያ ሰዎች በእናንተ እመካለሁ፥ ቅንዓታችሁም የሚበዙቱን አነሣሥቶአል።”
— 2ኛ ቆሮ 9፥2
“በእነዚህም ልጆች መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ፥ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን፥ በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን።”
— ኤፌሶን 2፥3
“ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምትገዙ በትጋትና በበጎ ፈቃድ ተገዙ፤”
— ኤፌሶን 6፥7
“አንዳንዶች ከቅንአትና ከክርክር እንኳ ሌሎች ግን ከበጎ ፈቃድ የተነሣ ክርስቶስን ይሰብኩታል፤”
— ፊልጵስዩስ 1፥15
“እንዲሁም እያፈቀርናችሁ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችንን ደግሞ እናካፍላችሁ ዘንድ በጎ ፈቃዳችን ነበረ፥ ለእኛ የተወደዳችሁ ሆናችሁ ነበርና።”
— 1ኛ ተሰሎንቄ 2፥8
“ነገር ግን በጎነትህ በፈቃድህ እንጂ በግድ እንዳይሆን፥ ሳልማከርህ ምንም እንኳ ላደርግ አልወደድሁም።”

— ፊልሞና 1፥14

"ሰው እግዚአብሔርን መፈለግ ይችላል።"
“ደግሞም ለአባቶቻቸው አምላክ ለእግዚአብሔር ይሠዉ ዘንድ ከእስራኤል ነገድ ሁሉ የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን ለመፈለግ ልባቸውን የሰጡ ሁሉ እነርሱን ተከትለው ወደ ኢየሩሳሌም መጡ።”
— 2 ዜና 11፥16

“ስለ እግዚአብሔርም ቤት አገልግሎት በጀመረው ሥራ ሁሉ፥ በሕጉና በትእዛዙም፥ አምላኩን ለመፈለግ በፍጹም ልቡ አደረገው፥ ተከናወነለትም።”— 2 ዜና 31፥21

“እግዚአብሔርን ፈለግሁት መለሰልኝም፥ ከመከራዬም ሁሉ አዳነኝ።”— መዝሙር 34፥4
**እምነት ከመወለድ ይቀድማል**

ሕዝቅኤል 18
----------

31 የበደላችሁትን በደል ሁሉ ከእናንተ ጣሉ አዲስ ልብና አዲስ መንፈስም ለእናንተ አድርጉ፤ የእስራኤል ቤት ሆይ፥ ስለ ምን ትሞታላችሁ?
32 የምዋቹን ሞት አልፈቅድምና፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ ስለዚህ ተመለሱና በሕይወት ኑሩ።"

""“ነገር ግን ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አትወዱም።”— ዮሐንስ 5፥40
“ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ ክርስቶስ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው እርሱ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ፥ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል።” — ሮሜ 8፥11"""
“በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፤”— ገላትያ 3፥26
**ሰው የእግዚአብሔርን ጥሪ አለመቀበል ይችላል።**
""“ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ሆይ፥ ነቢያትን የምትገድል ወደ እርስዋ የተላኩትንም የምትወግር፥ ዶሮ ጫጩቶችዋን ከክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ! አልወደዳችሁምም።”
— ማቴዎስ 23፥37
“ኢየሩሳሌም፥ ኢየሩሳሌም፥ ነቢያትን የምትገድል ወደ እርስዋ የተላኩትንም የምትወግር፥ ዶሮ ጫጩቶችዋን በክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ፥ እናንተም አልወደዳችሁም።”""
— ሉቃስ 13፥34
“ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና ደግሞም ሕያው ሆኖአል፤ ጠፍቶም ነበር ተገኝቶአልም። ደስም ይላቸው ጀመር።”
— ሉቃስ 15፥24

ማቴዎስ 13
----------

4 እርሱም ሲዘራ አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀ፥ ወፎችም መጥተው በሉት።
5 ሌላውም ብዙ መሬት በሌለበት በጭንጫ ላይ ወደቀ፤ ጥልቅ መሬትም ስላልነበረው ወዲያው በቀለ፥
6 ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ፥ ሥርም ስላልነበረው ደረቀ።
7 ሌላውም በእሾህ መካከል ወደቀ፥ እሾህም ወጣና አነቀው።
8 ሌላውም በመልካም መሬት ወደቀ፤ አንዱም መቶ፥ አንዱም ስድሳ፥ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ።
9 የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ።

...

18 እንግዲህ እናንተ የዘሪውን ምሳሌ ስሙ።
19 የመንግሥትን ቃል ሰምቶ በማያስተውል ሁሉ፥ ክፉው ይመጣል፥ በልቡ የተዘራውንም ይነጥቃል፤
በመንገድ ዳር የተዘራው ይህ ነው።
20 በጭንጫ ላይ የተዘራውም ይህ ቃሉን ሰምቶ ወዲያው በደስታ የሚቀበለው ነው፤
21 ነገር ግን ለጊዜው ነው እንጂ በእርሱ ሥር የለውም፥ በቃሉ ምክንያትም መከራ ወይም ስደት በሆነ ጊዜ
ወዲያው ይሰናከላል።
22 በእሾህ መካከል የተዘራውም ይህ ቃሉን የሚሰማ ነው፥ የዚህም ዓለም አሳብና የባለጠግነት መታለል
ቃሉን ያንቃል፥ የማያፈራም ይሆናል።
23 በመልካም መሬት የተዘራውም ይህ ቃሉን ሰምቶ የሚያስተውል ነው፤ እርሱም ፍሬ ያፈራል አንዱም መቶ
አንዱም ስድሳ አንዱም ሠላሳ ያደርጋል።